ጤናማ ሕይወት ለእናትነት
ገጽ 10

ያስጠጉትን ማጥቃት ከጥፋት ሁሉ የላቀ ጥፋት
ገጽ 12

ሲያከብሩን እንከበር!
ገጽ 14

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 138 ጥር 18 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# አቶ ደመቀ መኮንን

## ከብልጽግና ፓርቲ ም/ፕሬዚዳንትነት በክብር ተሰናበቱ

### - አቶ ተመስገን ጥሩነህ በቦታቸው ተተክተዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡፡- የብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አቶ ደመቀ መኮንንን ከምክትል ፕሬዚዳንትነት በክብር በመሸኘት አቶ ተመስገን ጥሩነህን ምክትል ፕሬዚዳንት አድርጎ መምረጡን አስታወቀ፡፡

ፓርቲው ከጥር 13 እስከ ጥር 17 ቀን 2016 ዓ.ም ያደረገውን የሥራ አስፈፃሚና የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ትናንት አጠናቋል፡፡

የብልጽግና ማዕከላዊ ኮሚቴ የፓርቲውን የአመራር የመተካካት መርሕን እና የአሠራር ሥርዓት በመከተል ነው አቶ ደመቀ መኮንንን በክብር የሸኘው፡፡

አቶ ደመቀ መኮንን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ከታጣቂ ቡድኖች ጋር የተጀመሩ ሠላማዊ አማራጮች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ብልጽግና ፓርቲ አስታወቀ

### - የባሕር በር ስምምነቱ ወደትግበራ እንዲደርስና ተጨማሪ አማራጮችን ለማግኘት ትኩረት ተደርጓል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የተሟላ ሀገራዊ ሰላም ለማስፈን ከታጣቂ ቡድኖች ጋር የተጀመሩ ሰላማዊ አማራጮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አቅጣጫ ማስቀመጡን ብልጽግና ፓርቲ አስታወቀ፡፡

ከሶማሌ ላንድ ጋር የተደረገውን የመግባቢያ

ከታጣቂ ቡድኖች ጋር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «የቀጣናው ሀገራትን በኢኮኖሚ በማስተሳሰር የጋራ ተጠቃሚነትን ማስፈን የኢትዮጵያ የምንጊዜም ፍላጎት ነው»

-አቶ ታገሰ ጫፎ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡፡- የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን በኢኮኖሚ በማስተሳሰር የጋራ ተጠቃሚነትን ማስፈን የኢትዮጵያ የምንጊዜም ፍላጎትና ጥረት መሆኑን የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ ገለጹ፡፡ የምሥራቅ አፍሪካ የአርብቶ አደሮች ኤክስፖ ትናንት በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ተከፍቷል፡፡

አቶ ታገሰ ጫፎ ኤክስፖውን በከፈቱበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ ኤክስፖው ትስስራችን

«የቀጣናው ሀገራትን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡፡ ገበዩ ገብሬ

## «በኢትዮጵያና በሶማሌላንድ መካከል የተደረሰውን ስምምነት ማወክ ለአጀንዳ 2063 ዝግጁ አለመሆን ነው»

-ሽብሩ ማሞ-
በታንዛንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡፡- በኢትዮጵያና በሶማሌላንድ መካከል የተደረሰውን የባሕር በር የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ማወክ ለአጀንዳ 2063 ዝግጁ አለመሆን ነው ሲሉ በታንዛንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሽብሩ ማሞ አስታወቁ፡፡

አምባሳደር ሽብሩ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአፍሪካ አጀንዳ በ2063 አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ መገንባት የሚል ራዕይ አንግቦ እየሠራ ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር አንድ የመገበያያ ገንዘብ መፍጠር፣ የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን መፍታት፣ ግጭትን ማስወገድና በጋራ ማደግ የሚል ራዕይ እንዳለው

«በኢትዮጵያና በሶማሌላንድ ... ወደ ገጽ 4






# በመዲናዋ በስድስት ወራት ከ13 ሚሊዮን ካሬ በላይ መሬት ወደመሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል

**አመለወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡-በከተማዋ በ2016 በጀት ዓመት በስድስት ወራት ከ13 ሚሊዮን ካሬ ሜትር በላይ መሬት ወደመሬት ባንክ እንዲገባ መደረጉን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን አስታወቀ።

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የ2016 በጀት ዓመት የስድስት ወር አፈጻጸም ግምገማ እና በቀጣይ ስድስት ወር አቅጣጫዎች ላይ ወይይት ባደረገበት ወቅት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ግማሽ ወራት በከተማው በተለያዩ ቦታዎች የመሬት ይዞታ ጥናት በማድረግ ከ13 ሚሊዮን ካሬ በላይ መሬት ወደመሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በስድስት ወራት ኮሚቴ በማቋቋም የመንግሥት፣ የግለሰብ፣ የአርሶአደር እና በልማት ላይ ያለው መሬት የትኛው እንደሆነ ጥናት ተደርጓል። በዚህም በቦታ 7 ሺህ 364፤ በካሬ ከ13 ሚሊዮን በላይ መሬት ወደመሬት ባንክ ገብቷል።

መሥሪያ ቤቱ የተረከባቸውን መሬቶች ከወረራ መጠበቅ ሌላኛው ኃላፊነቱ እንደሆነ የገለጹት ሻለቃ ዘሪሁን፤ በግማሽ ዓመቱ በከተማዋ በ26 ቦታዎች ላይ የወረራ ሙከራ የተደረገ ሲሆን፤ በደንብ አስፈጻሚዎች አማካኝነት ማስቀረት ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል።

ወደመሬት ባንክ ከገቡት 7 ሺህ 364 ቦታዎች 88 ቦታዎች፤ በካሬ 96 ሺህ ካሬ መሬት ለልማት ተላልፏል። በዚህም የመሬት ይዞታው ለልማት ሲተላለፍ ከመሬት አስተዳደር በኩል መሬቱ የሚተላለፍለት አካልና ሌሎች መረጃዎች ተሟልተው ለባለሥልጣኑ ከተላከ በኋላ ነው ከመሬት ባንክ እንዲወጣ የሚደረገው ሲሉ አስረድተዋል።።ሕገወጥ ግንባታን ከመቆጣጠር ረገድ በግማሽ ዓመቱ በ3 ሺህ 290 ሕገወጥ ግንባታዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ ከ3 ሺህ 700 በላይ ግንባታዎች ላይ እርምጃ መወሰዱ ተገልጿል።

ባለሥልጣኑ በሕገወጥ ተግባራት ላይ በወሰደው እርምጃ ከተወረሰ ንብረት፣ ከቅጣት ክፍያ እና ከጨረታ ከ18 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘቱንም ተናግረዋል።።

ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፤ በመንፈቅ ዓመቱ ሕገወጥ የጎዳና ንግድን ከመቆጣጠር ረገድ ሕገወጥ ነጋዴዎች ወደ ሕጋዊ መንገድ እንዲመጡ፤ የከተማዋን ፅዳት ከመጠበቅ እንዲሁም ለደንብ አስከባሪዎች የተለያዩ ሥልጠናዎችን ከመስጠት ረገድ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በቀጣይ ስድስት ወራት ያሉትን ክፍተቶች በመገምገም በቀጣይም የሚገጥሙትን የደንብ ጥሰቶች ለመከላከል ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር በጋራ እንደሚሠራ አስረድተዋል።

ሻለቃ ዘሪሁን አያይዘው እንደገለጹት በቀጣይ ወር ላይ ለሚካሄደው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ኮሚቴ ተቋቁሞ የከተማዋን ፅዳት ከማስጠበቅ እና ለእንግዶች ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አኳያ እየተሠራ ይገኛል።

# የከተሞች መሠረተ ልማት ፕሮግራም ትግበራ ላይ የማጣራት ሥራ ተጀመረ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ በ600 ሚሊዮን ዶላር እየተተገበረ ያለው የከተሞች መሠረተ ልማት ፕሮግራም ላይ የማጣራት ሥራ መጀመሩን የፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ።

በኮሚሽኑ የኮሚሽነር የጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ የማጣራት እንቅስቃሴውን አስመልክተው እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በ117 ከተሞች ላይ እየተተገበረ ይገኛል።

ፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ እንደ መንገድ፤ መብራት፤ ውሃና መፀዳጃ ቤት ያሉ መሠረተ ልማቶችን ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ እነዚህ ፕሮጀክቶች በጥራት ተሠርተው ለማኅበረሰቡ በወቅቱ ተደራሽ እንዲሆኑ እንደሚጠበቅና ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሥራ ዕድል ፈጠራውም የማኅበረሰቡ ተጠቃሚነት ይጠበቃል ብለዋል።

አቶ ተስፋዬ እንደተናገሩት፤ በዚህ ሂደት መሬት ለግለሰቦች፤ ለድርጅቶችና ለማኅበራት የሚተላለፍባቸው አግባቦች በመኖራቸው ለሙስና በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ መመሪያ በመጣስ እንዲሁም ከአቅምና ኅብረተሰብን ከማሳተፍ ረገድ ችግር ይስተዋላል። በዚህም የመሬት ወረራን ጨምሮ ይዞታ ሲሰጥ የተለያዩ ጥሰቶች ይፈጸማሉ። እንደ አጠቃላይም መሬት ከጥቃቅን እስከ ከፍተኛ ደረጃ ሙስና እና የፖለቲካ ሙስና የሚሠራበት ነው።

በመሆኑም ከተሞች መሠረተ ልማት ፕሮግራም ማኅበረሰቡ ከሥራ እድል ፈጠራና ከፕሮጀክት ግንባታ ጥራትና የተመደበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ እየዋለ መሆኑን እንዲሁም ማኅበረሰቡ የሚጠቀምበትን መሠረተ ልማቶች ከሙስናና ብልሹ አሠራር፤ ከተጠያቂነትና ከማኅበረሰቡ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሂደቱን የመፈተሽ ሥራ የሚከናወን ይሆናል ብለዋል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993
ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ኮሚሽኑ ባለፈው ዓመት በ25 ዘርፎች ላይ የሙስና ተጋላጭነት ጥናት አከናውኖ ነበር ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በዚህም የተቋማት አመራሮች፣ ሚኒስትሮችና ሚኒስትር ዴኤታዎች በተገኙበት ውይይት ተካሂዷል ሲሉ ገልጸዋል።

ጥናቱ መሬት እንዲወርድም አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ቢሆንም በአሁኑ የከተማ ዘርፍ የመሠረተ ልማት ተቋማዊ ፕሮግራም የመሬት ካዳስተር አያያዝ በከተሞች ነዋሪው ምን ያህል ያውቀዋል፤ ችግር ቢገጥም ጥቆማ እንዲሰጥ ምን ያህል ግልጽነት ተፈጥሯል፤ የሚለው ሁሉ የሚገመገም ይሆናል ብለዋል።

ለዚህም ለቀጣይ ሀያ ቀናት በሀገር አቀፍ ደረጃ በአስራ አንድ ከተሞች አስራ አንድ የጥናት ቡድን የመስክ ምልከታን ጨምሮ በተለያየ መንገድ የቁጥጥር ሥራዎችን እንደሚያከናውን አቶ ተስፋዬ ጠቁመው፤ ለትግበራውም በተቋቋመው የፌዴራልና የክልል ኮሚሽኖች አባላት እና ከተለያዩ ተቋማት የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ባለሙያዎች እንዲሁም ጋዜጠኞችም የሚሳተፉበት ይሆናል ብለዋል።

# የሲቪክስ ትምህርት ከ12ኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና መውጣቱ የሚፈጥረው ተፅዕኖ የለም

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የሥነ ዜጋ እና ሥነ ምግባር ትምህርት ከማጠቃለያ ፈተና ላይ መውጣቱ በተማሪዎች ውጤትና ባሕሪ ላይ ተፅዕኖ እንደማይፈጥር ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የማኅበራዊ ሳይንስ ትምህርቶች ሥርዓተ ትምህርት ዴስክ ኃላፊ የሆኑት አቶ ዑመር ኢማም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በዘንድሮ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውስጥ የሥነ ዜጋ እና የሥነ ምግባር ትምህርት እንዳይካተት ተደርጓል።


እንደ አቶ ዑመር ገለጻ፤ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚሰጡ ሲሆን ሥነ ዜጋ እና ሥነ ምግባር የሚባል ትምህርት ግን በአሁኑ ጊዜ ከ10ኛ ክፍል በላይ አይሰጥም።። ተማሪዎች የሚመዘኑት በአራት ዓመት ቆይታቸው (ከ9ኛ እስከ 12ኛ) ነው።

በዚህ ምክንያት የሥነዜጋና ሥነምግባር የትምህርት ዓይነት ከማጠቃለያ ፈተናው ሊወጣ ችሏል።

ከአንደኛ ክፍል እስከ ስድስተኛ ክፍል እንደ ድሮ የሥነ ዜጋ ይዘት ያለው ሳይሆን የሥነ ምግባር ይዘቱ ለብቻ ተነጥሎ እንዲሰጥ መደረጉን በመጥቀስ፤ በተለይ ሰብዓዊነት፣ ማኅበራዊ ሕይወት እና ሥነ ሥርዓት ላይ ዜጋ የሚታነፅበት ትምህርት እየተሰጠ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

በተመሳሳይ ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሥነ ዜጋ እና ሥነ ምግባር ውሕድ ሆኖ ዲሞክራታይዜሽን፣ ዜግነት፣ የአስተዳደር ዓይነቶችና የመንግሥት አወቃቀርን የሚያውቁበት ትምህርት እንዲሰጥ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተወስኖ ወደ ተግባር መግባቱን አስረድተዋል።

ብሔራዊ ፈተና ላይ ለማኅበራዊ ሳይንስ እና ለተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች የሚሰጠው ፈተና እኩል መሆን አለበት ያሉት አቶ ዑመር፤ ተመሳሳይ የትምህርት



ዓይነት የሆኑትን እንግሊዘኛ እና ሒሳብ ሁሉም ተማሪዎች እንደሚፈተኑ ጠቅሰዋል።

ለተፈጥሮ ሳይንስ ሒሳብ እና እንግሊዝኛን ጨምሮ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ እና አፕቲትዩድን የሚፈተኑ ሲሆን፤ የማኅበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ደግሞ እንግሊዘኛ፣ ሒሳብ፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ኢኮኖሚክስና አፕቲትዩድን እንደሚፈተኑ መወሰኑን አስረድተዋል።

ዜና

# «ለሰብዓዊ ድጋፍ ምላሽ ሕዝብና የሀገር ውስጥ ተቋማትን አቅም መጠቀም ያስፈልጋል»

- አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም
የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- ለሰብዓዊ ድጋፍ ምላሽ ለመስጠት የሕዝብና የሀገር ውስጥ ተቋማትን የተጠናከረ አቅም መጠቀም እንደሚገባ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም ገለጹ።።

ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በድርቅ፣ በግጭትና በሌሎች ምክንያቶች ሰብዓዊ ድጋፍ ለሚፈልጉ ዜጎች በሕዝብና በተቋማት አቅም ምላሽ ለመስጠት ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል።።

በኢትዮጵያ ድርቅና የጎርፍ አደጋ በተደጋጋሚ እያጋጠመና ጉዳት እያደረሰ መሆኑን ጠቁመው፤ ሰብዓዊ ድጋፍ የሚፈልጉ ዜጎች ለከፋ ጉዳት እንዳይዳረጉ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።።

በድርቅና ጎርፍ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ኅብረተሰቡንና የተለያዩ ተቋማትን በማስተባበር የሰብዓዊ ርዳታ በእራስ አቅም ለመቅረፍ ሰፊ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ባለፉት ሁለት ወራት ባጋጠመ የጎርፍ አደጋ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ለጉዳት መዳረጋቸውን የገለጹት ኮሚሽነሩ፤ በተለይ የቅድሚያ ቅድሚያ አስቸኳይ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች በመለየት በኮሚሽኑ በኩል ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በ2015 ዓ.ም የድርቅ አደጋ በአማራ ስምንት ዞኖች ላይ፣ በትግራይ አራት ዞኖች ላይ በአፋር ሦስት ዞኖች ላይ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልል አካባቢዎች ችግሩ በመከሰቱ አራት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ለችግር መዳረጋቸውን አስታውሰዋል።

ችግሩ በተከሰተባቸው አከባቢዎች የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች እርስ በእርስ እየተደጋገፉ ናቸው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ከክልል እስከ ቀበሌ ያለው መዋቅር ለችግሩ ትኩረት ሰቶ እየሠራ ነው ብለዋል።።

ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ዋነኛ የሰብዓዊ ድጋፍ አቅራቢዎች በአካባቢው የሚገኙ የተለያዩ ዜጎች መሆናቸውንም ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።

መንግሥት 11 ቢሊዮን ብር በመመደብ ለዜጎች የሚያስፈልውን የእህልና የተለያዩ ቁሳቁሶች ድጋፍ በሦስት ዙር ማድረሱን ጠቅሰው፤ የአጋር አካላትን ጨምሮ ለስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች የሚውል ዘጠኝ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚገመት የሰብዓዊ ድጋፍ ከጥር ወር ጀምሮ እየቀረበ መሆኑን አስታውቀዋል።

በአንድ አንድ አካላት በኩል መንግሥት የሚያደርገውን ሰብዓዊ ድጋፍ የማሳነስ፣ ትኩረት ያልተሰጠው አስመስሎ የመመልከት ችግር መኖሩን ጠቁመው፤ ይህም ለግል ጥቅም ሲባል የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው ብለዋል።።

ለችግሩ ዘላቂ ምላሽ ለመስጠት መንግሥት ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።።

የግል ባለሀብቶችን ጨምሮ ሁሉም አካላት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ርብርብ ሊያደርጉ ይገባል ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላለፈዋል።።



ፎቶ፡- ሀዲስ አብርሃ

# በጅማ ዞን ዘንድሮ 54 ቶን ማር ይሰበሰባል

**ውብሸት ሰንደቁ**

ጅማ፡- በዞኑ 54 ቶን ማር ተሰብስቦ 10 ቶን ማር ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን የጅማ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ መሐመድ ጠሃ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ ቀደም ብሎ ኦሮሚያን የማር ባሕር እናደርጋለን የሚል ንቅናቄ መጀመሩን ተከትሎ በማር ምርት ላይ ከፍተኛ መነቃቃት ተፈጥሯል።

በዚህም በተያዘው ዓመት 54 ሺህ ቶን የማር ምርት ለማምረት እየተሠራ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ ከሚመረተው አጠቃላይ ምርት 10 ሺህ ቶን ለውጭ ገበያ ይቀርባል ብለዋል።

እንደ አቶ መሐመድ ገለፃ፤ የማር ምርት ንቅናቄው በተጀመረባቸው ሦስት ዓመታት ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል። ጅማ ዞን የማር ምርት ንቅናቄውን ፈጥኖ የተቀላቀለ ዞን ነው።

በዘመናዊ ንብ ማነብ ላይ የተሠራው ሥራም ውጤት አሳይቷል ያሉት ከንቲባው፤ የጅማ ዞን በቡና የሚታወቀውን ያህል በማር ምርትም ግንባር ቀደም ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ስለመሆኑ አብራርተዋል።

ዞኑ በአካባቢው ያለውን የማር ምርት አቅም አስጠንቶ ወደሥራ እንደገባ ገልፀውም፤ በዘርፉ ያሉ ችግሮችም ተለይተው መፍትሔ ተቀምጦላቸዋል ብለዋል።

ኃላፊው እንዳሉት፤ የማር ምርት በዞኑ በ62 ሺህ ዘመናዊ ቀፎዎች ነው የተጀመረው። ይህን ቁጥር በከፍተኛ መጠን በመጨመር ምርትና ጥራትን ለማሳደግ የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በዚህም ሦስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የዘመናዊ ቀፎዎችን ቁጥር 388 ሺህ ማድረስ መቻሉን ተናግረው፤ ይህ ኦሮሚያን የማር ባሕር እናደርጋለን በሚል የተጀመረውን ንቅናቄ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው ሲሉ ገልፀዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ 167 ሺህ ዘመናዊ የንብ ቀፎዎች መሰራጨታቸውንም አመላክተዋል።

የዘመናዊ ቀፎዎች ዓመታዊ አማካይ የምርት መጠን 70 ኪሎ ግራም መሆኑን ጠቅሰው፤ የዘመናዊ የንብ ቀፎዎች አማካይ የምርት መጠን 33 ኪሎ ግራም መሆኑን በንፅፅር አሳይተዋል።

በተያዘው ዓመት በዞኑ 54 ሺህ ቶን የማር ለመሰብሰብ እየተሠራ እንደሚገኝም አብራርተዋል። ከዚህ ውስጥም 10 ሺህ ቶን ለውጪ ገበያ ይቀርባል ብለዋል።

ምርቱን ለውጭ ገበያ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለማቅረብ ከባለሃብቶች ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑንም ጠቅሰዋል።



# የንባብ ባሕሉን ያዳበረ ትውልድ ለማፍራት አማራጮችን የማስፋት ሥራዎች ይጠናከራሉ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ። -የንባብ ባሕሉን ያዳበረ ትውልድ ለማፍራት አማራጮችን የማስፋት ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ‹‹ንባብና ሀገር›› የተሰኘ ከተማ አቀፍ የንባብ ፌስቲቫል “አንባቢ ትውልድ ለሀገር ብልጽግና” በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ሙዚየም ከትናንት በስቲያ አስጀምሯል።።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የባሕል ዘርፍ ምክትል ኃላፊ አስፋው ኩማ እንደገለጹት፤ ሀገር የምትገነባው በእውቀትና በሥነምግባር በታነጹ ዜጎች ነው።። ይህ ደግሞ ያለ አንባቢ ትውልድ የሚታሰብ አይደለም።።

8ተኛው ከተማ አቀፍ የንባብ ፌስቲቫልም የንባብ ባሕል በማኅበረሰብ ደረጃ እንዲያብብና ሀገርን የሚያሻግር ትውልድ እንዲፈጠር ዓላማ ያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ በከተማዋ የንባብ ባሕልን ያዳበረ አንባቢ ትውልድ ለማፍራት የተጀመሩ ተግባራት ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።።

መጽሐፍት እውቀትን ከማሻገር ባለፈ በትውልዶች መሐከል ጠንካራ ትስስሮች ይፈጥራሉ ያሉት አቶ አስፋው፤ የከተማዋ ወጣቶች የንባብ ባሕልን እንዲያዳብሩ አስገንዝበዋል።።

ከተማዋን ለንባብ የበለጠ ምቹ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት የተለያዩ አካላት እንደሚሳተፉ ጠቁመው፤ በሳምንቱም በጎ ፍቃደኛ ባለሀብቶችንና ደራሲያንን በማቀናጀት ቤተ መጽሐፍትን የመጎብኘትና የጎደለውን የመሙላት ሥራ የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።።

የአዲስ አበባ ምክር ቤት የባሕል፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶሜ አበበ (ዶ/ር) በበኩላቸው ማንበብ ታሪክን ለማወቅ ብሎም የሚያግባባ ትውልድ መፍጠር ያስችላል ብለዋል።።

ማንበብ ዛሬ ላይ ነገን መሥራት መቻል ነው ያሉት ሰብሳቢዋ፤ ለዚህም መደበኛ የንባብ ቦታዎችን በስፋት መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።።

ዛሬ ልዩነትን ወደ ጎን ትቶ በአመክንዮ የሚግባባ ትውልድ ለመፍጠር አንብቦ የሚያስነብብ ትውልድ ያሻል ነው ያሉት ።።

አቶሜ (ዶ/ር) አንባቢ ትውልድ ላይ መሥራት ለሀገር ግንባታ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ገልጸው፤ ለዚህም ወላጆች ልጆቻቸው የንባብ ባሕልን እንዲያጎለብቱ መሥራት እንዳለባቸውም አመልክተዋል።።

ፌስቲቫሉ በየክፍለ ከተማ የሚገኙ ቤተ መጽሐፍት እንዲሁም ከ50 በላይ የሚሆኑ ተቋማት የሚሳተፉበት ሲሆን ከጥር 16 እስከ ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚቆይ ታውቋል ።።

ዜና

# ዲያስፖራዎች በታርጫ ከተማ ኢንቨስትመንትና መሠረተ ልማት ግንባታ እየተሳተፉ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

ታርጫ፡- የዳውሮ ተወላጅ ዲያስፖራዎች የዞኑ መቀመጫ በሆነችው ታርጫ ከተማ የኢንቨስትመንት እና የመሠረተ ልማት ሥራዎች ላይ ተሳትፎ እያደረጉ መሆኑን የከተማዋ ከንቲባ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

በዳውሮ ዞን የታርጫ ከተማ ከንቲባ ዳዊት ወንድሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዳውሮ ዞን ተወላጅ ዲያስፖራዎች በግልና በቡድን ሆነው አካባቢያቸውን እየደገፉ ነው።

የታርጫ ከተማ በአሁኑ ወቅት የደቡብ ምዕራብ ክልል ማኅበራዊ ዘርፍ እና የዳውሮ ዞን መቀመጫ ሆና እያገለገለች ትገኛለች።

በታርጫ ከተማ ከተመቻቹ የኢንቨስትመንት አማራጮች አንዱ



ፎቶ፡፡ ሀዲስ አብርሀ

**አቶ ዳዊት ወንድሙ**

በሆነው የሪል ስቴት ዘርፍ ዲያስፖራዎች በቡድን ተደራጅተው እየተሳተፉ ነው ብለዋል።

የተደራጁት ዲያስፖራዎች በ200 ሚሊዮን ብር መነሻ ካፒታል የሪል ስቴት ልማት መሬት ተረክበው ወደ ሥራ እንደገቡም ገልፀዋል።

በአሁኑ ወቅትም አራት ሄክታር መሬት ላይ ሥራቸውን እያከናወኑ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

ሪል ስቴት ልማቱ በጅማሮ ላይ እያለ ለ27 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ጠቅሰው፤ በማጠቃለያ ጊዜው ከ500 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቅሰዋል።

በተመሳሳይ በግለሰብ ደረጃ ለዞኑ ድጋፍ የሚያደርጉ እንዳሉ የጠቀሱት ከንቲባ ዳዊት፤ ለመንገድና መሠረተ ልማት አገልግሎት የሚውል 30 ሺህ ዶላር ከአንድ ግለሰብ መለገሱን አስረድተዋል።

የአካባቢው ተወላጅ ዲያስፖራዎች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሳተፍ ፍላጎት እያሳዩ ነው ያሉት ከንቲባው፤ በተለይ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጥሪን ተከትሎ መነቃቃት ታይቷል ሲሉ ገልፀዋል።

እንደ ከንቲባው ገለፃ፤ በዞኑ በማዕድን ልማት፣ በሪል ስቴት፣ በፍራፍሬ ማቀነባበሪያ እንዲሁም በሆቴልና አገልግሎት የኢንቨስትመንት አማራጮች ባለሃብቶች እየተሳተፉ ነው።

ዞኑ በተለይ በማዕድን፣ በፍራፍሬና በአገልግሎት እንዲሁም ሌሎች ዘርፎች ያልተነካ እምቅ አቅም እንዳለው ተናግረዋል።

በዳውሮ ዞን የምትገኘው ታርጫ ከተማ የዞኑ መቀመጫ፣ በደቡብ ምዕራብ ክልል የማኅበራዊ ክላስተር መቀመጫ እንዲሁም በመልማት ላይ የምትገኝ ከተማ መሆኗ ባለሀብቶች ኢንቨስት ቢያደርጉ ብዙ ያተርፋሉ ሲሉም ገልፀዋል።

ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች እና ሌሎች ዝግጅቶችን ከኅብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት እያከናወኑ መሆኑንም አቶ ዳዊት ገልጸዋል።።

# «የቀጣናው ሀገራትን በኢኮኖሚ በማስተሳሰር..

ከገጽ 1 የዞረ

ምን ያህል የጠነከረ፣ አጥርና ድንበር የሌለን ወንድማማቾችና እህትማማቾች መሆናችንን በግልፅ የሚያሳይ ነው። ይህንን ትልቅ እሴት በኢኮኖሚ በማስተሳሰር የጋራ ተጠቃሚነትን ማስፈን የኢትዮጵያ የምንጊዜም ፍላጎትና ጥረት ነው ብለዋል።

አርብቶ አደሩ አጥርም ድንበርም የለውም ያሉት አቶ ታገሰ፤ የቀጣናችንን ትስስር ለማጠናከር፣ አብሮ ለመበልፀግ እንዴት መጓዝና መደመር እንዳለብን ብዙ ይነግረናል ብለዋል።

እንደ አፈ ጉባኤው ገለጻ፤ ስንደመር ውበት እንጨምራለን፤ ኃይላችን ይበረታል። በመሆኑም ሀገራቱ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ብቻ ሳይሆን በታሪካቸው እና በሥነ ሕዝባዊ ባሕሪያቸው ያላቸውን የቅርብ ዝምድና አቅም አድርገን ወደ ብልፅግና ፈጥነን መራመድ እንደሚገባን አጥብቀን ማሰብ ይኖርብናል።

የአርብቶ አደር አካባቢዎች በተፈጥሮ ሀብት የበለጸጉ ቢሆኑም ገዝፎ የሚታየው የከፋ ድርቅ፣ ጎርፍ፣ ስደትና ግጭቶች መሆናቸውን አስታውሰው፤ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የሚከሰተው ተደጋጋሚ ድርቅና የምግብ ዋስትና እጦትም የእነዚህ አካባቢዎች መለያ ናቸው። ይህንን መልክ ለመለወጥ ከምንጊዜውም በላይ ቀጣናዊ ትስስርን ማጥበቅ ቀዳሚው ጉዳይ መሆን እንዳለበት አመላክተዋል።

በአርብቶ አደሮች መካከል ያለውን የባሕልና የደም ትስስር ወደ ኢኮኖሚ ትስስር ፈጥኖ መቀየር ለነገ የሚባል የቤት ሥራ እንዳልሆነ ጠቁመው፤ የቀጣናውን ሀገራት በኢኮኖሚ በማስተሳሰር የጋራ ተጠቃሚነትን ማስፈን የኢትዮጵያ የምንጊዜም ፍላጎትና ጥረት ነው። የምትገነባቸው ግዙፍ ፕሮጀክቶቿ ጎረቤቶቿንም እንዲጠቅሙና ከበረከቱም አብረው እንዲካፈሉ ማድረግ የቁርጠኝነቷ ማሳያ ነውም ብለዋል።

የተጀመረው የትስስር መንፈስ ተጠናክሮ አካባቢው የተቸረውን ውድ የተፈጥሮ ስጦታ በጋራ አልምተን፣ በጋራ ተጠቅመን፣ ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነታችን ባሻገርም የቀጣናችንን ሠላም እያረጋገጥን ለመጓዝ የተከፈተውን ኤክስፖ መሰል መድረኮች ትልቅ አቅም የሚፈጥሩ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትር ኢንጅነር አይሻ መሐመድ በበኩላቸው፤ የቀጣናው አርብቶ አደሮች የሚጋሯቸው የተፈጥሮ ሀብቶችና ፈተናዎች የጋራ ተጠቃሚነትን ለማጠናከር ምን ያህል ቁርጠኛ መሆን እንዳለብን ትምህርት የሚሆን ነው።

እነዚህ አርብቶ አደሮች ቀጣናዊ ትስስርን፣ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥና ቀጣናዊ ሠላምን ለማስፈን ትልቅ ማሳያዎች የሚሆኑ መሆናቸውንም ጠቅሰዋል።

አርብቶ አደሮች ለቀጠናው የሚያበረክቱት ሁለንተናዊ አስተዋፅዖ እንዳለ ሆኖ በተለይ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ ብዙ ችግሮች እንዳሉባቸው አስታውሰው፤ ለችግሮቻቸው መፍትሔ ለመስጠትና በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት በጋራ መሥራት እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ በየነ መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) ዋና ፀሐፊ አቶ ወርቅነህ ገበየሁ በተወካያቸው ባስተላለፉት መልዕክት፤ አርብቶ አደርና አርብቶ አደርነት የቀጣናው ሀገራትን ትብብር በማጠናከር በኩል ጉልህ ሚና አለው።

ለአርብቶ አደሮች አበርክቶ እውቅና ለመስጠት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 2026ን ‹‹የአርብቶ አደሮች ዓመት›› ተብሎ እንዲከበር መወሰኑን አስታውሰው፤ የኢጋድ አባል ሀገራትና ዲፕሎማቶች ይህ እውን እንዲሆን እንዲሠሩም ጠይቀዋል።

ከአህጉሪቱ እንስሳት ሀብት ከፍተኛው ድርሻ በዚህ ቀጣና እንዳለ ጠቁመው፤ በዚህም ኢኮኖሚውን በመደገፍና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችል ትልቅ አቅም ነው ብለዋል።

በመሆኑም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በሚከሰት የመሬት መራቆትና በሌሎችም ጉዳዮች የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ ተባብሮ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ አሳስበዋል።

ኢጋድም የቀጣናውን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡና ችግሮችን በሚቀር ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶ አደሮች ኤክስፖ "አርብቶ አደርነት የምስራቅ አፍሪካ ኅብረ ቀለም" በሚል መሪ ሀሳብ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ከኢጋድ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ኤክስፖ እስከ ጥር 23 ቀን 2016 የሚቆይ ይሆናል።

# ከታጣቂ ቡድኖች ጋር የተጀመሩ ሠላማዊ አማራጮች...

ከገጽ 1 የዞረ

ስምምነት ወደ ተግባራዊነት ለማድረስ፣ ከሌሎች ጎረቤት ሀገራትም ጋር ተጨማሪ የባሕር በር አማራጮችን በሰጥቶ መቀበል መርሕ ለማግኘት ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሠራም ፓርቲው ውሳኔ አሳልፏል።

የ2016 የበጀት ዓመት የኢኮኖሚ ዕድገት 7.9 በመቶ እንደሚሆን ተተንብዮአል። ይሄንንም ለማሳካት አመራሩና አባላቱ ከሕዝቡ ጋር በመሆን በቀሪ ጊዜያት ጠንክረው መሥራት እንዳለባቸው ተወስኗል።

ብልጽግና ፓርቲ ከጥር 13 እስከ ጥር 17 ቀን 2016 ዓ.ም ያደረገውን የሥራ አስፈፃሚና የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባውን መጠናቀቅ አስመልክቶ መግለጫ አውጥቷል።

የኢኮኖሚ ዕድገቱ አሁን ካለበት ደረጃ እንዳይቀጥል አንዱ ዕንቅፋት በጠባብ ቡድናዊ ፍላጎት የተፈጠሩ ትሥሥሮች ያስከተሏቸው አካባቢያዊ ግጭቶች መሆናቸውን በመግለጫው አመላክቷል።

እነዚህን ግጭቶች በመፍታት የብልጽግና ጉዞን ይበልጥ ለማፋጠንና የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል አግባብ የተሟላ ሀገራዊ ሰላም ለማስፈን እንዲቻል ከታጣቂ ቡድኖች ጋር የተጀመሩ ሠላማዊ አማራጮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ፓርቲው አቅጣጫ አስቀምጧል።

በሠላማዊ የፖለቲካ መንገድ ጥያቄዎቻቸውን ለሚያቀርቡ አካላት ሠላማዊ መንገዶች እስከሚቻለው ድረስ እንዲመቻቹ፤ ፍላጎታቸውን በነፍጥ ማስፈጸም ዓላማቸው በሆኑ አካላት ላይ ደግሞ፣ ተገቢው ሕግን የማስከበር ሥራ በተጠናከረ መንገድ እንዲካሄድ ውሳኔ አሳልፏል።

በፕሪቶርያው ስምምነት የተገኙ የሠላም ፍሬዎችን በመንከባከብ፣ የጎደሉ ክፍተቶችን በመሙላት፣ ወደ ዘላቂ ሰላም እንዲሸጋገር ፓርቲው የተጀመሩ ጥረቶችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አሳውቋል።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ እያደገ ከሚሄደው የሕዝብ ብዛቷና ኢኮኖሚዋ ጋር የሚመጣጠን የባሕር በር እንደሚያስፈልጋት ፓርቲው ካስቀመጠው አቅጣጫ በመነሣት፣ የተከናወኑ ተግባራትን ገምግሟል።

ከሶማሌ ላንድ ጋር የተፈረመው የመግባቢያ ስምምነት ኢትዮጵያ ለቀጣናዊ የኢኮኖሚና የባሕል ትሥሥር ያላትን አቋም የሚያሳይ መሆኑን አመላክቷል።

በቀጣይም የተጀመረውን የመግባቢያ ስምምነት ወደ ተግባራዊ ስምምነት ለማድረስ፣ ከሌሎች ጎረቤት ሀገራትም ጋር ተጨማሪ የባሕር በር አማራጮችን በሰጥቶ መቀበል መርሕ ለማግኘት ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሠራ ፓርቲው ውሳኔ አሳልፏል።

የዘመነ መረብ ጥቅሞችን በማብዛትና ጉዳቶችን በመቀነስ አፍራሽ ወገኖች መታገል የፓርቲው አመራርና አባላት ዋናው ተግባር መሆኑን በስብሰባዎቹ መወሰኑን ጠቁሟል።

ሀገራዊ ምክክር እንዲሳካ፣ የሽግግር ፍትሕና የቀድሞ ታጣቂዎች የተሐድሶ ፕሮግራሞች በተገቢው መንገድ ተከናውነው ለውጤት እንዲበቁ፣ ፓርቲው መንግሥትን እንደሚመራ ፓርቲ የሚጠበቅበትን እንደሚወጣ ገልጿል።

የሕዳሴ ግድቡንም በ2017 የበጀት ዓመት ለማጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑን ፓርቲው ጠቁሞ፤ ሜጋ ፕሮጀክቶች ያሉባቸውን ማነቆዎች በመፍታት እንዲጠናቀቁ እየተደረጉ መሆናቸውና በቀሪዎቹ ጊዜያትም የተጠናቀቁት እንዲመረቁ፣ ያልተፈቱ ችግሮች ያሉባቸውም ችግሮቻቸው ተፈትተው እንዲጠናቀቁ አቅጣጫ አስቀምጧል።

# «በኢትዮጵያና በሶማሌላንድ መካከል የተደረሰውን...

ከገጽ 1 የዞረ

አምባሳደር ሽብሩ ገልጸዋል።

ለማደግ ሲባል በሰጥቶ መቀበል መርሕ መሠረት በኢትዮጵያና በሶማሌላንድ መካከል የተደረሰውን የባሕር በር የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት እንቅስቃሴን ማወክ ለአጀንዳ 2063 ዝግጁ አለመሆንን ያመለክታል ሲሉም ገልጸዋል።

የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር የእርስ በርስ ንግድ እንዲኖር እየታሰበ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ በኢትዮጵያና በሶማሌላንድ መካከል ሁሉን አቀፍ የትብብርና የአጋርነት መግባቢያ ስምምነት ሰነድ መፈራረም ላይ እየተነሳ ያለው ጉዳይ የአፍሪካን አጀንዳ የሚያደናቅፍ ከመሆኑም ባሻገር የጥይት ድምፅ የማይሰማባትና የበለጸገች አፍሪካን ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት የሚያደናቅፍ ጭምር ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያን እድገት የማይፈልጉ ሀገሮችና ግለሰቦች የባሕር በር ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት ለማደናቀፍ መሞከር ብዙ አያስኬድም ያሉት አምባሰደር ሽብሩ፤ አብሮ ለማደግና ቀጣናውን የተረጋጋ ለማድረግ በመርሕ መሥራትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ አስፈላጊ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

አምባሳደር ሽብሩ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያንና በሶማሌላንድን መካከል የተጀመረው ስምምነት በፍጥነት መፈጸም ይኖርበታል። ሶማሌላንድ የራሷ ፓስፖርትና የመገበያያ ገንዘብ አላት። ዲሞክራዊያዊ ምርጫ ታካሂዳለች፤ ሌሎች ሀገሮች የሚሰጡትን ስምምነት የምትሰጥ በመሆኑ ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር የጀመረችው ስምምነት ሕጋዊ ነው።

እንደ አምባሳደር ሽብሩ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆና እንድትቀጥል የሚደረገው ጥረት የኢትዮጵያን የልማት እንቅስቃሴ ለመግታት መሞከር ነው። ኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት ብትሆን ከሶማሌላንድ ውጭ ለተቀሩት ጎረቤት ሀገራት ጥቅሙ የጎላ ነው። የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሁልጊዜም ቅድሚያ ለጎረቤት ሀገሮች ይሰጣል። ከሩቅ ቦታ መጥተው በኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገራት እያለሙ ኢትዮጵያ ከቅርብ ልታለማና ቀጣናውን በጋራ ለማሳደግ ስትንቀሳቀስ የሚነሳው ተቃውሞ በየትኛውም መመዘኛ ምክንያታዊ አይደለም።

የሶማሌላንድና የኢትዮጵያ ግንኙነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና የፀጥታ ሁኔታዎችን በቀጣናው ላይ ለማስተሳሰር የሚኖረው ሚና የጎላ መሆኑን አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ በብዙ ችግሮች ውስጥ ሆና በማደግ ላይ የምትገኝ ሀገር ናት ያሉት አምባሳደር ሽብሩ፤ ወደብ ብታገኝ ደግሞ በአፍሪካ ተወዳዳሪነቷ ይጨምራል። ይህን በመፍራት ኢትዮጵያ ለዘላለም ወደብ አልባ እንድሆን የሚሠሩ አካላት መኖራቸውን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ግድብ ስትገነባ ተቃውሞ፤ ወደብ ለማግኘት ንግግር ስትጀምርም ተቃውሞ መኖር አይቻልም። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ይህን በመገንዘብ ለብሔራዊ ጥቅም በጋራ መቆም ይኖርባቸዋል ብለዋል።

በወደብ ስምምነቱ ዙሪያ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ መገንዘብ ያለበት የዓለም አቀፍ ሕግ ወደብ የሌላቸው ሀገራት ወደብ ማግኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ መገንዘብ ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ እያደገ የሚሄድና ሰፊ መሆኑን ጭምር ነው። የወጭ ገቢ ምርቷን በተፋጠነ ሁኔታ ለማሳለጥ እንድትችል ድጋፍ ማድረግ አለባቸው። አንድ ሀገር ትልቅ የሚባለው በዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚና በመከላከያ መጠንከር ሲችል ነው፤ ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ የባሕር ኃይል ሊኖረን የግድ ነው ብለዋል አምባሳደሩ።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ራሷንና ቀጣናውን ከስጋት ለመከላከልና ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የባሕር ኃይል ያስፈልጋታል። ለዚህ ደግሞ ዋናው ጉዳይ የባሕር በር ማግኘት አለባት። የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ቅን ሆኖ ጉዳዩን በንጹሕ አዕምሮ መመልከት አለበት ብለዋል።

ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ አድጋ የራሷን ሕዝብ መመገብ ከቻለች ስደት ይቀንሳል ያሉት አምባሳደር ሽብሩ፤ ስምምነቱ ይዞት የሚመጣው ምንም አይነት ስጋት አይኖርም፤ ዘመኑ የጦርነት ባለመሆኑ በውይይት መፍታት ይቻላል ብለዋል። ከኢትዮጵያ በኩል ለሶማሊያ ወንድሞች ስለ ጉዳዩ ጠቃሚነት ማስገንዘብና ማስረዳት እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

# አቶ ደመቀ መኮንን ከብልጽግና...

ከገጽ 1 የዞረ

በምትካቸውም የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ የነበሩትን አቶ ተመስገን ጥሩነህ ምክትል ፕሬዚዳንት በማድረግ በአብላጫ ድምፅ መርጧል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አቶ ደመቀ መኮንን በ1980 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በባዮሎጂ ትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙ ሲሆን፣ ከዚያም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በግጭት አፈታት አጠናቀዋል።

በ1980ዎቹ መጀመሪያ ኢሕአዴግን የተቀላቀሉት አቶ ደመቀ፤ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የአማራ ክልል ምክር ቤት ተመራጭ ሆነው አገልግለዋል።

በ1997 የአማራ ክልላዊ መንግሥት ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሆነው የተመረጡ ሲሆን፤ በቀጣዩም ዓመት የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሆነው ተመርጠዋል።

አቶ ደመቀ መኮንን ኅዳር 2005 ዓ.ም የኢሕአዴግ ምክትል ሊቀመንበር ሆነው ከተመረጡበት ጊዜ ጀምሮ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ወደዚህ ኃላፊነት ከመምጣታቸው በፊትም የትምህርት ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል።

አቶ ደመቀ መኮንን በአዊ ዞን፣ ቻግኒ ከተማ፣ ለኢፌዲሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብልጽግናን ወክለው በመቅረብ አሸንፈዋል።

አቶ ደመቀ፤ በአሁኑ ወቅት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል፤ የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ።

ብልጽግና ፓርቲ አንደኛ ጉባኤውን ሲያከናውን አቶ ደመቀ መኮንንን ምክትል ፕሬዚዳንት አድርጎ መምረጡ የሚታወስ ነው።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

የቁም ገጾች




## «የባሕር በር ለማግኘት ወሳኙ ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ ነው»

- ኮሞዶር ጥላሁን መኮንን
የቀድሞ የባሕር ኃይል መኮንን

ገጽ 6



## ዛሬን በተስፋ - ነገን በስጋት

ገጽ 17



## ፅናትና ታታሪነት ለስኬት ያበቁት ሁሰገቡ ወጣት

ገጽ 20


ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አዲስ አበባ
The Vibrant Hub of Africa


## አፍሪቃዊቷ መልጎቅ

## አንባቢ ትውልድ ለሀገር ብልፅግና

ዳንኤል ዘነበ

አንጋፋው ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ የተማረው እስከ አራተኛ ክፍል ይሁን እንጂ እራሱን በንባብ አዳብሮ በሀገራችን አሉ ከሚባሉ ቁጥር አንድ ጋዜጠኛ፣ ጸሐፊያን እና አዋቂዎች መካከል አንዱ ሊባል የቻለው ምስጢሩ በማንበቡ እንደሆነ ይመሰከርለታል። በንባብ ራሳቸውን አንጋፋ ካስባሉ ሰዎች መካከል ሌላኛዋ ተጠቃሽ ደግሞ ሔለን ኬለር ናት። ሄለን ኬለር በብሬል የሚጻፉ ጹሑፎችን በማንበብ ራሷን እንደቀየረችም ይነገርላታል። እናም ሰዎች በንባብ ራሳቸው ካበለጸጉ እና ካሳደጉ መድረስ ካለባቸው ቦታዎች ለመድረስ ምንም ነገር እንደማያግዳቸው የእነዚህ ሰዎች ታሪክ ምስክር ነው ።

ጠንካራ የንባብ ባሕል መፍጠር ፋይዳው ከግለሰባዊነት የሚሻገርና ግዙፍ ሀገራዊ ፋይዳው ያለው ነው። በዓለማችን በሥልጣኔና በእድገታቸው በፊት አውራሪነት የሚጠቀሱ ሀገራት ለንባብ ልዩ ቦታ አላቸው። ለምሳሌ በንባብ ባሕሏ ተደናቂ የሆነችውን እንግሊዝን እንመልከት። እንግሊዞች በአንባቢነታቸው እጅግ የሚደነቁ ሲሆኑ፤ አንባቢነትን የባሕላቸው አካል ለማድረግ የቻሉም ናቸው። ይሄንን እመርታ ወይም ታላቅ ውጤት ያገኙት ግን ያለማሰለስ በብዙ ጥረትና ድካም እንጂ እንዲሁ የተዋሓዱት ብሎም አብሯቸው የተፈጠረ ልማድ ሆኖ አይደለም።

እንግሊዞች ሕዝባቸውን የዚህ ድንቅ ባሕል ባለቤት ሊያደርጉት የቻሉት ከኢንዱስትሪ (ከምንባብ) አብዮት በኋላ ወይም ሩቅ ባልሆነ ጊዜ በዚያው ወቅት ምቹ ፖሊሲ መመሪያ በመቅረጽ ለምሳሌ ወረቀትና መጽሐፍትን ከቀረጥ ነፃ በማድረግ አድካሚ የሆነ ታላቅ ዘመቻ በመክፈት ነበር። ለዚያ የተቀናጀና የተደራጀ ዘመቻ አንድ ጥሩ ግልጽና ሳቢ መሪ ቃል (slogan) ነበራቸው "እያነበብክ ያግኙህ" ወይም "እያነበብክ ተገኝ ("Let them find you while you are reading ወይም let you be found when you are reading") የሚል ነበር።

በዘመቻው ወቅት በምድረ እንግሊዝ ይህ መፈክር ያልተሰቀለበት ቦታና ግድግዳ የማስታወቂያ ሠሌዳ አልነበረም ማለት ይቻላል። በየአውቶቢሱ እና ሕዝብ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ በትልልቅ እና ባጌጡ ቃላት "እያነበብክ ተገኝ" የሚለው ጽሑፍ ይጻፍ ነበር። የብዙኃን መገናኛዎችም በልዩ ትኩረት አመርቂ ጥረት አድርገዋል። የዚህ ጠንካራ ጥበብ የተሞላበት ጥረት ውጤትም በሚያስደስት ሁኔታ ማንበብ ወይም አንባቢነት ባሕሉ የሆነን ማኅበረሰብ ማግኘት ሆነ። ለመሆኑ ይሄንን ያህል መድከም ያስፈለጋቸው ለምን ነበር ስንል መልሱ ቀላልና ግልጽ ነው። አንባቢ ሕዝብ ጠንካራና ባስተማማኝ ሁኔታ ያደገች የበለጸገች ሀገርን መፍጠር ስለሚችል ነው ።

በተጨማሪም አንባቢ ማኅበረሰብ ራሱንና አካባቢውን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ፤ አንባቢ ማኅበረሰብ ተወደደውም ሳይወደዱም ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሔ ሰጭና የመፍትሔ አካል ስለሆነ ንባብ ባሕል እንዲሆን ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል ። ጠንካራ የንባብ ባሕል መፍጠር ፋይዳው ከግለሰባዊነት የሚሻገርና ግዙፍ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው እንደመሆኑ፤ በኢትዮጵያ የማንበብ ባህል ለማሳደግም ከፍተኛ ሥራን መሥራት እንደሚገባ ጠቋሚ ይሆናል። ይህም ሁሉም በየደረጃው የትውልዱን የንባብ ባሕል ሊያሳድግ የሚችል ሥራ መሥራትን እንደሚጠይቅ አመላካች ነው።



8ኛው ዙር ከተማ አቀፍ የንባብ ባሕል ፌስቲቫል ከጥር 16 ጀምሮ ለ5 ተከታታይ ቀናት እየተካሄደ ይገኛል ፤

በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ ባሕል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የንባብ ባሕልን ዳግም ለማንሳት እና ነብስ እንዲዘራበት ለማድረግ አሁን ያለው ትውልድም አንባቢ፣ ንቁ እና ጠያቂ እንዲሁም ምክንያታዊ እንዲሆን ጭምር የተለዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ቢሮው ከሚሠራቸው ሥራዎች መካከልም የንባብ ባሕል ፌስቲቫሎች ማዘጋጀትና ማካሄድ ይገኝበታል።

ከሰሞኑ ቢሮው በሕትመት ዘርፍ ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ማተሚያ ቤቶች፣ ደራሲያን፣ በመጻሕፍት ሽያጭ ላይ የተሰማሩ አካላት እንዲሁም የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤት ቤተ-መጽሕፍቶች የሚሳተፉበት የንባብ ፌስቲቫል እያካሄደ ነው። 8ኛው ዙር ከተማ አቀፍ የንባብ ባሕል ፌስቲቫሉ ከጥር 16 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ለ5 ተከታታይ ቀናት በአዲስ አበባ ሙዚየም እየተካሄደ ይገኛል። ፌስቲቫሉ በታሪክ ረገድ ለንባብ ጉልህ አበርክቶ ሲያደርጉ የኖሩ የንባብ ዘርፍ ተቋማት ከአታሚ እና ከደራሲያን እንዲሁም ከአንባቢ ጋር ለማገናኘት መልካም አጋጣሚ ይፈጥራልም ተብሏል ።

በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ ባሕል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አስፋው ኩማ እንደተናገሩት፣ ቢሮው ላለፉት አምስት ዓመታት ከተማ አቀፍ የንባብ ባሕል ፌስቲቫል ሲያካሂድ ቆይቷል። በተካሄደው የንባብ ፌስቲቫልም በከተማው ለንባብ ባሕል ዕድገት የሚያግዙ መልዕክቶችን በማዘጋጀት ተደራሽ መደረጋቸውን አስታውሰዋል። አቶ አስፋው፣ ትውልዱ ጊዜውን አልባሌ ቦታ ከማሳለፍ እንዲቆጠብ እና የንባብ ባሕል እንዲያድግ የራሱን አስተዋፅዖ አበርክቷል የሚሉት ኃላፊው፤ በመዲናዋ የንባብ ባሕልን እንዲያንሰራራ አስተዋፅዖ ማድረጉን አስታውቀዋል ።

ዘንድሮም 8ኛው ዙር ከተማ አቀፍ የንባብ ባሕል ፌስቲቫል "አንባቢ ትውልድ ለሀገር ብልፅግና" በሚል መሪ ሀሳብ እየተካሄደ ነው ያሉት ኃላፊው፤ የንባብ ባህል ፌስቲቫሉ አዲሱ ትውልድ ከአልባሌ ቦታ እና ከደባል ሱስ ተላቆ ንባብን ባሕሉ በማድረግ የራሱን ድርሻ ለሃገር ለማበርከት እንደሆነ ነው። ዓላማውም ለከተማዋ ማኅበረሰብ የቤተ መጽሐፍትን አሠራርና አገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል አንባቢ፣ ተመራማሪ እና ችግር ፈቺ ትውልድ መፍጠር ነው ብለዋል።

ከጥር 16 እስከ ጀምሮ ለ5 ተከታታይ ቀናት በአዲስ አበባ ሙዚየም እየተካደ ባለው 8ኛው ዙር ከተማ አቀፍ የንባብ ባሕል ፌስቲቫል የከተማዋ ዕድሜ ጠገብ ማተሚያ ቤቶች፣ የመንግሥትና የግል ዩኒቨርሲቲ ቤተ-መጽሐፍት፣ መጽሐፍት ሻጮች፣ ደራሲያን፣ የተለያዩ ኤምባሲ ቤተ-መጽሐፍት እና ሌሎችም እየተሳተፉ ይገኛል ።

# ወቅታዊ

# «የባሕር በር ለማግኘት ወሳኙ ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ ነው»

*- ኮሞዶር ጥላሁን መኮንን*

*የቀድሞ የባሕር ኃይል መኮንን*



ፎቶ ፡- ገባቦ ገብሬ

አስቴር ኤልያስ

**ጊዜው 1950ዎቹ ውስጥ ነው፡፡ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ውስጥ የባሕር ኃይል ዩኒፎርም (የደንብ ልብስ) ለብሰው አልፎ አልፎ ብቅ የሚሉ መኮንኖችን ሲያዩ ከእነርሱ እንደ አንዱ የመሆን ፍላጎት ያድርባቸዋል፡፡ ሴላው ቀርቶ ሲኒማ ቤት ገብተው በሚያዩት ፊልም የባሕር ኃይል ዩኒፎርም የለበሰን መኮንን ማየት ለእርሳቸው ሕልማቸውን ለማሳካት የተቃረቡ ያህል ደስታ ይሰጣቸዋል፡፡ ብቻ መኮንኖቹን ሲመለከቷቸው ልባቸው የበለጠ ይነሳሳል፡፡ የዛሬው የዘመን እንግዳችን ኮሞዶር ጥላሁን መኮንን፡፡**

**አዲስ አበባ ተወልደው ያደጉት ኮሞዶር ጥላሁን፣ የባሕር ኃይል መኮንኖች አልፎ አልፎ በከተማዋ ውስጥ ለብሰው የሚያዩትን የደንብ ልብስ ‹‹ልክ እንደእነርሱ መልበስ ነበር!›› በሚል ብቻ ተመኝተው አልቀሩም፡፡ በደንብ ልብሱ ከመሳብ ባለፈ አባል መሆን ችለዋል፡፡**

**በተቋሙ በዕጩ መኮንንነት ተቀጥረው ሕልማቸውን እውን ያደረጉት ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት በ1954 ዓ.ም ነው፡፡ ትልቁን ተቋም ከተቀላቀሉ በኋላ በባሕር ኃይል ኮሌጅ ውስጥ ሦስት ዓመት ተምረው ዲፕሎማ አገኙ፡፡ እርሳቸው በተማሩበት ጊዜ በዲፕሎማ ለመመረቅ የሚወስደው ሦስት ዓመት ብቻ ነበር፡፡**

**በወቅቱ ኮሞዶር ጥላሁን፣ ከኮሌጅ የተመረቁት በምክትል መቶ አለቅነት ደረጃ ነው፡፡ ከዚያም ወደተለያዩ ሀገሮች በመጓዝ አጫጭር ሥልጠናዎችን ወስደዋል፡፡ ስልጠና ከወሰዱባቸው ሀገራት አንዱ እንግሊዝ ሀገር ነበር፣ እዚያም ስድስት ወር ያህል ተጨማሪ ኮርሶችን በመውሰድ ሙያቸውን ማዳበር ችለዋል፡፡**

**እንግዳችን፣ ከእንግሊዝ ሀገር ከተመለሱ በኋላ በተለያዩ የኢትዮጵያ መርከቦች ላይ ያገለገሉ ሲሆን፣ ለአብነትም የኢትዮጵያ ጦር መርከብ ላይ ሠርተዋል፡፡ ይህች መርከብ በወቅቱ በነበሩት በኢትዮጵያ ንጉሥ በአጼ ኃይለሥላሴ ስምም በኢትዮጵያ ስምም የምትጠራ እንደሆነች ያስታውሳሉ፡፡ በወቅቱ አጼ ኃይለሥላሴ ወደዚያች መርከብ አብዝተው ይመላለሱ ስለነበር በመርከቧ ውስጥ በልዩ ሁኔታ የሚያርፉበት ክፍል ተዘጋጅቶላቸውም ነበር፤ እርሳቸው ሲመጡ የሚያርፉባት ያች ክፍል በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀች መሆኗን ኮሞዶር ጥላሁን ያስረዳሉ፡፡**

**እንግዳችን መርከብ ላይ በምክትልና በዋና አዛዥነት ነው የሠሩት፡፡ ሚሳይል የሚጭኑ መርከቦች ላይም ሠርተዋል፡፡ ከመርከብ ወርደውም በተለያየ የባሕር ኃይል መደቦች ላይ አገልግለዋል፡፡ ለምሳሌ ምጽዋ ላይ የሰው ኃይል መምሪያ ኃላፊነት፣ በአሰብ ባሕር ኃይል የደቡብ ዕዝ ላይ ደግሞ በምክትል አዛዥነት አገልግለዋል፡፡**

**በተጨማሪም ባሕር ኃይል ውስጥ ዋናው ጠቅላይ መምሪያ የባሕር ኃይል የሰው ኃይል ዳይሬክተር ሆነውም ሠርተዋል፡፡ በጠቅላላ ከባሕር ኃይል በ1983 ዓ.ም እስከተሰናበቱበት ጊዜ ድረስ ለ25 ዓመታት ሀገራቸውን አገልግለዋል፡፡ ይህን ሁሉ ልምድ የቀመሩ የዘርፉ ሙያተኛ በመሆናቸው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ተቋሙ መልሶ እንዲደራጅ ባደረጉበት ወቅት የዛሬውን የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል እንዲያደራጁ ኃላፊነት ከተጣለባቸው ጉምቱ ባለሙያ አንዱ መሆን ችለዋል፡፡ ከእኚህ አንጋፋ የባሕር ኃይል መኮንን ጋር ነው ቆይታ ያደርግነው፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- ከእንግሊዝ መልስ ሲሠሩ የነበረው በአብዛኛው በአጼ ኃይለሥላሴ ስም በምትጠራው እና ንጉሡ ሲመጡ የሚያርፉባት ልዩ ክፍል በያዘች መርከብ ላይ ነው፤ መርከቧንም በመርከቧ ውስጥ ያለችዋንም ክፍል ልዩ የሚያደርገው ምን ይሆን?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** አብዛኛው የባሕር ኃይል አባላት ሥልጠና የሚሰለጥኑት በዚህች የጃንሆይ ተብላ በምትታወቀው መርከብ ላይ ነው:: ከዚህ የተነሳ ልዩ ያደርጋታል:: መርከቧ ወደ 250 ሰዎችን ትይዛለች:: በአብዛኛው ሰው የሚገኝባት ለሥልጠና ሲሆን ነው:: እኔ ራሴ እስከ ኃላፊነት ደረጃ የደረስኩት በዚያች መርከብ ሠልጥኜ ነው:: ከዚያ ሥልጠና በኋላ ነው በተለያዩ መርከቦች ላይ በኃላፊነት ተመድቤ ማገልገል የቻልኩት::

በወቅቱ ጃንሆይ (አጼ ኃይለሥላሴ) አብዝተው ወደዚያች መርከብ ይመጡ ስለነበር በመርከቧ ውስጥ እርሳቸው የሚያርፉባት ልዩ ክፍል ተዘጋጅቶላቸው ነበር:: ክፍሏን ልዩ የሚያደርጋት ደግሞ በወርቅ ቅብ የተዘጋጀች መሆኗ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የቀድሞው የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል በወቅቱ የነበረው ዋና ተልዕኮው ምን ነበር?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-**የኢትዮጵያን የባሕር ድንበር እና ጠቅላላ ክልሏን ከጠላት ጥቃት እና ከተለያዩ የውንብድና ተግባር መከላከልና መጠበቅ ነበር:: እንዲሁም ክልክል የሆኑትን እንደ ዓሣ ማሳገር ጭምር መከላከልም ነው:: በአጠቃላይ ባሕር ኃይሉ ያለበት ኃላፊነት ሕገ ወጥ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን መከላከል ነው::

ዋና ተግባሩ በሰላሙ ጊዜ ሥልጠና ማከናወን ነው:: የተለያዩ የሰው ኃይሎችን ብቁ ማድረግና ማደራጀትም ጭምር ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ባሕር ላይ የሚካሔዱትን ማንኛውንም ሕገ ወጥ ተግባራትን ሔዶ የመቆጣጠር እና አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት ተሰጥቶታል:: ባሕር ኃይሉ እስከ 1983 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ይህንን ተግባር ሲያከናውን የነበረ ነው::

የቀድሞው የኢትዮጵያ የባሕር ክልል በኪሎ ሜትር አንድ ሺ፣ በባሕር ማይልስ 540፣ የባሕር ግዛት ወደጎን Territorial water/ 12 የባሕር ማይል ነው:: የኢትዮጵያ የባሕር ኃይል ይቆጣጠር የነበረው ያንን ሁሉ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል በእርስዎ እይታ የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** በእርግጥ ባሕር ኃይሉን ትልቅ ባሕር ኃይል ነው ለማለት ይከብደኛል:: ባሕር ኃይልን ጠንካራ ባሕር ኃይል የሚያደርገው የሰው ኃይሉ ብቻ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚታጠቃቸው መሣሪያዎች ደግሞ ወሳኝ ናቸው:: በተለይ በጃንሆይ (አጼ ኃይለሥላሴ) ጊዜ የተወሰኑ የጦር መርከቦች እንዲሁም ጀልባዎች ነበሩን:: ከአሜሪካ ሀገርም በእርዳታ የተገኙ ነበሩ::

ከዚያም በደርግ ማለትም በወታደራዊ መንግሥት ጊዜ ጥሩ ትጥቅ ነበረ ማለት ይቻላል:: ምክንያቱም በወቅቱ ወታደራዊ መንግሥቱ ከሶቪየት ኅብረት ጋር በነበረው መግባባት የታጠቀው መሣሪያ ቀላል የሚባል አይደለምና ነው:: ምናልባት ባሕር ኃይሉ በቀይ ባሕር አካባቢ አሉ ከሚባሉት መካከል የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል ከግብጽ ቀጥሎ ተጠቃሽ ባሕር ኃይል ነው::

በአጠቃላይ ግን በአፍሪካ ውስጥ ደግሞ ምናልባት ቀዳሚው ደቡብ አፍሪካ ይሆን እንጂ ከእኛ የተሻለ አልነበረም:: ስለዚህ በጥቅሉ የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል በወቅቱ ጠንካራ የሆነ ነበር ማለት ይቻላል:: በውስጡ የነበረው የሰው ኃይልም የተማሩ ስለነበሩ ጥሩ እንቅስቃሴ የነበረው ነው:: በወቅቱ ሲሰጠው የነበረውን ተልዕኮም ሲያከናውን የነበረው በአግባቡ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ወታደራዊው መንግሥት ሥልጣኑን ከተነጠቀ ከ1983 ዓ.ም በኋላ የባሕር ኃይሉ የመዳከም ምስጢር ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** ባሕር ኃይል ሁለት ኃይል ነበረው:: አንዱ ጦር የታጠቀ መርከብ እና በሌላ በኩል የባሕር ኮማንዶ የሚባል ነው:: ይህ ኮማንዶ እግረኛ እንደሚባለው ዓይነት ሲሆን፣ ይህም የባሕር ኃይል ማሪን ኮማንዶ የሚባለው ነው፤ የሚንቀሳቀሰውም ባሕር ላይ ነው:: ባሕር ጠለቅም ኃይል ነበረው:: ባሕር ኃይል የሚባለው እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ነው::

ከዳህላክ እና ከዚያ አካባቢ እስከለቀቅንበት ጊዜ ድረስ ባሕሩን ሙሉ ለሙሉ ስንቆጣጠር ነበር:: የሻዕቢያ ኃይል ምጽዋን ከተቆጣጠረ በኋላ እንኳን ሙሉ በሙሉ እንደልቡ መርከብ ማስገባት አይችልም ነበር:: ምክንያቱም በወቅቱ ባሕሩን እንቆጣጠር የነበርነው እኛ ነን:: በዚያም ተሰጥቶን የነበረውን ግዳጅ በሙሉ አጠናቅቀናል:: የነበሩንን መርከቦች ጠላት አንዳቸውንም ሳይወስደው ያሸሸን ነን::

የነበረብን ድክመት ባሕሩን በኋላ ላይ መቆጣጠር አለመቻል ነው:: ለምሳሌ ጥቃት የደረሰብን ምጽዋ ላይ በባሕር በኩል ሳይሆን በመሬት የመጣብንን ኃይል እግረኛ ያልኩት ኮማንዶ የባሕር ወለድ አንድ ብርጌድ ኃይል ኖሮን ቢሆን ኖሮ በሚገባ እንከላከላለን፤ ምጽዋንም አናስነካም ነበር:: ይሁንና በወቅቱ መንግሥት አልፈቀደልንም:: እኛ ራሳችን ካለን ስጋት የተነሳ ወደ አንድ ሻለቃ የሚሆን በራሳችን ማለትም በ«ሞተ ከዳ» በሚባል በጀት ሁሉ ነበር ስንገለገል የነበረው:: በመሬት በኩል መጥተው ምጽዋን ሊቆጣጠሩ የቻሉት ለዚህ ነው::

የማሪን ኮማንዶ ሙሉ በሙሉ ተጠናክሮ ባለማግኘታችንም ጭምር ነው:: በወቅቱ ሻዕቢያ ሊያጠቃ የመጣው ሁለት ጊዜ ነው:: የመጀመሪያው በ1970 ዓ.ም ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ምጽዋን የተቆጣጠረበት በ1982 ዓ.ም ነው:: ምርኮኞቻችን ጀልባዎቻችን ናቸው ማለት ይቻላል:: ሲዋጉ የነበረው እንደ እግረኛ ሆነው ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- ኤርትራ ነፃ ሀገር መሆኗ ከተረጋገጠ በኋላ ኢትዮጵያ ወደብ ማጣቷ ይታወቃልና ያጣንበትን መንገድ የሚገልጹት እንዴት ነው?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** ሻዕቢያ ምጽዋን በ1982 ዓ.ም መጥቶ በመቆጣጠሩ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ አሰብም እንዲሁ ነው ማለት ይቻላል:: እኛ ይዘን የነበረው ሁለት ዕዝ ነው:: አንደኛው የሰሜን ዕዝ ሲሆን፣ ያለው ምጽዋ ነው፤ ደቡብ ዕዝ ደግሞ ያለው አሰብ ነው:: እና የደቡብ ባሕር ኃይሎች አሰብ አካባቢ ያለው እስከመጨረሻው ድረስ በእኛ ቁጥጥር ስር ነበር:: ይህ ማለት እስከ 1986 ዓ.ም መሆኑ ነው:: ለቀን የወጣነው ጦሩ ሲለቅ ብቻችንን ምን እናደርጋለን በሚል ነው እንጂ አሰብ ሙሉ በሙሉ በእኛ ቁጥጥር ስር ነበር:: ትንሽ ሙከራ በጀልባ ሻዕቢያዎች ሞክረው ነበር:: ይሁን እንጂ የዚያን ያህል ኃይል አልነበራቸውም:: እኛ እስከ መጨረሻው እዚያ ነበርን:: እናም ያጣነው ምጽዋን ሙሉ በሙሉ ነው እንጂ አሰብ የእኛው ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ አሰብን የለቀቀችበት መንገድ አግባብነት አለው ብለው ያስባሉ? አሰብ በመታጣቱ የሚሰማዎት ስሜት ምንድን ነው?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** አሰብን ያጣነው በፖለቲካ ውሳኔ እንጂ በኃይል አይደለም:: አሰብን በኃይል የተቆጣጠረ ማንም የለም:: ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ ባሕር ኃይልን አፈረሰ:: ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ አሰብን አስረከበ:: ኤርትራ ምጽዋን ያገኘችው ነፃ በመውጣቷ ነው፤ ይህ ደግሞ ልክ መሆኑን ሁላችንም የምንቀበለው ነው:: አሰብ ግን ከእጃችን ሊወጣ የቻለው እንዳልኩሽ በፖለቲካ ውሳኔ ነው::

አሰብ በመታጣቱ ሁሉንም የሚያስቆጭ ጉዳይ ነው:: አንድ ሀገር መንቀሳቀሻ የሚሆነውን የባሕር በር ማጣት የለበትም የሚል እምነት አለኝ:: እኛ ይህን በማጣታችን የሚሰማን ስሜት አለ:: ምክንያቱም አንድ ሀገር የባሕር

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# «የባሕር በር ለማግኘት ወሳኙ ዲፕሎማሲያዊ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ



በር የለውም ማለት የመታሰር ያህል የሚቆጠር ነው:: መውጫ መግቢያ በሌለው ቦታ እንደመቀመጥም የሚታይ ነው:: በዋናነት የሚያስፈልገን በነፃ መንቀሳቀስ የሚያስችለንን የባሕር በር ማግኘት ነው እንጂ ወደብንማ በተለያየ መንገድ እናገኛለን:: በአሁኑ ወቅትም ምንም እንኳ የራሳችን ባይሆንም በመጠቀም ላይ እንገኛለን::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ዘመናዊ የባሕር ኃይልን ቀድማ ያቋቋመች ሀገር መሆኗ ይነገራል:: ይሁንና በኢህአዴግ ዘመን መፍረሱ ይታወቃል፤ በአሁኑ ወቅት ይህ የለውጡ መንግሥት ደግሞ ተቋሙን መልሶ እያደራጀው ነውና ይህን እንዴት ያዩታል?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** በአሁኑ ወቅት እየተደራጀ ያለውን የባሕር ኃይል እኔም በሥራው ውስጥ በአማካሪነት ሠርቻለሁ:: ከቀድሞ የባሕር ኃይል አባላት መካከል አራት ያህላችን በማማከሩ ሥራ ተሳትፈናል:: በተለይ አራታችን ባደረግነው የማማከር ሥራ ባሕር ኃይል ተመልሶ እንዲቋቋም አድርገናል ማለት ይቻላል:: የሚቋቋመውም ልክ እንደ ድሮ እንዲሆን ነው:: እኛ በዚያ መልኩ አማክረናል፤ ተግባራዊ የማድረግ ድርሻ ደግሞ የመንግሥት ነው:: በጥቅሉ ለማለት የምፈልገው የባሕር በር ወሳኝ መሆኑን ነው::

ከዚህ ጋር ተያይዞ አሰብ ቢገኝ ጥሩ ነው:: ያንን የማግኘቱ ጉዳይ የመንግሥት ቁርጠኝነት ይሆናል ብዬ አምናለሁ:: ይህ የሚሆነው ግን በተለያየ መንገድ ሲሆን፣ ለምሳሌ ዋናው ጉዳይ ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ መሔድ የበለጠ ተመራጭ ነው:: እንዲያ ሲሆን ባሕር ኃይልም ይኖረዋል:: ሀገሪቱን በባሕር ኃይል ብቻ ሳይሆን የንግድ መርከብ እንቅስቃሴና የገቢ ወጪ ምርቱንም ሁሉ በራስ የመቆጣጠር ደረጃ ላይ የሚያደርስ ይሆናል:: ስለዚህ በሌሎች ላይ ጥገኛ ሆኖ መኖር ያበቃና በራስ ለመንቀሳቀስ ያስችላል::

**አዲስ ዘመን፡- ለባሕር ኃይል መደራጀት የባሕር በር ወሳኝና እሱን ለማግኘት ደግሞ በዲፕሎማሲ መንገድ መንቀሳቀስ መልካም እንደሆነ ተናግረዋል፤ ከዚህ ባሻገር የባሕር በርን መልሶ ማግኘት የሚያስችሉ ሌሎች አማራጮች ይኖሩ ይሆን?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** በእርግጥ ባሕሩ ሳይኖር ባሕር ኃይሉ መኖር አይችልም:: እንዳልኩት ነው፤ የባሕር በርን ለማግኘት ዋናውና ወሳኙ ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ ነው:: ጉርብትና እስካለ ድረስ እና ከጎረቤት ጋር አብሮ በሰላም መኖር እስካልተቻለ ድረስ ችግር መምጣቱ አይቀሬ ነው:: ስለዚህ ከጎረቤት ጋር ሊኖረን የሚችለው ግንኙነት ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ ነው ብዬ አምናለሁ:: ከዚህ የተነሳም ፍላጎታችን በሰላማዊ መንገድ ሊመለስ የሚችል ነው የሚል እምነት አለኝ::

ኢትዮጵያ በኢህአዴግ ጊዜ አሰብን ለኤርትራ መስጠቷን ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው:: ይህ ውሳኔ የተደረሰበት በወቅቱ በነበረው መንግሥት አማካይነት ነው:: በዚያን ወቅት ጉዳዩ ሲከሰት የተቃወመ አካል ያለ አይመስለኝም:: በወቅቱ እኛን አሰናብተውናል፤ ነገር ግን በወቅቱ አሰብ ለኤርትራ ሲሰጥ ሕዝቡ መቃወም ነበረበት:: ይሁንና ተቃውሞ ያሰማ አካል የለም:: ያንን ያላደረገበት ምክንያት ቢጠየቅ ሁሉም የተለያየ ምክንያት ይኖረዋል::

አሁንም የባሕር በርን ለማግኘት በሚደረገው እንቅስቃሴ ቀዳሚ ሊሆን የሚገባው ዲፕሎማሲ ነው:: ወደብ የማግኘት ጉዳይ ብዙም ከባድ አይደለም:: በዙሪያችን ጂቡቲን ጨምሮ ብዙዎች አሉ:: አሁንም ቢሆን እየተጠቀምንበት እንገኛለን::

**አዲስ ዘመን፡-ኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ተስፋ ይኖራት ይሆን? በዚህ በኩል የዓለም አቀፍ ሕጉስ ምን ይላል?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** ይህ እንኳ ከበድ ያለ ጥያቄ ነው:: በዚህ ጉዳይ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉት ፖለቲከኞች ናቸው ብዬ አስባለሁ:: ከባሕር ጋር በተያያዘ እና ከባሕር ሕግ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ሁኔታ በሌላ ሀገር ገጥሞ የሚያውቅ አይመስለኝም:: ምክንያቱም የራስን መሬት ቆርጦ ለሌላ ሀገር የሰጠ ሀገር ካለ ብዬ መረጃ ለማግኘት ሞክሬ ነበር፤ ግን አላገኘሁም:: በእርግጥ ምናልባት ሊኖር ይችላል:: እኔ ግን ስላላየሁ ነው፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያ እንዳላት የሕዝብ ብዛት ታይቶ የባሕር በር ሊኖራት ይገባል:: እንደሚታወቀው በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት ሀገር ናት:: ይህ ሁሉ ሕዝብ ደግሞ ሊኖረው የሚገባ ነገር አለ:: ከዚህ ውስጥ አንዱ የባሕር በር ሲሆን፣ ሁኔታዎች ደግሞ እንዲኖሩት ያስገድዳል:: በተለይ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትንም ሆነ ከሀገር የሚወጡትን ጉዳዮች ለማሳለጥ የባሕር በር ያስፈልገዋል::

ከፍ ያለ ሕዝብ እንቅስቃሴውም የዚያኑ ያህል ከፍ ይላል:: ስለዚህ ለዚህ ሕዝብ መግቢያ እና መውጫ ያስፈልገዋል:: ከዚህ አኳያ ምናልባት በዓለም አቀፍ ደረጃ ነገሮቹ ሊታዩ ይገባ ይሆናል:: ጉዳዩን እስከ ተባበሩት መንግሥታት ድረስ በመውሰድ ለስኬታማነቱ መሥራት ይገባል:: ከዚያ አስቀድሞ ግን በኤርትራ እና በኢትዮጵያ መካከል የዲፕሎማሲ አካሄድ መፈጠር አለበት:: ዲፕሎማሲውን ማጠናከር ነው::

ጉዳዩን በሰጥቶ መቀበል መርህ ማስኬድ ይቻላል:: ይህንንም ሁኔታ ማየት አስፈላጊ ነው:: በዚህ በዲፕሎማሲና በሰጥቶ መቀበል መርህ የምንሔድ ከሆነ የባሕር በር ይገኛል የሚል ተስፋ አለኝ:: ያለን አማራጭ ይህ ሲሆን፣ ከዚህ ውጪ የሆነው ሌላ አማራጭ አዋጭ ነው ብዬ አላስብም:: ውጤት ያስገኝልናል ብዬም አልገምትም::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የባሕር በሯንም ሆነ በወቅቱ ጠንካራ የነበረውን የባሕር ኃይሏን በማጣቷ ምን ይሰማዎታል?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** የባሕር ኃይላችንን ማጣታችን ሁላችንንም ቢሆን በጣም የሚያሳምም ነው:: የባሕር ኃይላችንን ብቻ ሳይሆን የባሕር በራችንንም ማጣት የሚያስቆጭ ነው:: ድሮም ቢሆን በአክሱም ዘመነ መንግሥት ጊዜ አጣን፤ በመጨረሻም በጃንሆይ (አጼ ኃይለሥላሴ) ጥረት ደግሞ መልሰን ባሕራችንን ማግኘት ቻልን:: አሁን ደግሞ መልሰን አጥተነዋል::

የባሕር በሩን ምናልባት የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር መልሰን እንደምናገኘው ተስፋ አደርጋለሁ:: ይህ የሚሆነው ግን ጉርብትናን እስካሳመርነው ድረስ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በሥራ ላይ እያሉ ያጋጠመዎ ፈተና ካለ? አሲያም ደግሞ በሥራዎ ደስ የተሰኙበት ጊዜ ካሳለፉ ቢገልጹልን?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** አንዴ በ1960 ዓ.ም በጃንሆይ (አጼ ኃይለሥላሴ) አንድ ተልዕኮ ተሰጥቶኝ ነበር:: ይኸውም የዓባይ ወንዝን የማሰስ ተልዕኮ ነበር:: አሰሳውም የሚደረገው ዓባይን በማቋረጥ ነው:: እርሳቸው ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ተነጋግረው የተወሰነ ኃይል መጥቶ እንዲያይላቸው ጠይቀው ነበር:: የመጡትም የዘርፉ እውቀት ያላቸው ወታደሮች ናቸው:: እኔም ከዚህ ኃይል ጋር ተሳትፌ ነበር:: በወቅቱ የዓባይን ወንዝ አቋርጦ መመለሱ ትልቅ ጀብድ ነበር:: ዓባይን በጀልባ ከጫፍ እስከ ጫፍ በመሔድ ማቋረጡ በጣም ከባድ ጉዞ ነበር:: ልክ እንደ ማንኛውም ወንዝ ወይም ባሕር አይደለም::፡ ጉዞው በጣም ከባድ የነበረ ነው::

ከዚያ በፊት በርካታ የውጭ ሀገር ሰዎች ሞክረውታል:: ይሁንና በወቅቱ ሊሳካላቸው አልቻለም:: ለእኛ ግን ተሳክቶልናል:: አንደኛ ሳይንሳዊ ጥናትም ተካሂዷል:: በወቅቱ አራት የሞተር ጀልባዎች ነበሩን:: በዚያ ላይ ወደ 30 የምንጠጋ ሰዎች ነን ስናስስበት የነበረው:: አሰሳውንም ጀምረን የነበረው ደጀን አካባቢ ከሚገኘው ድልድይ ነው:: መቼም የዓባይ ወንዝ አፈሳሰስ በራሱ ተዓምራዊ የሆነ ነው:: በሁላችንም ዘንድ የሚታወቀው ውሃ መፍሰስ ያለበት ከላይ ወደታች ነው:: የዓባይ ወንዝ ግን በተቃራኒው ሁሉ የሚወርድ ነው::

ዓባይን በምናስስበት ጊዜ የእንግሊዞች የምድር ጦር አባላትና የተወሰኑ ደግሞ ሲቪሎች ነበሩ:: በተጨማሪም ከአየር ኃይል የተካተቱ አሉ:: የምድር ኃይልም ነበር:: እነሱ እኛ በምንንቀሳቀስበት ወቅት ሬሽን የሚያቀርቡልን ነበሩ:: አብዛኛው ጊዜ ግን ሬሽናችን የሚቀርብልን በአየር ላይ ሲሆን፣ ወርደው የሚያቀብሉንም በፓራሹት ነው:: ወንዙን ለማሰስ የወሰደብን ጊዜ ሁለት ወር ያህል ነው:: ይህ በሕይወቴ የማልረሳው ጊዜ ነው::

ከኢትዮጵያ ከእኔ በተጨማሪ የመከላከያ ሰዎች እንዲሳተፉ ተጋብዘው ነበር:: ይሁንና ከእኔ በስተቀር ሌሎቹ አልተላኩም:: ከሲቪል ደግሞ የማዕድን ሰዎች ተጋብዘው ነበር:: እነርሱም አልመጡም፤ ቢመጡ ኖሮ ከፍተኛ የማዕድን ክምችት እንዳለ የሚነገርለትን ቦታ መለየት ይችሉ ነበር ባይ ነኝ:: በእነርሱ ፈንታ የመጡት እንግሊዞች በተወሰነ መልኩ ማዕድንም ያለበትን ለማጥናት ሞክረዋል:: በጥቅሉ ግን ከተለያዩ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት የተጋበዙ ቢኖሩም መምጣት ግን የሆነላቸው አልመሰለኝም:: በመጨረሻም እኔን ጨምሮ አምስት ያህል ኢትዮጵያውያን ለጉዞው ዝግጁ ነበርን:: ይሁንና በውሃው ላይ ለመሄድ የበቃሁት ከኢትዮጵያውያኑ በኩል እኔ ብቻ ነኝ፡፡ የወንዙን 75 በመቶ የሸፈንኩትም እኔ ብቻዬን ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት እርስዎ ሥራ እየሠሩ ነው? በምን ሁኔታ ላይ ነው የሚገኙት?**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** ከስደት ከተመለስኩ ቆየት ብያለሁ:: ማለትም ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁት በ1991 ዓ.ም ነው:: የነበርኩትም ጅቡቲ ነው:: በኢትዮጵያ በባሕር ኃይሉ የወሰድነው ትምህርትና ሥልጠናው መልካም የሚባል በመሆኑ በእዛም ሆኜ የባሕር ኃይል ውስጥ ለመሥራት በቅቻለሁ:: በመሆኑም ለተወሰኑ ዓመታት በሱማሌ፣ ገልፍ አካባቢ፣ ዱባይና ኢራንም በካፒቴንነት ተንቀሳቅሻለሁ:: ጅቡቲ ብቻ ወደ ስምንት ዓመት ያህል ቆይቻለሁ:: ከዚህ ውስጥ ሁለት ዓመት ያህል ባሕር ላይ ስሠራ ነው የቆየሁት::

በአሁኑ ወቅት እየሠራሁ ያለሁት በቻይና ኮሙኒኬሽን ኮንስትራክሽን ኩባንያ ውስጥ ነው:: በዚያም የኮንስትራክሽን ሥራ ነው የምሠራው::

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን መረጃ ከልብ አመሰግናለሁ::**

**ኮሞዶር ጥላሁን፡-** እግዚአብሔር ይስጥልኝ፤ እኔም አመሰግናለሁ::

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የነባር ፕሮጀክቶች ግንባታን የማጠናቀቅና ዲዛይን የማስጠበቅ ሥራዎች

በኃይሉ አበራ

ሀገሪቱ ግንባታ በስፋት የሚካሄድበት በመባል ስትጠቀስ ቆይታለች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የግንባታው ዘርፍ መቀዛቀዝ ቢታይበትም፣ በአሥር አመቱ መሪ አቅድ ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች። በዚህ እቅድ በመንግሥት ብቻ በርካታ የመንገድ፣ የባቡር፣ የመኖሪያ ቤቶች፣ የኃይል ማመንጫ፣ ወዘተ ፕሮጀክቶች ለመገንባት ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል።

የግንባታው ዘርፍ ባለፉት ዓመታት መቀዛቀዝ ውስጥ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ዓለምን ጭምር ቀውስ ውስጥ የከተተው ኮቪድ 19፣ የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነትና ያንን ተከትሎ በሀገሪቱ ላይ የተደረገው ጫና፣ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የታዩ ግጭቶች፣ የግንባታ ግብአት እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ዘርፉ እንዲቀዛዝ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳሉ፤ ይህን ተከትሎም በርካታ ፕሮጀክቶች ተጓትተው ይታያሉ፤ መንግሥት ትኩረቱን የተጓተቱ ፕሮጀክቶችን መጨረሻ ላይ ማድረጉን ተከትሎ አዳዲስ ፕሮጀክቶች መጀመር ላይ ብዙም አልተሰራም።

በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም በግሉ ዘርፍ እየተካሄደ ያለው ግንባታ እንዳለ ሆኖ በመንግሥት በኩል የህዝቡን መሰረታዊ ችግር የሚፈቱ፣ በቀጣይ የልማት አቅም መሆን የሚችሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ይገኛሉ። ለእዚህም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት በከተማዋም በመላ ሀገሪቱም እየተካሄዱ የሚገኙ ግዙፍ ፕሮጀክቶች በአብነት ይጠቀሳሉ።

ሀገሪቱ ግንባታ የሚጓተትባት ብቻም ሳትሆን ግንባታዎች የዲዛይን ችግር የሚታይባቸው መሆናቸውም ይታወቃል። ግንባታዎች ከጥራት፣ ከዲዛይን፣ ከጊዜ አኳያም ሰፊ ክፍተት እንደሚታይባቸው ይገለጻል። አካል ጉዳተኞችንና አካባቢን ታሳቢ ያላደረጉ ህንጻዎች በስፋት መታየታቸውም ይህንኑ ያመለክታል።

በመዲናችን አዲስ አበባ እና በክልል የተገነቡና እየተገነቡ የሚገኙ አንዳንድ ህንፃዎችን ስንመለከት አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያላደረጉ ሆነው ይታያሉ፤ ከእነዚህ ግንባታዎች አንዳንዶቹ ከጅምሩም የዲዛይን ክፍተት እንዳለባቸው ይታወቃል። አንዳንዶቹ የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ ግንባታዎች ቢያደርጉም በቅጡ ታስቦበት የተከናወነ ሥራ ግን አይስተዋልባቸውም። ለ45 ዲግሪ የቀረቡና ከባድ ቁልቁለት ያለባቸው የአካል ጉዳተኛ መወጣጫዎች በአንዳንድ ህንጻዎች ይታያሉ፤ ይህ ብቻም አይደለም፤ መወጣጫዎቹ አንሸራታች ሆነው የተገነቡበት ሁኔታም ያጋጥማል። ከዚህም ግንባታዎቹ አካል ጉዳተኞቹን ሊጠቅሙ ቀርቶ ለበለጠ አደጋ የሚያጋለጡ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌላቸው ህንጻዎች እንዳሉም ይገለጻል።

የግንባታዎች በታቀደላቸው ጊዜ አለመጠናቀቅ የከተማዋ ብቻም ሳይሆን የሀገሪቱ መሰረታዊ ችግር ሆኖ ቆይቷል። በሀገራችን ከለውጡ በፊት ከነበረው የፕሮጀክቶች መጓተት በተጨማሪ ባለፉት አመታት በተከሰተው ጦርነት እና የፀጥታ ችግር የተነሳም ግንባታቸው የተጓተተ ፕሮጀክቶች ጥቂት የሚባሉ ስለ አለመሆናቸው በግልጽ የሚታይ ሀቅ ነው፤ ችግሩ ስለመኖሩ የዘርፉ ባለሙያዎችና ኃላፊዎችም ያረጋግጣሉ። ይህን ተከትሎም የግንባታ ዲዛይን እና የዋጋ ማስተካከያዎችን ማድረግ በእጅጉ የተለመደ ሆኖ ቆይቷል፡፡

በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የኮንስትራክሽን ግብአቶች ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ በረከት ተዘራ እንደሚናገሩት፤ ከ2013 ዓ-ም ጀምሮ አገሪቱ ከነበረችበት ጦርነት፣ ከሰላምና ጸጥታ ችግሮች እና ከሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የግንባታ ሥራዎችን በሚፈለገው ፍጥነት እና በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ ያለመፈጸም ችግሮች ታይተዋል። ግንባታዎችን ለማጠናቀቅ ያለው በጀት ውስን መሆንም ሌላው ተግዳሮት ሆኗል።

ከግብርናና ቀጥሎ ብዙውን የሰው ኃይል የሚያቅፈው የግንባታው ዘርፉ መሆኑን አቶ በረከት ጠቅሰው፣ ዘርፉ ብዙ የስራ እድል መፍጠር የሚችለው ፕሮጀክቶች ሲንቀሳቀሱ መሆኑን ይናገራሉ። አሁን በፕሮጀክቶች እንቅስቃሴ ላይ መቀዛቀዝ መታየቱን ተከትሎ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ብዙም እንደማይጀመሩም ይገልጻሉ። ነባሮቹን ባለው በጀት ቅድሚያ በመስጠት ለማጠናቀቅ ግን ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸውን ይጠቁማሉ።

በተለይ በመንግሥት በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ከዚህ ቀደም ይመደብላቸው ከነበረው በ2016 በጀት ዓመት ቢያንስ ከ50 እስከ 75 በመቶ ያላቸውን መጠን በመቀነስ እየተጠቀሙ እንደሚገኙም መሪ ሥራ አስፈጻሚው አስታውቀዋል። የበጀት እጥረቱ ፕሮጀክቶች በሚፈለገው መንገድ እንዳይንቀሳቀሱ ካደረገ ደግሞ በዘርፉ የተሰማራው የሰው ኃይል ቁጥር በዚያው ያህል የሚቀንስ መሆኑንም ይገልፃሉ።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የታየውን ይህን ተግዳሮት በምን መልኩ መሻገር እንደሚገባም በመንግስት በኩል እየታሰበበት መሆኑንም ጠቅሰው፣ በቀጣይ ሀገርን ከማረጋጋት አኳያ በሚኖረው እንቅስቃሴ ጥሩ ለውጦች እንንደሚኖሩም ነው ያመለከቱት። በሙሉ አቅም መስራት ውስጥ ባይገባም፣ ከነባሮቹ ፕሮጀክቶች ቀድመው ማለቅ የሚገባቸውን በማየት እና ቅደም ተከተላቸውን በመጠበቅ የማንቀሳቀስ ስራዎችን ለመስራት የሚፈለገውን የሰው ኃይል በማሰማራት እየተሰራ ነው ይላሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ነባር ፕሮጀክቶች ከሚባሉት መካከል በዋናነት በመደበኛ የመንግስት በጀት የሚገነቡ የዩኒቨርሲቲዎች፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ፕሮጀክቶች ይገኙበታል። በአዲስ አበባና በሸገር ሲቲም በጤና ሚኒስቴር የሚገነቡ ፕሮጀክቶች፣ በአለርት ሆስፒታል ግቢ የሚገነቡ ፕሮጀክቶች፣ የኢትዮጵያ ሚትሮሎጂ ግንባታዎች ነባር ተብለው የተያዙ ናቸው። በክልሎች ደግሞ በዩኒቨርሲቲ፣ በተለያዩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚካሄዱ ግንባታዎችም አሉ።

መንግሥት የእነዚህን ፕሮጀክቶች አጠቃላይ በጀት መቶ በመቶ እንዳላሟላላቸው መሪ ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰው፤ ከሚፈለገው አገልግሎት አኳያ የትኛው መቅደም አለበት በሚል መንግሥት ቅድሚያ ሰጥቶ በጀታቸውንም መቶ በመቶ ባሟላላቸው ፕሮጀክቶች መጠን ግንባታቸው እየተከናወነ መሆኑን ያስረዳሉ።

በተለይ አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ተማሪን ከመቀበልም አኳያ በተወሰነ መልኩ ለተማሪዎች ማደሪያ፣ ለመማር ማስተማር ሂደቱ አጋዥ የሆነ ግንባታ በግቢው የሚገኝ ከሆነ የትኛው ቅድሚያ ይሰጠዋል በሚል እየተለየ የማጠናቀቅ ስራው እንደሚካሄድ ገልጸዋል። ቅድሚያ ከሚሰጣቸውም መካከል የመኖሪያ፣ የምግብ ማብሰያ በሚል ቅደም ተከተል ወጥቶላቸው እንዲገነቡ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።



አቶ በረከት እንዳብራሩት፤ በተመሳሳይ መልኩም ከዋጋ ግሽበቱ ጋር በተገናኘ መንግስት ለሁሉም መንግስታዊ ፕሮጀክቶች ባስተላለፈው የዋጋ ማስተካከያ መሰረት እየተሰራ አለመሆኑን ይገልጻሉ። ይሁንና ከውጭ የሚገቡ ግብአቶች ከኤልሲ ጋር በተገናኘ በሚቀመጥላቸው ስኬጁል (ፕሮግራም) መሰረት እየሄዱ አለመሆናቸውንም ተናግረዋል።

ይሄንንም ባለሥልጣኑ ቀደም ሲል ባደረገው ቁጥጥር ባገኘው ግኝት መሰረት ከሚወስዱት የተጨማሪ ክፍያ አኳያ መሰራት ያለባቸው ስራዎች እንዲሰሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገርም በአብዛኛው የግንባታ ሥራ እየተጠናቀቀ መሆኑን መሪ ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰው፣ ውስን የማጠናቀቂያ ቀሪ ስራዎች እንዳሉም ይጠቁማሉ።

ቀደም ሲል በተካሄደው የተካሄደውን ቁጥጥር ተከትሎ በተከናወኑ ተግባሮች መሰረትም ከውጭ መግባት የነበረባቸው እቃዎች ሙሉ በሙሉ መግባታቸውንና መከማቸታቸውን ገልጸው፤ በማጠናቀቂያ /የፊኒሺንግ/ እቃዎች ላይ ጤና ሚኒስቴር ካለው የበጀት ጉድለት አኳያ የዋጋ ማስተካከያ እየሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

እነዚህ ሁኔታዎችን ማስማማት ከተቻለም ፕሮጀክቶቹ በ2016 መጨረሻ ላይ በተቀመጠላቸው ፕሮግራም መሰረት የሚያልቁበት እድል ከፍተኛ መሆኑንም መሪ ሥራ አስፈጻሚ አስታውቀዋል። ይህ ባይሳካ እንኳን በ2017 መጀመሪያ እና ሩብ ዓመት የማጠናቀቅ እድሉ ከፍ ያለ መሆኑንም ይገልፃሉ። ከፕሮጀክቱ ውስበስብነትና ሆስፒታል ከመሆኑም አኳያ ጥንቃቄ እንደሚፈልግ ጠቅሰው፣ የፕሮጀክቱ ግንባታ ሥራ ጥሩ ደረጃ ላይ መድረሱንም ነው ያመለከቱት።

አቶ በረከት በግንባታ ስራዎች ቁጥጥር ላይም በዋናነት በግንባታዎቹ ጥራት ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው፣ በቀጣይነት ደግሞ ዋጋ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሰራም አስታውቀዋል። ሶስተኛው ጊዜ፣ አራተኛው ደግሞ የደህንነት እና ከአካባቢ ጋር ያለው ተስማሚነት በመመርኮዝ የቁጥጥር ስራው እንደሚካሄድ አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይኖች እነዚህን መስፈርቶች ከግንዛቤ ውስጥ ያካተቱ ስለመሆናቸው በቀዳሚነት ይታያል። እነዚህን ያገናዘቡ ከሆነ ወደ መሬት ወርደው መስፈርቶቹን ባገናዘበ መልኩ እንዲገነቡ የማድረግ ተግባር እና ኃላፊነቱ በ524 ደንብ ቀጥር ጸድቆ ለባለስልጣኑ ተሰጥቷል። በመሆኑም ባለስልጣኑ ይሄንን ተግባር የመወጣት ግዴታ አለበት። ግንባታዎች በአጠቃላይ ጥራትን ብቻ ሳይሆን ጊዜን፣ ዋጋን፣ ለአካባቢና ሰራተኛ ምቹ ሁኔታን መፍጠራቸውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ባለስልጣኑ እየሰራ ይገኛል።

በፌዴራል መንግሥት በጀት ተደግፈው የሚሰሩ ፕሮጀክቶች በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን በኩል ማለፍ እንዳለባቸው ለሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በ2013 ከገንዘብ ሚኒስቴር ባተላለፈላቸው የውስጥ አሰራር (ሰርኩላር) መሰረት አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች ወደ ተቋሙ በመምጣት ዲዛይኖቻቸውን እያፀደቁ ወደ ተግባር እንዲገቡ ይደረጋል።

ዲዛይኑም ጥራትን፣ ዋጋን፣ ጊዜን እና የአካባቢና የማህበረሰብ የሥራ ቦታ ደህንነት ባረጋገጠ መልኩ እንዲዘጋጅ ተደርጎ እየተሰራ ነው ብለዋል። ከጥራት አኳያ የሚፈጠሩ ግድፈቶችም ወዲያውኑ እርምት እንዲደረግባቸው እንደሚደረግ ጠቅሰው፣ በቀጣይም ለአካባቢውም ለማህበረሰቡም ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ መሆናቸው እንደሚታይም ተናግረዋል። አደጋ ያመጣሉ ተብለው በሚታሰቡት ላይም በፍተሻ መሳሪያዎች ተጨማሪ የማስተካከያ ስራዎች እንዲደረግ እንደሚሰራም አስታውቀዋል።

ፕሮጀክቶች በተለይ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያላደረጉ ከሆነ ዲዛይን አይሰጣቸውም ሲሉ ገልጸው፤ የ2003 ህንፃ አዋጅ መመሪያን መነሻ በማድረግ የዲዛይን ቁጥጥር ስራው ሲሰራ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ስለማድረጉ በቼክ ሊስት እንደሚታይታም ገልጸዋል።

በተለይም ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ እንደ ትላልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶች ያሉ ግንባታዎችን በዚያ ደረጃ እያረጋገጥን እንሰራለን ሲሉም ተናግረዋል። በሜጋ ደረጃ ያሉ ፕሮጀክቶች ወደ ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ሲመጡ የዲዛይኑ አንዱ ቼክሊስት አካል ሆነው እየተሰራበት መሆኑን አስታውቀዋል።

አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ ዲዛይን ያለማዘጋጀት ክፍተት በአብዛኛው የሚታየው በግሉ ዘርፍ በመገንባት ላይ ባሉት ግንባታዎች ላይ መሆኑን ጠቅሰው፣ የግሉ ዘርፍ ፕሮጀክቶች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ ግንባታዎችን በማካሄድ በኩል ዝንባሌአቸው ዝቅተኛ መሆኑን ይጠቁማሉ።

አብዛኛዎቹ የግንባታ ፕሮጀክቶች ዲዛይኖች በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ ጸድቀው የሚወጡ መሆናቸውን መሪ ስራ አስፈጻሚው ጠቅሰው፣ እነዚህን የመቆጣጠር እና አካል ጉዳተኛን ተደራሽ የማድረግ ሥራ በቀጣይ በትኩረት እንዲሰራበት ለማድረግ ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር ውይይት እየተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በግል ዘርፉ እና በሪል ስቴት ግንባታዎች ላይ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ ዲዛይኖች ላይ በቀጣይ በመነጋገር እና ሁሉንም የሚመለከታቸውን አካላት ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንደሚሰራበት አመላክተዋል።


እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በሕግ ማዕቀፉ እና በህንፃ አዋጁ ላይ ግንባታዎች አካል ጉዳተኞችን ማካተት እንዳለባቸው በገልጽ ተደንግጓል፤ በህንፃ ቁጥጥር ስራውም አንዱ የጥራት ማረጋገጫ መስፈርት የአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት ወይም በህንፃው አገልግሎት ተደራሽ መሆናቸው ላይ ያለው ምቹነት እንደሆነም ይፈተሻል። የአካል ጉዳተኞች መካተት ጉዳይ በአዋጆች ላይ የተቀመጠ መሆኑን ጠቅሰው፣ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ማየት እና መፈተሽ የሚፈልግ ሥራ እንዳለም አስታውቀዋል።

የባለሥልጣኑ አንዱ ተግባር በሀገር ደረጃ ያሉት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አዋጆች፣ ኮዶች፣ ስታንዳርዶች በግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ በአግባቡ መተግበራቸውን ይቆጣጠራል የሚል ተግባር እና ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑንም አስታውቀው፣ የዚህ ምሰሶም የህንፃው ዲዛይን መሆኑን ገልጸዋል። ይህ ዲዛይን አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ስለማድረጉ እየታየ እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ሁሉም አካል “የኔ ችግር ነው”፤ ባለቤት ነኝ ብሎ መስራት እንዳለበትም አስገንዝበዋል። ዛሬ ጤነኛ ሆኖ የሚንቀሳቀስ ነገ የሚገጥመው የማይታወቅ መሆኑን በማሰብ ጭምር ጉዳዩ በግንባታ ፕሮጀክቶች በሚገባ ተካቶ እንዲሰራበት ለማድረግ መስራት ይኖርበታል።

# ማህደረ ጤና

## ጤናማ ሕይወት ለእናትነት




**እየሩስ ተስፋዬ**

የጥር ወር ለኢትዮጵያ ልዩ ወር ነው:: ደስታ እና ፌሽታ የሚበዛበት የአደባባይ በዓል እንዲሁም የሠርግ ወቅት ነው:: ይህ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክዋኔዎች በስፋት የሚከወንበት ወር በጤናውም ዘርፍ «የጤናማ እናትነት ወር» ተብሎ ተሰይሟል:: በዚህ ልዩ ወር ጥንዶች ስለ ጋብቻ ሲያስቡ ጤናማ ቤተሰብ እና ጤናማ ልጅ እንዲኖራቸው ግንዛቤ እንዲያገኙ የተለያዩ ሥራዎች ይሠራሉ::

እንደ ሀገር ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረው «የጤናማ እናትነት ወር» ዘንድሮም «ፍትሀዊነት፣ ተደራሽነት እና ጥራት ያለውን የቅድመ ወሊድ ክትትል በወቅቱ በማስጀመር ጤናማ እናትነትን እናረጋግጥ» በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ኩነቶች እየተከበረ ይገኛል::

የጤናማ እናትነት ወርን አስመልክተው ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት በ1990ዎቹ የነበረው የእናቶች ሞት ምጣኔ በአሁኑ ሰዓት መቀነሱን የተናገሩት የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ፣ የጤናማ እናትነት ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው:: የጤናማ እናትነት እ.አ.አ በ2030 ለማሳካት ከተያዙት የልማት ግቦች አንዱ ሲሆን፤ በዘንድሮው በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት ተጎጂ የሆኑ እናቶችን በማሰብ፣ በአካባቢያቸው የጤና አገልግሎትን መልሶ ማቋቋምን ትኩረት አድርጎ እየተከበረ ይገኛል::

ሚኒስትሯ እንደጠቆሙት፤ እርግዝና ተፈጥሯዊና በራሱ ለአንዲት ሴት እና ቤተሰብ አስደሳች የሕይወት ምዕራፍ ቢሆንም ወቅቱን የጠበቀ የሕክምና ድጋፍና ክትትል ካልታከለበት ደስታው ዘላቂ ላይሆን ይችላል።

የቅድመ ወሊድ ክትትልን በጊዜ መጀመርና ቢያንስ ለስምንት ጊዜ በመከታተል፣ በሰለጠነ ባለሙያና በጤና ተቋም መውለድ መከላከል በምንችላቸው ምክንያቶች በሕይወት የምናጣቸው እናቶች እንዲሁም ጨቅላ ሕፃናት ሞትን በከፍተኛ ቁጥር እንዲቀንስ ያግዛል:: የአንድ እናት ሕይወት ህልፈት ለመላው ቤተሰብ፣ ማኅበረሰብ ብሎም በሀገር ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ የተናገሩት ዶክተር ሊያ፤ በሀገራችን በ2015 ዓ.ም የቅድመ ወሊድ ክትትልን ከ12 ሳምንት በፊት የጀመሩ እናቶች ምጣኔ 22 በመቶ ብቻ ሲሆን፤ ክትትላቸውን ስምንት ጊዜና ከዚያ በላይ ያደረጉት ደግሞ 15 በመቶ ብቻ መሆናቸው አክለዋል።

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ በበኩላቸው፤ ጤናማ እናትነት ወር የሚከበረው የእናቶችን ሞት ለመከላከልና ጤንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በንቃት እንዲሠሩበት ለማድረግ እንደሆነ ተናግረዋል።

የጤና ሚኒስቴር የእናቶችን ጤንነት ለማረጋገጥ የተቀናጀ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን እንዲተገበር በማድረግ፣ የቅድመ ወሊድ ክትትልን ተደራሽነትን በሁሉም ጤና ተቋማት በማረጋገጥ፣ በጤና ጣቢያዎች የቀዶ ሕክምና አገልግሎት በማስፋፋት፣ ከጤና ጣቢያዎች ርቀት ላይ ለሚገኙ እናቶች ደግሞ በጤና ተቋማት የእናቶች ማቆያ ቤቶችን በመገንባት ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ዶክተር ደረጄ አብራርተዋል።

በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የማህጸን እና የጽንስ ስፔሻሊስት እንዲሁም የጽንስ ሰብ ስፔሻሊስት የሆኑት ዶክተር ታደሰ ጉሬ እንደተናገሩት፣ በእኛ ሀገር ያሉ አብዛኛዎቹ እናቶች የእርግዝና ክትትል ማድረግ የሚጀምሩት ነፍሰጡር መሆናቸውን ካረጋገጡ ከሁለት እና ከዚያ በላይ ባሉት ወራት በኋላ ነው። እናት ጤና ልጅም ደህና እንዲሆኑ ባለትዳሮች የቅድመ እርግዝና፣ በእርግዝና ወቅት እና ድህረ ወሊድ ያሉ ክትትሎችን በተገቢው መንገድ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉም ይመክራሉ::

በጤና ሚኒስቴር የሥርዓተ ምግብ ማስተባበሪያ ሥራ አስፈጻሚ ክፍል ውስጥ የመከላከል ተኮር ዴስክ ኃላፊ የሆኑት ቅድስት ወልደ ሰንበት እንደሚሉት፤ አንዲት እናት ከመጸነሷ በፊት አንድ ወር ቀደም ብላ እንዲሁም እስከ ሦስት ወር ድረስ የፎሊክ አሲድ እንክብል በመውሰድ፤ የሰውነት ክብደት (መጨመርም ሆነ መቀነስ) በማስተካከል እና የተመጣጠነ ምግብ መውሰድ ልጅም እናትም ጤናማ እንዲሆኑ ያግዛል:: ምግብን ማስተካከል፣ ከሁሉም የምግብ ዓይነቶች አመሳጥሮ እና አመጣጥኖ መመገብ በእናቶች ላይ የሚደርሰውን ችግር አስቀድሞ ለመከላከል ያግዛል ይላሉ::

በጤና ሚኒስቴር የእናቶች፣ የሕፃናትና የአፍላ ወጣቶች መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር መሠረት ዘላለም በበኩላቸው፤ የጤና ሚኒስቴር የጤና አገልግሎቱን ከማስፋፋት ጎን ለጎን በጤና ኤክስቴንሽኖች አማካኝነት እናቶች ስለ ጤናቸው ሙሉ መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ የተሠራው ሥራ ውጤታማ እንደሆነ ይናገራሉ::

በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች በተከሰቱ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት ለእናቶችና ሕፃናት የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች ፈተና የገጠማቸው መሆኑን በመጠቆም፤ በተለይም በትግራይ ክልል በጦርነት እና ተፈጥሮአዊ ችግሮች ምክንያት መጠነ ሰፊ የአገልግሎት መስተጓጎል እንዳለና ችግሮቹን ለመፍታት የተጀመሩ ሥራዎችን በማጠናከር በጋራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል:: ከዚህ ጋር ተያይዞም የእናቶች ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል የጤናማ እናትነት ወር የንቅናቄ ማስጀመሪያ መድረክ በትግራይ ክልል መደረጉም አንዱ ማሳያ ነው ይላሉ::

የጤናማ እናትነት ወር ዘመቻ ዓላማ ታሳቢ በማድረግ እናቶች የቅድመ ወሊድ ክትትልን በጊዜ ካለመጀመር ጋር በተያያዘ ያሉትን ችግሮች በተገቢው መንገድ መከላከል እንዲቻል፣ ብሎም በባለሙያ የታገዘ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማገዝ የትግበራ አቅጣጫዎች ላይ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነታቸውን ወስደው መሥራት እንደሚገባቸውም አስቀምጠዋል::

ዶክተር መሠረት እንደሚስረዱት፣ እናት ጤናማ ሳትሆን ስለሀገር ጤናማነት ማሰብ ይከብዳል:: ከዚህ ጋር ተያይዞም ስለ ሀገር እድገትም ሆነ ብልጽግና ማሰብ ከቶ አይቻልም:: የእናቶች ሞት እየቀነሰ ቢመጣም ብዙ ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው።

በትግራይ ክልል የጤና አገልግሎትን ለማሻሻል የመድኃኒትና የሕክምና ግብአቶች ድጋፍ በማድረግ፣ ሥልጠና በመስጠት፣ የሥነ ልቦናና የአእምሮ ጤና ድጋፍ እየተደረገ መሆኑና በሂደት ላይ ያሉ ሰፊ ሥራዎች መኖራቸውን የተናገሩት ዶክተር መሠረት፤ የጤናማ እናትነት ወር ምክንያት በማድረግ ጤና ሚኒስቴር በርካታ አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር 12ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የሕክምና ግብአቶችን ድጋፍ እንዳደረገም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የስምምነት ሰነድ ከተፈራረመችባቸው ቁልፍ ጉዳዮች መካከል የእናቶች የጤና ጉዳይ አንዱ ነው:: «የእናቶችን ሞት መቀነስ ቁልፍ የሆነ ሀገራዊ አጀንዳ ነው» ያሉት ዶክተር መሠረት፣ በመሆኑም በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድ ጊዜና በድህረ ወሊድ ተደራሽ የሚደረጉ መረጃዎችና አገልግሎቶች መኖራቸውን ያስረዳሉ:: አብዛኛውን የሀገራችን ሕዝብ በገጠር የሚኖር እንደመሆኑ በተለይም በጤና ኤክስቴንሽን መርሐ ግብር በኩል አገልግሎቱ ተደራሽ እየተደረገ እንደሚገኝም አክለዋል።

እንደ ዶክተር መሠረት ገለፃ፤ በገጠሩ የሀገራችን ክፍል እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች መካከል እናቶች ከመውለዳቸው በፊት ጥቂት ጊዜ ሲቀራቸው የሦስት ዓመትና ከዚያ በታች ልጅ ካላቸው ልጆቻቸውን ይዘው በአቅራቢያቸው ባለ ጤና ጣቢያ ቆይተው ክትትልና ድጋፍ ተደርጎላቸው፤ ምግባቸው ተሟልቶላቸው፣ ጤናቸው ተጠብቆላቸው ልጅ ወልደው እንዲሄዱ ይደረጋል:: በተጨማሪም እናቶች ከጤና ኬላ ተነስተው ፣ ጤና ጣቢያ እንዲሁም ሆስፒታል ድረስ በሚያደርጉት የጤና ክትትል የግንኙነት መስመሩ የተመቻቸ እንዲሆን በሙያው የተሻሉ የጤና ባለሙያዎች በአቅራቢያቸው በሚገኝ የጤና ተቋማት ተገኝተው ድጋፍ የሚያደርጉበት የአጥቢያ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ አሠራርም ተፈጥሯል።

በሀገራችን ያሉ ሁሉም ወረዳዎች በአስፋልት ወይም በመንገድ የተገናኙ እና ምቹ እንዳልሆኑ ይታወቃል:: በዚህ ረገድ የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ላይ ብዙ መሥራትን ይጠይቃል የሚሉት ዶክተር መሠረት፤ የእናቶች ጤና መሠረታዊ ከሆኑ አገልግሎቶች ጋር በእጅጉ የተገናኘ መሆኑን ነው የሚያብራሩት:: ለአብነት ከመንገድ፣ ከስልክ፣ ከመብራት፣ ከውሃ፣ ከትራንስፖርት እና ከሌሎችም ጋር የተያያዘ ነው:: በተለይም ነፍሰጡር ለሆነች ሴት የመውለጃ ጊዜዋ ሲደርስ በመኪና አልያም የአምቡላንስ አገልግሎት በመስጠት የእናትንም የሕፃናትን ጤና ለማስጠበቅ ብዙ መሥራት እንደሚስፈልግ አጽንኦት ሰጥተውታል።

ዶክተር መሠረት ሲያብራ፤ እናቶችን ከሞት ለመታደገ በሚሠሩ ሥራዎች ከሌሎች ሥራዎች ጋር መጋቢ ወይም አብሮ ከሚሠሩ ፕሮግራሞች ጋር አያይዞ መሥራትን ይጠይቃል:: ዛሬም ቢሆን ቤታቸው የሚለወልዱ እናቶች አልጠፉምና የመረጃ ተደራሽነት ላይ በስፋት መሠራት አለበት። የመረጃ እጦት እናትንም ልጅንም አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ፤ መሠረተ ልማት ያልተስፋፉባቸው አካባቢዎች ላይ አማራጭ መንገዶችን እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንፃር ሰፊ ሥራዎች ይሠራሉ።

እንደ ጤና ሚኒስቴር ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል የተሠሩ ሥራዎች መኖራቸውን የሚገልጹት ዶክተር መሠረት፤ በደም መፍሰስ የሚሞቱ እናቶችን ለመታደግ በተለይም ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ ሥራዎች መሠራቱን ያወሳሉ:: በመረጃ እጦት፣ የጤና ተቋማት ዝግጁ አለመሆን እና በመሠረተ ልማት ችግር በደም መፍሰስ ሕይወታቸው የሚያልፉ እናቶችን ሕይወት ለመታደግ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ70 ሆስፒታሎች የመለስተኛ የደም አገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲኖራቸው የግብአት ድጋፍ መደረጉንም ያስረዳሉ::

በአጠቃላይ በእናቶችና ሕፃናት ጤና አገልግሎት እንደ ሀገር ባለፉት ዓመታት በተሠሩ ሥራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የእናቶችና ሕፃናት ጤና አገልግሎት መሻሻል የታየበት መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር መሠረት ፤ በቀጣይም በሚከናወኑ ተግባራት የሁሉም አጋር አካላት በትብብር እና በቅንጅት መሥራት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ባይ ናቸው::

# ነፃ ሃሳብ

# የሀገራችን ሰላም በእጃችን ነው!

**ታሪኩ ዘለቀ**

አስራት ፈጠነ የተባለ ግለሰብ ” ከአንተ ሌላ ለአንተ ሰላም የሚሰጥህ የለም” በሚል ርዕስ በፃፈው መጣጥፍ፤ሰላም ምትክ የማይገኝለት በህይወት የመኖር፣ ሰርቶ የመለወጥ፣ ወጥቶ የመግባት፣ ተኝቶ የመነሳት ምስጢር መገለጫና በገንዘብ የማይተመን ስጦታን በውስጡ የያዘ ነው። ብሏል።

በእርግጥም ያለ አስተማማኝ ሰላም ህዝብም ሆነ ሀገር የመለወጥና የማደግ ተስፋው የሰማይ ያህል ሩቅና የማይደረስበት ይሆናል። በጫካ የሚኖሩ አእዋፋት እንኳ ሳይቀር የመኖሪያ ጎጇቸውን ጠብቀውና የእለት ምግባቸውን ጭረው ለመብላት፣ ተፈጥሮ የለገሳቸውን ዝማሬ ለማሰማት ሰላም ይሻሉ። የዱር አውሬም እንዲሁ።

በተለይማ ወደዚች ምድር ‹‹ለፍተህ፣ ጥረህ፣ ግረህና በላብህ ብላ›› ተብሎ ለተፈጠረው የሰው ልጅ ያለ ሰላም አንድ እርምጃ እንኳን መራመድ እንደማይችል ከተሞክሮ ማየት ይችላል። ሁከትና ብጥብጥ ለአእምሮም ይጨንቃል። ድምር ውጤቱም ጥፋትና ውድቀት ብቻ ነው።

የተራበ ምግብ እንዳያጣ፣ የተጠማም ጉሮሮው እንዳይደርቅ፣ ዳቦ በሌማት፣ ውሃ በእንስራ በበረንዳቸው የሚያኖሩ ዜጎች ዛሬ የሰላምን ንፋስ ይናፍቃሉ። ከአንዱ ቀበሌ ወደ ሌላው ቀበሌ እንደቀደሙት ጊዜያት እንዳሻቸው መንቀሳቀስ እንዲችሉ ሰላም ያስፈልጋቸዋል።

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮች የህዝቡን የዕለት ተእለት እንቅስቃሴ እያስተጓጎሉ ይገኛሉ።ይሔንና ከላይ ከጠቀስነው የሰላም ዋጋ አንፃር መሰል ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ ሀገሪቱ በተለያዩ ጊዜያት የምታገኘውን ሰላም ዘላቂ ማድረግ ያስፈልጋል።

የሀገራችን ዋነኛ የሰላምና ደህንነት ችግር ውስጣዊ ነው። ዋልታ ረገጥ የሆኑ እና በእኔነት ላይ የተመሰረቱ የብሔርተኝነት ዕሳቤዎች ለኢትዮጵያ ፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ናቸው። እነዚህ ውስጣዊ ችግሮች መፍትሄ እስካላገኙ ድረስ የቅርብ ሆነ የሩቅ ጠላቶቿ ሁኔታውን እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ የተጨማሪ ችግሮች ምንጭ መሆናቸው የማይቀር ነው።

ባለፉት አመታት የተጋፈጥነው የግጭትና መፈናቀል አዙሪት ኢኮኖሚውን ጭምር ምን ያህል እንዳናጋው ታይቷል። ሰላምን ለመጠበቅ ቅድሚያ ለመስጠት እንዲሁም የፖለቲካ ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት ቀናኢ አለመሆን ደግሞ ላለፍናቸው የሰላም ናፍቆት ወቅቶች አጋልጠውናል።

አሁን የሚስተዋለው የኑሮ ውድነት ሀገራችን ካለችበት አሁናዊ ሰላም ጋር ይገናኛል። አርሶ አደሩ ያመረተውን ምርት ገበያ ላይ አቅርቦ ለመሸጥ የሰላም እጦት ፈትኖታል። የኢኮኖሚ አሻጥረኞችም ለግል ኪሳቸው ማደለቢያ እየተጠቀሙበት ነው።ሸጦ ለውጦ ህይወቱን መምራት የማይችልበት ሁኔታዎችም ተፈጥረዋል።

በእርግጥ ሰሞናዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ ሀገሪቱ ቀደም ሲል አጋጥሟት ከነበረው የደህንነት ስጋት ስለመሻገሩዋ የሚናገረው ቢኖርም፤ከሰላም ጋር በተያያዘ ጎዶሎዋ ግን አሁንም ብዙ ነው። አሁንም የሰላም ጉዳይ የህዝቡ ጥያቄ እንደ ሆነ ነው። ስለ ሰላም የሚጮሁም በርካቶች ናቸው። ይሑንና እጅ ላይ ያለን አንፃራዊ ሰላም ጠብቆ ማፅናት የግድ ነው።

> **ለነገዎቻችን ብሩህነት ካለፈው ያለመግባባት ታሪካችን ብዙ ልንማር ይገባል። ከሁሉ በላይ በኃይል የምንፈልገውን ማሳካት እንደማንችል ጠንቅቆ ሊገባን ግድ ይላል**

እንደ ሀገር አሁን ላይ የተፈጠረውን አንፃራዊ ሰላም ዘላቂ ለማድረግ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ የሰላምና ደህንነት ሥራን አጠናክሮ መስራት ያስፈልጋል። ይህ የሰላምን አስፈላጊነት በማህበረሰቡ ውስጥ ከማፅናት ጀምሮ ሰላሙን በራሱ እንዲጠብቅ ማስቻልን የሚያካትት ነው።

ባለፉት ጊዜያት የሰላም አየር ለመተንፈስ የመቸገራችን ዋነኛ ምክንያት ተደርገው ከሚጠቀሱት መካከል የፖለቲካ ባህላችን አለመዘመኑ አንደኛው ነው።በተለይም አንድን ስርአት በድርድር፣ በሰላም አሊያም በዴሞክራሲዊ ምርጫ ሳይሆን በኃይልና በጉልበት ለመጣል ማሰባችን በንግግር እንፈልገዋለን የምንለውን ሰላም በተግባር አሳጥቶናል።ያለፍንበት የፖለቲካ ባህል እና ፖለቲካው ይሰራበት፣ይተገበርበት፣ ይደረግበት ከነበረው ዘዴ መውጣት አልቻለም።

በሰለጠነ ውይይት ሰጥቶ በመቀበል ሳይሆን በጠመንጃ አፈሙዝ አሸንፎ ሁሉንም አጥፍቶ እንደ አዲስ በመጀመር ነው። ይሄ መንገድ በፖለቲካ ባህላችን የተለመደ ነው። ይሄ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ውስጥ ስር ሰድዷል። ትልቁ ነገር ከዚህ መላቀቅ አለመቻላችን ነው።

ሰላምን ያፀናሉ የምንላቸው የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሲቪክ ማህበራት ተፅዕኖ የማሳደር ጉልበታቸው እየላላ መምጣትም ሌላኛው ነው።ይህም ሀገሪቱን ሰላም እንድታጣ፣ምጣኔ ሀብቷ እንዲዳከምና ከገባችበት ቅርቃር እንዳትወጣ አድርጓታል።

ይሑንና ካለፈው አዙሪት ልንፋታ የሚገባን ትክክለኛው ጊዜ አሁን መሆን አለበት። ይህ ካልሆነ ሰላም እንደናፈቅን ይቀራል።ሰላምም ማጣጣም የምንሻ ከሆነ ደግሞ ስለሰላም መጨነቅ መስራት መተባበር ይኖርብናል።

በተለይ በሰላም እጦት ትርምስ ውስጥ እንዳንገባ መደረግ ካለባቸው በርካታ ጉዳዮች መካከል የመጀመሪያው በልዩነቶቻችን ዙሪያ ሀገራዊ መግባባት ላይ መድረስ ነው። ጠረጴዛ ስበን ቁጭ ብሎ በመነጋገር መግባባት ላይ ልንደርስ እንደምንችል ማመን ብሎም መስማማት አለብን።

የእኔ ብሄር፣ ጎሳ፣ ሰፈር...ወዘተ ከሚለው የተበላሸ እሳቤ መውጣትም ግድ ይለናል። በተለይ የህዝብ ውክልና ያላቸው ግለሰቦች፣ የፖለቲካ ልሂቃን ወይም ካድሬዎች ለሰላም በቁርጠኝነት አበክረው መስራት ይጠበቅባቸዋል ።

ለነገዎቻችን ብሩህነት ካለፈው ያለመግባባት ታሪካችን ብዙ ልንማር ይገባል። ከሁሉ በላይ በኃይል የምንፈልገውን ማሳካት እንደማንችል ጠንቅቆ ሊገባን ግድ ይላል። ኃይል አሁን ላይ ይህ ዘመኑን የሚዋጅ አስተሳሰብም ብሎም ድርጊት አይደለም።ከዚህ በፊት ተሞክሮ ያልተሳካ ነገር ነው።

ይህ እንደመሆኑም ካለፈው ታሪክና ነባራዊ ሁኔታ ተምረን በሰለጠነው መንገድ በምክክር ፤በምርጫ ስልጣን መያዝ እንዳለበት ማመን አለብን።ከዚህ ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለም በከፊል ሳይሆን በሙሉ ልብ መቀበል ያስፈልጋል።

ልዩነቶችን ሁሉ በጉልበት ለመፍታት የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ ያተረፉት ነገር ሰብአዊ እልቂትና ቁሳዊ ውድመት ብቻ ነው። በዚህ መካከል ዋነኞቹ ተጎጂዎች የፖለቲካ ተዋንያኑ ሳይሆኑ ንፁሀን ናቸው። በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ ግጭቶችን በህገ አምላክ ብሎ ማስቆም ካልተቻለ መጪው ጊዜ ከበፊቱ የበለጠ መከራ ሊያስከትል እንደሚችል ለመገመት ነብይ መሆንን አይጠይቅም። እዚህም እዚያም የሚታዩ የግጭት ምልክቶች ህብረተሰቡ ጭንቀትና ስጋት የወረረው ህይወት እንዲመራ ምክንያት እየሆነ ነው።

እንዲህ አይነት ተስፋ የሚያሳጡ ችግሮች ሲደጋገሙ የመንግሥት ተቀዳሚ ተግባር ህዝብን የሚያረጋጉና በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የባለቤትነት ስሜት በሚፈጥሩ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ነው። እርግጥ ነው ሀገር ችግር ውስጥ በምትገባበት ጊዜ እያንዳንዱ ዜጋ የችግሩ ተጋሪ ብቻ ሳይሆን ከችግሩ የሚያወጡ መፍትሄዎችን እንዲያመነጭና አስተዋፅኦ እንዲኖረው ማበረታታት ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በእርሱ ምንም ችግር የለበትም። ኦሮሞ ከትግሬ፣ትግሬ ከአማራ፤አማራ ከኦሮሞ፣ ወላይታ ከከምባታ፣ ስልጤ ከጋምቤላ፣ ጉራጌ ከከፋው ጋር ምንም ችግር የለበትም።

በዚህ መልክ ከተሳሰረና ከሚዋወድ ህዝብ ዘንድ ዘልቆ ገብቶ የጠብ ዳቦ የሚጋጋረው የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ብሎም በህዝቦች ግጭት ለማትረፍ የሚታትረው ሴረኛው ነጋዴ ነው።

ይህን ሃቅ አሁን ላይ በርካቶች ጠንቅቀው ያውቁታል። ይህ ማለት ግን ሁሉም ያውቀዋል ማለት አይደለም።አንዳንዶች አሁንም የሴረኞች ሰለባ ሲሆኑ ይስተዋላል። ይህ መታረም ያለበት ድክመት ነው።ይህን ድክመት ማስተካከልም በኢትዮጵያ ምድር ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ከሚያግዙ ግንባር ቀደም መፍትሄዎች አንዱ ነው።

የሀገር ባለቤት የሆነው ህዝብ ምክረ ሀሳብ ቢጠየቅ መፍትሄዎችን እንደሚያመነጭ መጠራጠር የለብንም።አሁን የኢትዮጵያ ችግሮች የበዙ ቢመስልም በትብብርና በመነጋገር ግን መስመር እንዲይዙ ማድረግ አይከብድም።

በሀገረ መንግስቱ ውስጥ ያሉትን ልዩነቶች ቢያንስ እንኳ አጥበን፣ ከሁሉም በፊት ሀገር ትቀድማለች የሚል የተረጋጋ የሰከነ መንግሥትም ከመፍጠርም አንፃር ሁላችንም የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል።

የትናንት አብሮነታችን የጋራ ስኬቶቻችን ምስጢር ናቸው። ለዚህም ነው በችግሮቻችን ላይ ተወያይተን ነገን ያለህፀፅ ለትውልድ ለማስተላለፍ የምናገኘውን አንፃራዊ ሰላምን ማፅናት የግድ ይለናል የሚባለው።

መፍትሄው በሁላችንም እጅ ነው።መንግሥት ሀገረ መንግሥትን የሚያጸኑ ተቋማትን የመገንባት ታሪካዊ ኃላፊነት አለበት። ይህን ታሪካዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የዛሬን ሳይሆን የነገዋን ኢትዮጵያ ታሳቢ ያደረገ የተቋማት ግንባታ ላይ ሊያተኩር ይገባል። ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑም ለዚህ ትልቅ አቅም እንደሚሆን አይጠያይቅም።

መንግሥታዊ ያልሆኑ የሲቪክ ማህበራት፣ የሀገር ሽማግሌዎች በሀገሪቱ በሰላም በማጥናት ሂደት ውስጥ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው።ትክክል ያልሆነውን ትክክል አይደለም ማለት ፤መገሰፅ ያለባቸውን አካል ፊት ለፊት መገሰፅ መቻል አለባቸው። ሁሉንም በትክክለኛው መንገድ በማስተካከል የኢትዮጵያ ሰላም እንዲፀና ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ።

የብርቱ አርሶ አደር ጎተራዎች በእህል እንዲሞሉ፣ ኢትዮጵያም ምጣኔ ሀብታዊ እድገቷን እንድታስቀጥል፤ የተጀመረው ሀገራዊ ልማት ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሻገር ሁለንተናዊ እድገትን እውን ለማድረግ ከሁሉም በላይ ዘላቂነት ያለው ሰላም ማስፈን የግድ ነው። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ዜጋ ስለሰላም በኃላፊነት መንፈስ ሊነሳ ይገባል።

# ተናጋሪው ዶሴ

## ያስጠጉትን ማጥቃት ከጥፋት ሁሉ የላቀ ጥፋት

**አስመረት ብስራት**



**ፖሊስ በሕክምና ምርመራ ተደጋጋሚ ጥቃት መፈፀሙን ከመረዳቱ ባሻገር ይህች ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰች አፍላ ወጣት ልጅ ተገዳ በተደፈረችበት ሁኔታ ውስጥ ሆና መፀነሷን ማወቁ አሳሰቦታል**

አስገድዶ መድፈር የፆታዊ ጥቃት ዓይነት ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች ከሌላ ሰው ፈቃድ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የሚያካትት ነው። አስገድዶ መድፈር የሚፈጽሙ ሰዎች የተጎጂውን አቅም ማጣት (የንቃተ ኅሊና ማጣት፣ ከፍተኛ የአልኮል ስካር፣ የአእምሮ ሕመም)፣ አካላዊ ጥቃትን ወይም የአጠቃቀሙን ስጋት፣ የሥነ-ልቦና ጫና፣ የተጎጂውን ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ ወይም ሌላ ጥገኝነት ይጠቀማሉ።

አስገድዶ መድፈር ከፆታዊ ወንጀሎች አንዱ ነው። ትክክለኛው ፍቺው በተለያዩ ግዛቶች ሕግ ይለያያል... «ብዙ ደፋሪዎች አይደፈሩም» ምክንያቱም ጉዳት ለማድረስ ስለሚፈልጉ በቀላሉ እሷን/እሱን እንደ ህያው ሰው አይገነዘቡም ወይም አይቆጥሩም።

ስለ አስገድዶ ደፋሪዎች ለምን ተነሳ ቢባል በየጊዜው የምንሰማቸው ነገሮች በጣም አሳዛኝ ነገሮች በመሆናቸው ነው። ድርጊቱ ብዙዎችን የሚያሳዝን የሚያስቆጣ ከባህላዊ እሴታችን ጋር የማይሄድ ማኅበረሰባዊ ሕግና ሥርዓትን የጣሰ ነውር ነው።

ከዚሁ ኀዘንና ቁጣ በመነሳት አንዳንድ ሰዎች መደረግ ያለበትን እርምጃዎች ይጠቅሳሉ። በሕግ የተቀመጠው ቅጣት አነስተኛ ነው። ወደ ሞት መቀየር አለበት የሚሉ ሃሳቦች ይሰማሉ። እንዲህ ዓይነት ወንጀል የሠሩ ሰዎች ስማቸው፣ አድራሻቸውና እንቅስቃሴያቸው ሊመዘገብና ለሕዝብ ይፋ መሆን አለበት የሚሉ ሃሳቦች ይሰማሉ።

የወንጀል ቅጣትን ውጤታማ ማድረግ የሚቻለው ቅጣትን በመጨመር ብቻ አይደለም። የመያዝና የመቀጣት ዕድሉን በመጨመር፣ ፈጣን የፍትህ ሂደት እንዲኖር በማድረግና በመሳሰሉትም ነው። ከሁሉም በላይ ግን ለወሲባዊ ነፃነት ያለንን ማኅበራዊ እይታ በመፈተሽ ነው።

በአንዳንድ ሀገራት የወሲብ ጥቃት ፈፃሚዎች ስም፣ አድራሻ፣ እንቅስቃሴ እንዲመዘገብና ይፋ እንዲሆን ያደርጋሉ። ጥያቄው ምን ዓይነት ውጤት አለው? ከድርጊታቸው መውጫ ቀዳዳውን በማጥበብ በዚያው እንዲወሰኑ የሚያደርግ ስለሆነ። ፍትህ የራሱን ወሳኔ ቢሰጥም ቅሉ እንደ አንድ ማኅበረሰብ የችግሩን ስፋት በመመልከት መሻሻል ቢኖር የሚሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሃሳብም እንዳይዘነጋ በማለት ነው ይህን ሃሳብ ያነሳነው። ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ ልንል የወደድነው ለዛሬ ከአዲስ አበባ ፖሊስ መዝገብ ቤት ያገኘነውን የወንጀል ታሪክ ልናካፍላችሁ ስለሆነ ነው። መልካም ቆይታ።

### ወጣትዋ ማስተዋል

ማስተዋል አይቸው ትባላለች። ከተወለደችበት ቀዬ የዋጣችው የዕድሜዋን መጨመር የተመለከቱ ልጅነቷ አልፎ ወደ ወጣትነት መሸጋገሯን የተመለከቱ የአካባቢው ጎረምሶች ከዓላማዋ እንዳያሰናክሏት በሚል ነበር። ልጅቷ ጎንታይዋ ሲበዛ የሩቅ ዘመድ የተባሉ ሰዎች ተፈለገው እነሱ ጋር ተጠግታ እንደትማር በሚል ነበር የሞቀ የእናቷን ቤት ጥላ የወጣችው።

እንደመጣች ትምህርት ቤት በመግባቷ እጅግ በጣም ነበር የተደሰተችው። ከተወለደችባት ቀዬ የወጣቸው በ15 አመቷ ነበር። ልጅነትና ጉርምስና መካከል የምትዋዥቀው ቆንጆ ቀን ትምህርት ቤት ውላ ከትምህርት ቤት መልስ አሳዳሪዎቿን በሥራ በማገዝ ለማስደሰት ትጥር ጀመር።

ከትምህርትና ከቤት ውስጥ ሥራ የተረፋትን ጊዜ ዓላማዬ ነው ላለችው ከትውልድ ቀዬዋ ላስወጣት ትምህርቷ ስኬት እንቅልፍ ራሱ ገፍቶ እስኪጥላት ድረስ ታነባለች። ከዚያ ደግሞ ማልዳ ተነስታ አስፈላጊውን የቤት ውስጥ ሥራ ከውና ወደ ትምህርት ቤት ትሮጣለች። እንዲህ እንዲህ እያለች ለሦስት አመታት የቀጠለችው ልጅ ዕድሜዋ ሲጨምር ውበቷ ጎልቶ መታየት ጀመረ። ሸሽታ ያመለጠችው የመሰላት ጉንተላም እዚህ ድረስ ተከትሏት መጣ።

የውጪውን ጫና እንደምንም ተቋቁማ ትምህርቷን ዳር ለማድረስ መትጋት ጀመረች። ከቤት ውጭ ያለውን ታግላ ልታሸንፍ ብትታትርም የሩቅ ዘመድ ነው እሱ ጋር ተጠግተሽ ትምህርትሽን ዳር ታደርሻለሽ ተብላ የተጠጋችውን በእሷ አጠራር የአጎቷን ጉንተላ ለማስቆም አቅም ተሳናት።

በቤት ውስጥ ሥራ ድካም የተጫጫናት ወጣት የጀመረቻትን ለመጨረስ ከእንቅልፍ ጋር እየታገለች ጥናቷን እያጠናች በነበረችበት ወቅት ነበር የተቀመጠችበት የመኝታ ቤቷን በር ገፋ ተደርጎ የተከፈተው። የምትተኛው ከዕቃ ቤቱ አንድ ጥግ ላይ ስለነበር ውሃ ፈልጎ ወደ ክፍሉ የመጣ መሰሏት ስለነበር ከተቀመጠችበት ተነስታ ልታቀብለው ስትሞክር ነበር ወትሮም ተዘጋጅቶ የመጣው ሰው ባላሰበችው መልኩ እጅና አፏን ይዞ አልጋ ላይ የጣላት።

የምትወደውን ትምህርቷን እንዳያስተጓጉላት ከተወለደችበት ቀዬ ያሉ ጎረምሶችን ሸሽት የተጠጋችው ሰው የፈራችውን ነገር ፈፀመባት። ህልሟን ለማሳካት የተጠጋችው ግንብ ባላሰበችው መልኩ ህልሟን ደፍልቆ ጣለው።

### አስጠጊው አጥቂ

ይድነቃቸው በላይ ይባላል። ከተወለደበት አካባቢ በትምህርቱ የገፋ ስለነበረ በአካባቢው ሰው የተከበረ የችግር ጊዜ መወጫ እንደሆነ ተደርጎ የሚታሰብ ሰው ነበር። ትንሽ ትልቁ ጎንበስ ብሎ ሰላም የሚለው ኮሌጅ የበጠሰ ነው የሚባለው ይህ ሰው በአጋጣሚ ወላጆቹን ሊጠይቅ ወደ ተወለደባት ቀዬ ሲሄድ ነበር የማስተዋልን ወላጆች ያገኛቸው።

በአካባቢያቸው የተማረ ከተማ የሚኖር አንድ እሱ በመሆኑ ነገ ተምራ ሰው የደረሰበት ትደርስላች ያሏትን የዓይን ማረፊያ የሆነችውን ልጃቸውን ወስዶ እንዲያስተምርላቸው ይለምኑታል። ወላጆቹን ለመጠየቅ ብሎም ባለቤቱ አጋዥ ያስፈልጋት ስለነበር ሰው ይዞ ለመመለስ አቅዶ የነበረው ይህ ሰው ጥያቄው ከነሱ ከመጣ ብሎ ይስማማል።

ባለቤቱም እየረዳቻት ራሷን ለመቻል የምትታትር ቀልጠፍ ያለች ልጅ ስለመጣች ደስ ብሏት እየተጋገዙ እንድትማር ትፈቅዳለች። ዘመዳችን ነው ላሉት ሰው ልጃቸውን አምነው የሰጡት ወላጆች አመት አመትን እየወለደ ልጅቱም ጠንክራ እየተማረች መሆኑን ሲረዱ ሃሳባቸውን ጥለው በሰላም ኑሯቸውን ቀጠሉ።

ማስተዋልም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባልና ሚስቱ በምን ምክንያት እንደሚጣሉ ባይገባትም መጨቃጨቃቸው እያሳሰባት ቢሆንም ይህ ነው የሚባል ችግር ከመጣች ጊዜ አንስቶ ገጥሟት አያውቅም ነበር።

ከቀየዋ ያመጣትም ሰው አስፈላጊውን ነገር እያሟላላት ያስተምራት ስለነበር አስብቶ ያርደኛል የሚል ግምት አልነበራትም። ከሚስቱ ጋር ግጭት የጀመረው ይህ ሰው የቤቱ ሰላም ሲደፈርስ ዓይኑ ውጪን ማማተር ጀመረ። ውጭ ላይ ያሰበውን ያህል ነገር ሳያገኝ ቀርቶ ዓይኑን መለስ ሲያደርግ ነበር የልጅነት መልኳ ወጥቶ አዩኝ አዩኝ የምትለው የዘመድ ልጅ ናት የተባለችው ማስተዋል ላይ ዓይኑ ያረፈው።

አይቶ ልቡ ካሰባት ቀን ጀምሮ ይከታተላት የነበረው ይህ ሰው አምሽታ እያነበበች ቆይታ በዚያው እንቅልፍ እንደሚወስዳት አስተውሏል። ይህን ተገን አድርጎ ቀኑን ጠብቆ የባለቤቱን እንቅልፍ ውስጥ መሆን በመመልከት ወደ ልጅቷ መኝታ መጣ። ልጅቷ የሥራ ጫናና እንቅልፍ አዳክመዋት በነበረበት ሰዓት አግኝቶ የፈራችውን ነገር በሙሉ ፈፀመባት።

በዚህ ቢበቃው መልካም ነበር። ልጅቷ ባልና ሚስቱ እንዳይጣሉ በመስጋት ዝም ስትል እያስፈራራ በተደጋጋሚ ይደፍራት ጀመር። በዚህም የተነሳ እርግዝና የተከሰተባት ይህች ልጅ የሆነችውን በሙሉ አብራት ወደ ትምህርት ቤት ለምትሄድ ለጎረቤት ልጅ ተናገረች።

### ጎረቤቶቹ

በየዕለቱ እየተፈፀመባት ያለውን ነገር አብራት ለምትሄደው የጎረቤት ልጅ የተናገረችው ማስተዋል መሄጃ በማጣቷ ጉዳዩን አፍና መቀመጧን ታስረዳለች። ይህን የሰሙ ጎረቤቶች ጉዳዩን በደንብ በማጣራት ለፖሊስ መረጃውን ያቀብላሉ። ፖሊስም ጥቃት የደረሰባትን ልጅ መርምሮ ደህንነቱ በተጠበቀ ማረፊያ ውስጥ ካኖራት በኋላ ነበር ጥቃት አድራሹን በቁጥጥር ስር ያዋለው።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ በሕክምና ምርመራ ተደጋጋሚ ጥቃት መፈፀሙን ከመረዳቱ ባሻገር ይህች ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰች አፍላ ወጣት ልጅ ተገዳ በተደፈረችበት ሁኔታ ውስጥ ሆና መፀነሷን ማወቁ አሳሰቦታል። ይህን እምነቱን ያጎደለ ሰው በምስክሮችና በተጠናከረ መረጃ በቁጥጥር ስር አውሎ ቃሉን ተቀብሏል።

ተከሳሽ ይድነቃቸው በላይ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታው ኪንባ ሠፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ነው። ይህ ሰው በሰኔ ወር 2014 ዓ.ም በግምት 12፡30 ሰዓት ሲሆን ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰች ልጅ ላይ የግብረ ስጋ ድፍረት በመፈፀሙ የተነሳ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 626/4/ሀ/ እና 628/ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል በመከሰስ ፖሊስ መረጃውን ለአቃቤ ሕግ አቅርቧል።

### የዐቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር

ዐቃቤ ሕግም የክስ መዝገቡ እንደደረሰው ጉዳዩን መመልከት ጀመረ። የክስ ዝርዝሩ እንደሚያስረዳው የግል ተበዳይ ከ17 እስከ 18 ዓመት የምትሆን እና በተከሳሽ ቤት ውስጥ በጥገኝነት የምትኖር ስትሆን ተከሳሽ ቀኑ ባልታወቀ ሰኔ ወር 2014 ዓ.ም በራሱ የመኖሪያ ቤት ውስጥ በተደጋጋሚ የግብረስጋ ግንኙነት በመፈፀም ተበዳይዋን ለእርግዝና የዳረገ መሆኑ እና ቀኑ ባልታወቀ ግንቦት ወር 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት እስከ 4፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ በተከሳሽ መኖሪያ ውስጥ በተደጋጋሚ በማስፈራራት እና በማስገደድ የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመባት በመሆኑ ተከሳሽ በተበዳይ ላይ የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል የፈፀመባት በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶበታል፡፡

ዐቃቤ ሕግ የተከሳሽን ጥፋተኝነት ያስረዳሉ ያላቸውን 2(ሁለት) የሰው ምስክሮችን እና 2(ሁለት) የሰነድ ማስረጃዎችን በማቅረብ የተከራከረ ሲሆን ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ቢሰጥም ተከሳሽ ያቀረበው የመከላከያ ምስክር ጥፋቱን ያላስተባበለ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን ጥፋተኛ ነው ብሎታል፡፡

### ውሳኔ

**በመጨረሻም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ወንጀል ችሎት ኅዳር 12 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሹን በስምንት (8)ዓመት ፅኑ እስራት እና ከሕዝባዊ መብቱ ለ2 (ሁለት ዓመት) ተገድቦ እንዲቆይ በማለት ወስኖበታል፡፡**

## ከአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ዲጂታላይዜሽን በሆስፒታሉ ሕክምና አሰጣጥ ላይ ያመጣው ለውጥ

**መክሊት ወንድወሰን**

ያለንበት ዘመን የዲጂታላይዜሽን በመሆኑ ተቋማት ራሳቸውን በማሳደግ የዲጂታላይዜሽን ሲስተምን ያስተዋውቃሉ፣ ተግባራዊ ያደርጋሉ:: ይህ የዲጂታል ሲስተም አሠራር የተቋማቱን የመረጃ አያያዝ ከማዘመን እና ከማቅለል ባሻገር ከደንበኞቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ሰላማዊ እና ተግባቦት የተሞላበት ያደርገዋል:: የአማኑኤል ሆስፒታልም በተለያዩ ክፍሎች ወደ ሆስፒታሉ የሚመጡ ታካሚዎችን ለአመታት በማኑዋል ሲስተም ሲያገለግል ቆይቷል:: የዲጂታል ሲስተም በተለይም አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ላይ ተግባራዊ መደረጉ ጠቀሜታው አጠያያቂ አይደለም ::

በመሆኑም በአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለሕክምና አገልግሎቱ መሠረታዊ የሆኑ አገልግሎት መስጫዎች ይገኛሉ:: በተቋሙ ውስጥ እነዚህን አገልግሎቶች የሚሰጡባቸውን ክፍሎች ከማኑዋል ወደ ኤሌክትሮኒክስ ዳታ ሪኮርዲንግ ሲስተም በመቀየር የመረጃ አያያዝና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን አዘምኗል:: ይህ የኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ወደ ሥራ ከገባ አንድ አመት ሆኖታል::

በአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የተመላላሽ ሕክምና ክፍል ኃላፊ አቶ ሳሙኤል ቶሎሳ ከማኑዋል ወደ ዲጂታል ሲስተም ከተቀየረ በኋላ የአሠራር ሥርዓቱ ምን እንደሚመስል የሰጡንን ማብራሪያ እንደሚከተለው አቅርበነዋል:: ታካሚዎች በሆስፒታል ውስጥ የተመላላሽ ሕክምና ክፍል፣ በተኝቶ ሕክምና ክፍል፣ በላብራቶሪ፣ እንዲሁም በፋርማሲ ውስጥ አገልግሎት ያገኛሉ::

የመጀመሪያው ታካሚዎች የሚስተናገዱበት በተመላላሽ ሕክምና አገልግሎት ክፍል ሲሆን ከዚህ ቀደም አገልግሎቱ ይሰጥ የነበረው በማኑዋል ሲስተም ነበር:: የተመላላሽ ሕክምና አገልግሎት በውስጡ ብዙ ከታካሚ ልየታ ጀምሮ፣ የካርድ መዝገብ ክፍል፣ የተመላላሽ ሕክምና መስጫ ክፍሎች አፒዲ፣ የሥነ-ተዋልዶ ሕክምና (ላይዘን)፣ የሕፃናትና ወጣቶችን ጨምሮ የሚያካትት ዘርፍ ነው::

ከዚህ ቀደም ታካሚዎች በማኑዋል በሚስተናገዱበት ወቅት የሚሰጣቸው ካርድ በመዝገብ ቤት የሚቀመጥ በመሆኑ የመጥፋት፣ የእያንዳንዱን ታካሚ መረጃ በቶሎ ለማግኘት መቸገር ነበር:: ምክንያቱም የሥነ-አዕምሮ ሕክምና የረጅም ጊዜ ክትትልን የሚፈልግ ሲሆን፣ ካርዱ በተደጋጋሚ በሚወጣበት ጊዜ የማርጀት፣ በቦታው ያለመቀመጥ ክፍተት፣ የአያያዝ ጉድለት ነበረበት:: ነገር ግን ሆስፒታሉ የዲጂታል ሲስተምን ካስተዋወቀ በኋላ መረጃን በሶፍትዌር አማካኝነት መውሰድና መመዝገብ እንዲሁም መረጃው በሚፈለግበት ጊዜ በቀላሉ አውጥቶ መጠቀም የሚያስችል እና ሙሉ ለሙሉ ከወረቀት የጸዳ ኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ተገንብቷል:: በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት ወደ ሆስፒታሉ የሚመጡ ታካሚዎች በስማቸው ፣ በስልክ ቁጥራቸው፣ በካርድ ቁጥራቸው መጠቀም እንዲቻል ተደርጓል:: የኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ወይንም የመረጃ አያያዝን ማዘመን በዋናነት ዘመናዊነትን ያላብሳል፣ ቅልጥፍናን ያመጣል::

ሲስተሙ ተግባራዊ ሲደረግም በእያንዳንዱ አገልግሎት ላይ ያመጣውን ለውጥ አብሮ ማየት ይቻላል:: በተመላላሽ ሕክምና የሚሰጡ እነዚህን አገልግሎቶች በዲጂታል ሲስተም ማድረግ በማነዋል ሲስተም ታካሚዎች በሚገለገሉበት ወቅት የነበረውን ከፍተኛ ወረፋ አስቀርቷል::

በተጨማሪም ይህ የዲጂታል ሲስተም ታካሚዎችም ሆኑ አገልግሎት ሰጪዎች በሚያስተናግዱበት እና በሚስተናገዱበት ወቅት የሚጠፋውን መረጃ አገልግሎት ለማግኘት የሚባክነውን ጊዜ አስቀርቷል:: አንድ ታካሚ ወደ ሆስፒታሉ መጥቶ ሕክምና ከማግኘቱ በፊት ካርዱን እስከሚያገኝ መጠበቅ፣ ወደ ፋይናንስ ክፍል ሄዶ መክፈል ረጅም ሰልፍ እና ሰዓት ይባክናል::

> **በሕክምና ተቋም ውስጥ ከማኑዋል ሲስተም የተላቀቀው ሌላኛው ክፍል የመድኃኒት ክፍል (ፋርማሲ) ነው:: ሲስተሙ ኮምፒዩተራዝድ ከመሆኑ በፊት ታካሚዎች መድኃኒት የሚታዘዝላቸው በወረቀት ነበር**

ይህ ሲስተም ታካሚዎች በአንድ ሲስተም ተስተናግደው ወደ ሚፈለገው አገልግሎት እንዲሄዱ የሚፈልጉትን ሕክምና በቶሎ እንዲያገኙ አድርጓቸዋል:: የመረጃ መጥፋትን እንዲሁ አስቀርቷል::

የመረጃና የመዝገብ አያያዝን ወጥ ማድረግና ማዘመን የታካሚዎችን የሕክምና ታሪክ በአግባቡ ለመሰነድ አስችሏል:: ከሕግ ተጠያቂነት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮችን አስቀርቷል:: ይህ ሲስተም መዘርጋቱ አንድ ታካሚ ከሕክምና ሥርዓት ውጪ ተመሳስለው የሚሠሩ ሕገ-ወጥ (ፎርጂድ ካርድ ማውጣት) አይችልም:: የመረጃ ደህንነትን አምጥቷል ፣ ሕገ-ወጥነትን ይከላከላል፤ ታካሚዎችን ከአድራሻቸው ጀምሮ እስከ የሕክምና ታሪካቸውን የሚገልጽ የግል መረጃ ምስጢራዊነታቸውን እንዲጠበቅ አድርጓል::

ከዚህ ቀደም የታካሚዎች የሕክምና ታሪክ በካርድ ክፍል አብሮ የሚቀመጥ ሲሆን የመጥፋት አደጋና በማይመለከታቸው ሰዎች እጅ የሚገባበት አግባብም ነበር:: አሁን ግን ይህ የዲጂታል ሲስተም በመዘርጋቱ ምክንያት ከሚመለከተው ባለሙያ ውጪ ማንም ሰው እንዳያየው አስችሏል::

ከዚህ ቀደም ሆስፒታሉ የነበረው የመረጃ አያያዝ በወረቀት ስለነበር የረጅም አመት ታሪክና መረጃ በሚከማችበት ወቅት ሰፊ ቦታን ይይዛል:: ይህ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝም ኮምፒዩተራይዝድ በመሆኑ በብዙ መጋዘን ሊቀመጥ የሚችለውን ሰብስቦ የመያዝ አቅም አለው::

ሌላኛው በሆስፒታሉ የሚሰጠው አገልግሎት የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት ነው:: እንደ አቶ ሳሙኤል ገለጻ የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት ስታንዳርድ ሰዎች በድንገተኛ ሕክምና ለመስተናገድ በሚመጡበት ወቅት በአምስት ደቂቃ ውስጥ ሕይወታቸውን ሊያተርፍ የሚችል ሕክምና ማግኘት እንዳለባቸው ያስቀምጣል::

የማኑዋል ሲስተም በነበረበት ወቅት ታካሚዎች ወደ ሆስፒታሉ ሲመጡ ካርድ ማውጣት፣ ገንዘብ መክፈል የሚባሉ ሂደቶችን ማለፍ ነበረባቸው:: በዚህ መሀል ማግኘት የሚገባቸውን ሕክምና በቶሎ ማግኘት ሳይችሉ ይቀራሉ:: በመሆኑም ይህ ክፍል ዘመናዊ ከሆነ በኋላ በድንገተኛ ሕክምና ለመስተናገድ የሚመጡ ታካሚዎችን ባለባቸው የሕመም ደረጃ ኮድ በማድረግ እንዲከፋፈሉ ያደርጋል:: በመሆኑም በድንገተኛ ሕክምና በጣም ከፍተኛ ሕመም የገጠማቸው ታካሚዎች በቀይ ቀለም የሚለዩ ሲሆን እንደየደረጃቸው ብርቱካናማ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ እያደረገ በመለየት ሐኪሙ ከልየታ ክፍል የሚመጣለትን ቅድሚያ መሰጠት ያለበትን ታካሚ እያስቀደመ እና አስፈላጊውን እርዳታ እያደረገ መረጃውንም በቀላሉ እንዲመዘግብ ያስችለዋል::

የዲጂታል ሲስተም መጀመሩ የድንገተኛ ክፍል ኦዲት ሥራውንም አሻሽሏል:: ከዚህም በተጨማሪ በድንገተኛ ክፍል አገልግሎት ውስጥ ሙያን መሠረት ያደረገ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጓል:: ይህም ማለት ታካሚዎች በሚመጡበት ጊዜ በጠቅላላ ሐኪም የሚታይ፣ በስፔሻሊስት፣ በሰብ ስፔሻሊስት የሚታዩ ታካሚዎች አሉ:: በመሆኑም ወደሆስፒታሉ በሚመጡበት ወቅት የልየታ ክፍል ባለሙያው በሲስተሙ አማካኝነት እየለየ በማስቀመጥ ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች ይልካል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘም ሲስተሙ ምን ያህል ታካሚዎች በየትኛው ክፍል እየታከሙ እንደሆነ እና ምን ያህል ደቂቃ እንደሚወስዱ በመለየት የተጠያቂነት ሲስተምን እንዲሁ መዘርጋት ችሏል:: ማኑዋል በነበረበት ወቅት የሕክምና ስህተት እንኳን ቢፈጠር በሌላ መረጃ አልያም ወረቀት መተካት ይቻላል:: በመሆኑም ይህ ሲስተም ተጠያቂነትን አረጋግጧል::

በሕክምና ተቋም ውስጥ ሌላኛው የአገልግሎት ክፍል የላቦራቶሪ ወይም የምርመራ አገልግሎት ነው:: ከዚህ ቀደም ታካሚዎች የታዘዘላቸውን ምርመራ አጽፈው የታዘዙትን ናሙና ሰጥተው ከላቦራቶሪ ክፍል ወደ ሐኪሙ እስከሚዘዋወር ድረስ ረጅም ሰዓትን ይጠብቃሉ:: አሁን ግን ምንም የወረቀት ንክኪ ሳይኖር የታካሚው የምርመራ ውጤት ከናሙና ክፍል ወደ ሠኪሙ ይላካል ሲስተሙ ለእያንዳንዱ ታካሚ የሚሰጠው መለያ ቁጥር በመኖሩ በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉና ጊዜንም እንዲቆጥቡ ያደርጋል:: ሌላኛው ከዚህ ቀደም በተለያየ ምክንያት በታካሚዎች መካከል የሚፈጠረውን የስም ስህተት ያስቀራል:: ከዚህም በተጨማሪ ሲስተሙ የታካሚዎችን መረጃ በሚፈለግበት ወቅት በቀላሉ ማግኘት ያስችላል::

በሕክምና ተቋም ውስጥ ከማኑዋል ሲስተም የተላቀቀው ሌላኛው ክፍል የመድኃኒት ክፍል (ፋርማሲ) ነው:: ሲስተሙ ኮምፒዩተራዝድ ከመሆኑ በፊት ታካሚዎች መድኃኒት የሚታዘዝላቸው በወረቀት ነበር:: ሰዎች ሕመም በተሰማቸው ጊዜ ትክክለኛውን ምርመራ ሳያደርጉ በሌሎች ባለሙያዎች መውሰድ አለብን ብለው ያሰቡትን መድኃኒት አስጽፈው ይወስዳሉ::

መድኃኒቱ በወረቀት ተጽፎ በሚታዘዝበት ወቅት ያልተሟላ የመድኃኒት ጽሕፈት እና ያልተሟላ መረጃ ያጋጥማል:: በመሆኑም ወደዚህ ሲስተም መቀየሩ መድኃኒት ማዘዝ የሚችሉት በሲስተሙ ላይ ስማቸው ተመዝግበው የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች ብቻ ሲሆን እነዚህን እና መሰል ችግሮችን እንዲሁም በዚህ ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የሕክምና ስህተት አስቀርቷል:: ይህ ሲስተም መፈጠሩ መድኃኒቱ ለሚመለከታቸው ታካሚዎች እንዲደርስ ከማድረግ እና የመድኃኒት ብክነትን ከማስቀረት ባሻገር ተጠያቂነትንም ያመጣል::

በሆስፒታሉ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ አያያዝ ውስጥ ከተካተቱ ክፍሎች የተኝቶ ሕክምና ሌላኛው ነው :: በተኝቶ ሕክምና ውስጥ ከዚህ ቀደም ለታካሚዎች የሚሆን ክፍት አልጋ የሚለየው በሚደረገው ቆጠራ ነው:: በተቋሙ ያሉ ክፍት አልጋዎችን በቀን ሦስት ጊዜ ባለሙያዎች በመዞር ቆጠራ ያደርጋሉ:: ነገር ግን ታካሚው በሌለበት አልጋዎች የሚያዙበት ልማድ በመኖሩ ትክክለኛው ቁጥር ላይታወቅ ይችላል::

ሲስተሙ በተቀየረ ጊዜ ግን የሕሙማን ቅበላ እና ስንብትን የሚቆጣጠረው ክፍል በየትኛው ክፍል ውስጥ ምን ያህል ታካሚ አለ፣ ምን ያህል ጊዜ ይቆያሉ ፣ መቼ ይወጣል ፣ ምን ያህል ክፍት አልጋ አለ የሚለውን መቆጣጠር እንዲችል አድርጓል:: ይህ መሆኑም አልጋን በትክክል ለሚያስፈልገው ሰው እና በቦታው ለሚገኘው ሰው እንዲውል አስችሏል:: ከዚህም ባሻገር ሲስተሙ በተኝቶ ሕክምና ክፍል ውስጥ ያሉ ታካሚዎች ያያቸውን ዶክተር፣ ነርስ ሰዓት እና ምን ያህል ጊዜ እንዳዩአቸው መድኃኒት የወሰዱበትን ሰዓት መዝግቦ ያስቀምጣል:: ይህም ታካሚው በትክክለኛው ባለሙያ መታየቱን የታዘዘለትን መድኃኒት ፣ በቀን ውስጥ መታየት ያለበትን ብዛት ለሚቆጣጠረው አካል ያረጋግጣል::

ይህ የዳታ ሪኮርዲን ሲስተም በየዕለቱ የሠራውን ሥራ መዝግቦ የሚይዝ የራሱ ዋና ሰርቨር ያለው ነው:: ይህ ሰርቨር አደጋ ቢደርስበት አልያም ቢበላሽ ተጨማሪ ተለዋጭ ሰርቨር አለ:: በተጨማሪም በተመረጡ ክፍሎች ላይ የየዕለቱ ዳታ በሀርድ ዲስክ ተወስደው ደህነታቸው በተጠበቀ ቦታዎች ላይ ይቀመጣሉ::

የአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ረጅም አመትን ያስቆጠረ በመሆኑ ወደ ኤሌክትሮኒክ ሜዲካል ሪከርድ መረጃዎችን ዘመናዊ በሆነ መልኩ በሶፍትዌር የመመዝገብ ሥራውን ሲጀምር ከዚህ ቀደም በኮምፒዩተር ተመዝግበው የነበሩ ዳታዎችን ወደዚህ ሲስተም የማምጣት ሥራ በቅድሚያ ተሠርቷል ::

በማኑዋል የተቀመጡ የታካሚዎችን መረጃዎች እንዲሁ በተመረጡ ባለሙያዎች ከታየ በኋላ የተመረጡ መረጃዎችን ወደ ሲስተሙ ለማስገባት ተችሏል:: ይህ መሆኑ አንድ የጤና ባለሙያ ታካሚው አስቀድሞ የነበረውን የሕክምና መረጃ በቀላሉ ለማወቅ ያስችለዋል::

ኤሌክትሮኒክ ሜዲካል ሪከርድ ሲስተም በሕክምና ተቋም ውስጥ መዘርጋቱ የሕክምና ሥርዓቱን ጤናማ፣ ፈጣን፣ ከአድሎና ከተለያዩ መጭበርበሮች የጸዳ ከማድረግ ባሻገር የኦዲት አድራጊውን አካል በአንድ ቦታ ሆኖ እንዲመዘግብ እና እንዲቆጣጠር ከማድረግ በዘለለ የመረጃ አያያዙንም አዘምኗል ::

በተቋሙ ምን ያህል ታካሚ ፣ ምን ያህል ሰው ወደ መድኃኒት ቦታ ሄዷል ፣ ምን ያህል ሰው በቀን ታይቷል ፣ ምን ያህል ሰው ተኝቶ ታክሟል፣ ምን ያህል ሰው ሞቷል የሚለውን ቁጥራዊ መረጃ በቀላሉ ለመያዝ ያስችላል:: ከዚህም በተጨማሪ በሕክምና ውስጥ አንዱ ስታንዳርድ የሆነውን የኦዲት ሥራን አሻሽሏል:: ሕክምናውን ለመስጠት በተቀመጠው ስታንዳርድ እና በተስማማባቸው መስፈርቶች ለመገምገም እና ለመከታተል አስችሏል:: ጊዜው የዲጂታል በመሆኑ ሲስተሙን እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው ባለሙያዎች በተቋሙ ውስጥና አቅራቢያ ሆነው በእጅ ስልካቸው መከታተል እንዲችሉም ቀላል አድርጎታል::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ሲያከብሩን እንከበር!

**ዋለልኝ አየለ**

በዚህ ሳምንት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ስም በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ሲታወስ ነበር:: በተለይም ‹‹ሲጂቲኤን›› የተባለው ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ሰፋ ያለ ሐተታ ሠርቶ ነበር:: ሌሎች ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ደግሞ ዜናውን ሠርተውታል:: ይህ ሁሉ ሲሆን የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያ ግን ያሏት የመገናኛ ብዙኃን የውጭዎችን ያህል እንኳን አልሠሩበትም:: በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቢሲ) በዓለም አቀፉ እንግሊዘኛ ቋንቋ የሠራውን ዜና ግን ማመስገን ያስፈልጋል::

ኬንያ የአንድ ፈጣን መንገድ የተሽከርካሪ መውጫ የኢትዮጵያ መሪ በነበሩት አጼ ኃይለሥላሴ ስም ሰይማለች:: ከዚህ በፊትም በኃይለሥላሴ ስም ጎዳና እንደሰየመች ሲነገር ቆይቷል:: ይህ የፈጣን መንገድ የተሽከርካሪ መውጫ ደግሞ የበለጠ የመታየት እና ልብ የመባል ዕድሉ ሰፊ ነው:: ጽሑፉ ከላይ በትልቁ ስለሚታይ በዚያ መንገድ ያለፈ ሁሉ “HAILE SELASSIE›› የሚለውን የእንግሊዘኛ ጽሑፍ ያነባል ማለት ነው:: ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩ መሆናቸውን ያስባል ማለት ነው:: በዚሁ አጋጣሚ ኢትዮጵያ ትታወሳለች ማለት ነው:: ሀገር የሚተዋወቀው ደግሞ በእንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ነው::

አፍሪካውያን ለአፍሪካውያን እንዲህ ሊተሳሰቡ ይገባል:: ኬኒያ ኢትዮጵያን ማክበሯ ያስከብራታል። ሊከባበሩ የሚገባቸው ራሳቸው የአህጉሪቱ ሀገራት ናቸው:: ራሱ ያላከበረውን ማንም ሊያከብርለት አይችልም:: ዳሩ ግን በአፍሪካ ውስጥ ይህ ሲደረግ ብዙም አይስተዋልም:: ይህ በመሆኑ ይመስላል ከአፍሪካ መሪዎች ውስጥ የነፃነት ታጋይ እና የመብት ተሟጋች የሌለ እስከሚመስል ድረስ የአፍሪካ መሪዎችን በሙሉ ጭራቅ አድርጎ የመሳል ትርክት ሥር ሰዷል::

ብዙዎቻችን የአፍሪካ መሪዎችን ከማድነቅ ይልቅ አንድ የምዕራባውያን አምባገነን መሪ ማድነቅ ይቀለናል:: ምዕራባውያን በጻፉልን ታሪክ ስለምንመራ የራሳችንን

**ለመሆኑ ግን እኛ ራሳችንን** አክብረናል? ውጭዎች ያከበሩልንን ያህል መሪዎቻችንን አክብረናል? እነርሱ የሰየሙትን ያህል ሰይመናል? የእነርሱን ያህል ውለታቸውን ዘክረነዋል?

ሰዎች ጭራቅ አድርገን የእነርሱን ደግሞ ቅዱስ አድርገን በልቦናችን ቀርጸናቸዋል:: እንደ ፓትሪስ ሉሙምባ ያሉ የነፃነት ታጋዮች የተገደሉት በእነ አሜሪካና እንግሊዝ ሴራ በቅኝ ገዥዋ ቤልጂየም ነው::

የቀድሞዋ ዛየር (በዛሬው ስሟ ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ) እንደ ፓትሪስ ሉሙምባ ያሉ የነፃነት ታጋዮች ነበሯት:: ዳሩ ግን ለበዝባዦቹ ምዕራባውያን አልተመቻቸውምና አስገደሉት:: እንዲህ አይነት የአፍሪካ መሪዎችን በማስወገድ የዛየርን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ለማጥረግረግ ተመቻቸው! ስለፓትሪስ ሉሙምባ የነፃነት ታጋይነት ከመናገር ይልቅ የዛየር አምባገነን መሪ ስለነበረው ሞቡቱ ሴሴ ሴኮ ብዙ ዘገባዎችን፣ ብዙ ትንታኔዎችን እና ብዙ ዘጋቢ ፊልሞችን ሠርተዋል::

እነርሱ ለጥቅማቸው ነውና በሚፈልጉት መንገድ አደረጉት እንበል! እኛ አፍሪካውያን ግን የራሳችንን ጀግኖች የማድነቅና የማመስገን ችግር አለብን:: በነገራችን ላይ አዲስ አበባ ውስጥ ፒያሳ ጊዮርጊስ አካባቢ በፓትሪስ ሉሙምባ ስም የተሰየመ አነስተኛ ሆቴል አለ:: እንዲህ በጥቂቱም ቢሆን መታወሳቸው ይበል የሚያሰኝ ነው:: ከስያሜ ባሻገር ግን አፍሪካ እንደነ ፓትሪስ ሉሙምባ ያሉ መሪዎች የነበሯትና ያሏት መሆኑ መታወስ አለበት::

እርግጥ ነው ብዙ የአፍሪካ መሪዎች አምባገነኖች ናቸው:: ሥልጣን የሚለቁት በተፈጥሮ ኃይል ወይም በመፈንቅለ መንግሥት ነው:: ዳሩ ግን ለዓለም አርዓያ የሚሆን ሥራ የሠሩትንም የሚያመሰግናቸው የለም:: ለምሳሌ፤ የታንዛኒያ መሪ የነበሩት ጁሊየስ ኒሬሬ ሥልጣን የለቀቁት በራሳቸው ፈቃድ ነው:: በ21ኛው ክፍለ ዘመን የዓለም የሥልጣኔ እና የዴሞክራሲ ቁንጮ ናት የምትባለው አሜሪካ ብዙ የምርጫ ማጭበርበር ሲወራባት፤ የአፍሪካዊቷ አገር ታንዛኒያ መሪ ጁሊየስ ኒሬሬ ግን በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ሥልጣን በራሳቸው ፈቃድ ለቀው ለዓለም ምሳሌ ሆነዋል::

ሆኖም ግን አፍሪካ ውስጥ የሚደረግን በጎ ነገር ማመስገን የማይቀናቸው ምዕራባውያን ጁሊየስ ኒሬሬን ያላመሰገኑ ኢዲ አሚን ዳዳን እንዲያመሰግኑ አይጠበቅም:: እነ ዘጋርዲያን ይሠሩት የነበረው ሰፋፊ ሐተታ፤ ኒሬሬ በአገሩ ሕዝብ የማይወደድ፣ ሶሻሊዝምን አሰርጻለሁ ብሎ ሀገሩን ድህነት ላይ እንደጣላት የሚያስመስል ነበር:: እውነታው ግን ኒሬሬን የሀገሩ ሕዝብ ‹‹ሙዋሊሙ›› እያለ ይጠራው እንደነበር ነው:: ሙዋሊሙ ማለት በእስዋሂሊ ‹‹መምህራችን፣ አባታችን›› እንደማለት ነው::

‹‹ዴሞክራሲ በራስህ አገር ዓውድ የምታዳብረው እንጂ እንደ ኮካ ኮላ ከውጭ የምትገዛው አይደለም›› በሚለው ንግግሩ የሚታወቀው ኒሬሬ ግን ሶሻሊዝምን እንደ ወረደ መቀበል ሳይሆን ከታንዛኒያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ያደረገ በመሆኑ በሀገሩ ሕዝብ ይመሰገናል::

እነ ኔልሰን ማንደላ፣ ኩዋሜ ኒኩሩማህ፣ ጆሞ ኬንያታ፣ ሴዳር ሴንጉር፣ ኬኔት ካውንዳ የመሳሰሉት የአፍሪካ መሪዎች የውጭ ወራሪን በመታገል ለአፍሪካ አገራት ነፃነት ውለታ የዋሉ ናቸው:: እንደነ ሳሞራ ማሼል፣ ሮበርት ሙጋቤ የመሳሰሉት በአገዛዛቸው አምባገነን የነበሩ ቢሆንም ሀገራቸውን ከውጭ ብዝበዛ ነፃ ለማድረግ ግን ሲጋፈጡና ሲታገሉ የነበሩ ናቸው:: እንደነ ቶማስ ሳንካራ የመሳሰሉት ‹‹አፍሪካዊ ቼ ጉቬራ›› የሚል ቅጽል ስም የሚሰጣቸው አብዮተኛ ነበሩ::

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የአፍሪካን ታሪክ የጨለማ ታሪክ፣ የአፍሪካን መሪዎች ጭራቅ መሪዎች ማድረግ የምዕራባውያኑ ዘላቂ ሥራ ነው:: አሳዛኙ እሱ አይደለም:: እነርሱ ገናና ሆነው ለመታየት ሌላው ዓለም የኋላቀር ወካይ መሆን ስላለበት ሥራቸው በሙሉ አፍሪካውያንን በሙሉ ማጠልሸት ነው:: የሚያሳዝነው ግን አፍሪካውያን ራሳቸው ለራሳቸው ክብር የማይሰጡ መሆኑ ነው::

አሁን ወደ ሀገራችን እንመለስ:: ኢትዮጵያ የአፍሪካ ገናና አገር ናት:: ይህ ‹‹ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ›› የሚባል አይደለም፤ ምክንያቱም ራሳቸው የአፍሪካ ሀገራት የሚመሰክሩት ነው:: ለዚህም ነው በመሪዎቻችን ስም ጎዳናዎችን እና የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰይሙት:: ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌት ናት:: ይህን የኢትዮጵያን ገናናነት ዓለም ያውቀዋል፤ የአፍሪካ ሀገራትም እነሆ እያከበሩን ነው::

ለመሆኑ ግን እኛ ራሳችንን አክብረናል? ውጭዎች ያከበሩልንን ያህል መሪዎቻችንን አክብረናል? እነርሱ የሰየሙትን ያህል ሰይመናል? የእነርሱን ያህል ውለታቸውን ዘክረነዋል?

ብዙ የሚያስተዛዝቡ ነገሮች አሉ:: መሪዎች በዘመናቸው ዘመኑ የሚፈቅደውን ከፉም ሆነ ደግ ነገር አድርገዋል:: ከመቶ ምናምን ዓመታት በፊት የነበሩ መሪዎችን ዴሞክራሲያዊ አልነበሩም ብሎ መውቀስ በጣም ሲበዛ የዋህነት ነው:: መሠልጠን ማለት ከዘመናት በፊት የነበሩ ነገሮችን በዘመኑ ዓውድ በማየት ዛሬ ላይ ያለውን መሥራት ነው:: ከዚህ በፊት የነበሩ ታሪካዊ ተሳትፎዎቻችንን ማክበር ለዛሬው ዲፕሎማሲ ትልቅ ዋጋ አለው:: ከዚህ በፊት የነበሩ ዓለም አቀፍ ተሳትፎዎቻችን ደግሞ በዘመኑ በነበሩ መሪዎች የተገኙ ናቸው::

የወቅቱን የኢትዮጵያ የብሽሽቅ ፖለቲካ ካስተዋልን ግን አንዱ የደገፈውን ሌላው መቃወም ግዴታ የሆነ ይመስላል:: እንዲህ አይነት ብሽሽቅ የሀገርን የውስጥ ገመና ለውጭ ኃይል ማጋለጥ ይሆናል::

ስለዚህ፤ ዓለም እያከበረን ነውና እኛም ራሳችንን እናክብር! ‹‹ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ›› የሚለው የአፍሪካ ኅብረት መሪ ቃል እርስ በርስ መከባበርን በማስቀደም ሊተገበር ይገባል።

# ዓስም አቀፍ

## ዓለምን እያሳሰበ የመጣው የኩፍኝ ወረርሽኝ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዓለም ጤና ድርጅት እና የአሜሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል (ሲዲሲ) እአአ ከ2023 መጨረሻ ጀምሮ የኩፍኝ በሽታ በልጆች ላይ የደቀነው ስጋት ቀጥሏል ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

የሁለቱ ተቋማት የጋራ መግለጫ የወጣው ለዓመታት በሽታውን ለመከላከል የሚውለውን ክትባት የሚወስዱ ሰዎች ማሽቆልቆሉን ተከትሎ ነው።

ሲዲሲ በድረ-ገጹ እንዳስታወቀው የኩፍኝ ወረርሽኝ በሁሉም የዓለም ክልሎች እየተከሰተ መሆኑን ነው። የመን፣ ሕንድ እና ካዛኪስታን የኩፍኝ ቫይረስ በብዛት የተሰራጨባቸው ሀገራት ናቸው።

የዓለም ጤና ድርጅት እና ሲዲሲ እንደሚሉት ከአውሮፓውያኑ 2021 ጋር ሲነጻጸር በ2022 የኩፍኝ በሽታ ተጠቂዎች ቁጥር በ18 በመቶ ሲጨምር፣ የሟቾች ቁጥር ደግሞ 43 በመቶ ከፍ ብሏል።

ይህም በኩፍኝ የተያዙ ሰዎችን ቁጥር ወደ 9 ሚሊዮን አሳድጎታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሕይወታቸው ያለፈው ደግሞ 136 ሺህ ሲሆኑ፣ ከእነዚህ መካከል አብዛኞቹ ልጆች ናቸው።

ባለፈው ዓመት አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ በአውሮፓ የኩፍኝ በሽታ በ30 እጥፍ መጨመሩን የዓለም ጤና ድርጅት ተናግሯል። እአአ በ2023 በአህጉሪቱ ከ30 ሺህ በላይ ሰዎች በቫይረሱ የተያዙ ሲሆን፣ በ2022 የነበረው ቁጥር 941 ብቻ ነው።

የኩፍኝ በሽታ ከቀላል እስከ ከባድ የጤና እክልን በታማሚዎች ላይ የሚያስከትል ከመሆኑ በተጨማሪ እስከ ህልፈት ሊያደርስ ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች እንደ ሳንባ ምች፣ የኢንሰፋላይትስ (የአንጎል እብጠት) እና ዓይነ ስውርነት ያሉ ከባድ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ።




ቫይረሱ የታመመ ሰው ሲያስል ወይም ሲያስነጥስ በሚለቀቁ ትንንሽ ፍንጣቂዎች ውስጥ ይገኛል። ጠብታዎቹ ባሉበት አካባቢ በመተንፈስ፣ ወይም እነሱን በመንካት በእጅ አማካይነት በአፍንጫ ወይም በአፍ በኩል ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፍ ይችላል።

የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች በቆዳ ላይ የሚወጣው ሽፍታ ከታየባቸው እስከ ከአራት ቀናት ድረስ ቫይረሱን ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

የዓለም ጤና ድርጅት፣ የአሜሪካው ሲዲሲ፣ የዩናይትድ ኪንግደም ብሔራዊ የጤና አገልግሎት (ኤንኤችኤስ) እና ሌሎች የጤና ባለሥልጣናት እንደሚሉት ኩፍኝ በጣም ተላላፊ በሽታ ነው።

በሲዲሲ አኃዝ መሠረት ሰዎች በሽታውን በተገቢው የመከላከያ መንገዶችን ተከትለው እራሳቸውን ካልጠበቁ ለቫይረሱ ከሚጋለጡ 10 ሰዎች መካከል 9 ያህሉ ይያዛሉ።

ኩፍኝን በሁለት ጊዜ በሚሰጥ ሚዝል፣ መምፕስ ኤንደ ሩቤላ (ኤም ኤም አር) በተሰኘ በኩፍኝ ክትባት መከላከል ይቻላል። ክትባቱ እነዚህን ሦስት በሽታዎች ይከላከላል።

የዓለም ጤና ድርጅት እንደሚለው ከሆነ በሽታው በብዛት በሚገኝባቸው ሀገራት የሚገኙ ሕጻናት 9 ወር ሲሞላቸው የመጀመሪያውን የኤም ኤም አር ክትባትን እንዲወስዱ ይመከራል። ሁለተኛው ደግሞ ብዙውን ጊዜ ከ15 እስከ 18 ወራት ሲሆናቸው መሰጠት እንዳለበት ይገልጻል።

“በ1963 [የኩፍኝ] ክትባት ከመጀመሩ እና በስፋት ከመሰጠቱ በፊት፣ በየሁለት እና ሦስት ዓመቱ ወረርሽኞች ይከሰቱ ነበር። በዚህም በየዓመቱ ወደ 2.6 ሚሊዮን የሚገመቱ ሰዎች ሕይወታቸው ያልፋል” ብሏል።

የዓለም ጤና ድርጅት አክሎም የሟቾች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በክትባቱ አማካይነት በጣም መቀነሱን “በ2021 በግምት 128 ሺህ ሰዎች በኩፍኝ ሞተዋል” ሲል አስታውቋል።

“አስተማማኝ እና ወጪ ቆጣቢ ክትባት ቢኖርም አብዛኞዎቹ ሟቾች ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ሕጻናት ናቸው” ብሏል።

ለትርፍ ያልተቋቋመ የአሜሪካ የጥናት ማዕከል የሆነው ማዮ ክሊኒክን ጨምሮ ሲዲሲ፣ ኤንኤችኤስ እና ሌሎችም ተቋማት እንደሚሉት፣ ድጋሚ የመያዝ አጋጣሚ በእጅጉ ዝቅተኛ ቢሆንም ዕድሉ ግን አለ።

የማዮ ክሊኒክ እንዳለው ከሆነ የመጀመሪያውን ክትባት ከወሰዱት ሰዎች ከ93 በመቶ በላይ የሚሆኑት ኩፍኝን የመከላከል አቅም አላቸው። ከሁለተኛው ክትባት በኋላ ደግሞ 97 በመቶው ከበሽታው ይጠበቃሉ።

የኩፍኝ ክትባት ስለመውሰዳቸው እርግጠኛ ያልሆኑ ሰዎች በደም ምርመራ ማረጋገጥ ይችላሉ።

በአሜሪካ በሽታውን የመከላከል አቅም የሌላቸው አዋቂዎች ቢያንስ አንድ ጊዜ ክትባቱን እንዲወስዱ ይመከራሉ።

በሽታው ያልያዛቸው ወይም ክትባቶቹን ወስደው የማያውቁ ሰዎች በአንድ ወር ልዩነት ሁለት ጊዜ መከተብ ያስፈልጋቸዋል።

እንደ ዓለም ጤና ድርጅት፣ ሲዲሲ እና ሌሎች የጤና ተቋማት ከሆነ ኩፍኝ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ሊያስከትል ይችላል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የመንግሥትን ጥረት ለመደገፍ ፈጥኖ ሊንቀሳቀስ ይገባል!

በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰተ የድርቅ አደጋ እና ግጭቶች የምግብ እህል እጥረት ማጋጠሙ የሚታወስ ነው። መንግሥት ችግሩን ለመፍታት ”አንድም ዜጋ የሚበላው አጥቶ መሞት የለበትም” በሚል ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ያሉትን አቅሞች አቀናጅቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

በዚህም ችግሩ የከብደቱን ያህል ጥፋት እንዳያስከትል ማድረግ ተችላል፤ በቀጣይም ችግሩ ዜጎችን ዋጋ እንዳያስከፍል በመንግሥት በኩል ዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ከማስተባበር ጀምሮ ሀገራዊ አቅሞችን አቀናጅቶ ችግሩን ለመከላከል የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው ቀጥለዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰሞኑን እንዳስታወቀው፤ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ የድርቅ አደጋ እና ግጭቶች ከጥር እስከ መጋቢት ወር 2016 ዓ.ም ድረስ 6 ነጥብ 6 ሚሊዮን ለሚጠጉ ወገኖች የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ደራሽ ርዳታ ያስፈልጋቸዋል።

ከዚህ ውስጥ የፌዴራል መንግሥት በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አማካኝነት ከጥር ወር 2016 እስከ የካቲት ወር 2016 ዓ.ም ለሚኖረው የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ደራሽ ዕርዳታ ምላሽ 500 ሺህ ኩንታል ስንዴ በመመደብ የቅድሚያ ቅድሚያ ምላሽ ለሚሹ ከ3 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ወገኖች ተደራሽ ያደርጋል ፡፡

ድጋፍ ከሚያስፈልጋቸው አጠቃላይ ዜጎች ውስጥ 4 ሚሊዮኑ በአፋር፣ ትግራይና አማራ ክልሎች እንዲሁም በኦሮሚያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ የድርቅ እና የግጭት አደጋ ተጎጂዎች ናቸው። 2 ነጥብ 6 ሚሊዮን የሚሆኑት በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች በጎርፍ፣ ግጭት እና የድርቅ አደጋዎች ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው ፡፡

ለአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ደራሽ ርዳታ የሚያስፈልገው የምግብ መጠን አንድ ሚሊዮን 118 ሺህ 700 ኩንታል ነው፣ ይህም በብር ሲሰላ 9 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የሚገመት ነው፡፡ እስካሁን ካለው ተጨባጭ እውነታ አንጻር ይህንን ሀብት በማፈላለግ ሂደት ውስጥ የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ሚና የጎላ እንደሚሆን ይታመናል ።

በርግጥ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም እስከ ታኅሣሥ ወር 2016 ዓ.ም ባሉት ስድስት ወራት ከመንግሥትና አጋር አካላት በተገኘ 15 ቢሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ ለሦስት ተከታታይ ዙሮች አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ድጋፍ ተደርጓል። ከዚህም ውስጥ አንድ ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል ምግብ በዓይነት እና ሁለት ቢሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብ የቀረበ ነው ፡፡

ከተሰጠው የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ደራሽ ዕርዳታ ውስጥ 77 በመቶ በመንግሥት /11ቢሊዮን ብር አካባቢ/ ፣ 23 በመቶ /4 ቢሊዮን ብር አካባቢ/ በአጋር አካላት የተሸፈነ ነው፤ ከተሠራጨው ሁለት ቢሊዮን ብር ውስጥ 40 በመቶ /2 ቢሊዮን ብር / በመንግሥት 60 በመቶው ደግሞ ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ የተሸፈነ ነው ፡፡

መረጃዎች መንግሥት ለችግሩ የቱን ያህል ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ በተጨባጭ የሚያሳዩ ፣ ሀገራዊ አቅሞችን አቀናጅቶ በመንቀሳቀስ ችግሩ እንደሀገር ሊያስከትል ይችል የነበረውን የከፋ አደጋ ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ እንደቻለ አመላካች ናቸው።

መንግሥት እስካሁን ባለው የርዳታ አቅርቦት ከ13 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ ለችግር የተጋለጡ ዜጎችን መታደግ ፣ በዚህም ለዜጎች ህይወት ያለውን ትልቅ ከበሬታ በተጨባጭ ማሳየት ፣ ቀደም ባሉት ጊዜያት በተመሳሳይ መልኩ የተከሰቱ ችግሮች ያስከተሉትን የከፋ አደጋ መቀልበስ ችሏል።

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ሆኖ የሠራቸው የልማት ሥራዎች እንደ መንግሥት ለፈጠረው ጥንካሬ ፣ እንደ ሀገርም ለተገኘው አደጋዎችን የመቋቋም ብሔራዊ አቅም ትልቅ መሰረት ሆነውታል። በቀጣይም ችግሩን ለዘለቄታው ለመቋቋም ለሚደረጉ ጥረቶች ዋነኛ ጉልበት እንደሚሆኑ ይታመናል።

ይህንን የመንግሥት አደጋ የመቋቋም አቅም በማሳደግ ሂደት ውስጥ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ከፍ ያለ ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት አስካሁን የሄደባቸው ርቀቶች የሚጠበቀውን ያህል አይደሉም።

የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ደራሽ ርዳታ በባህሪው ፈጥኖ መንቀሳቀስን የሚጠይቅ ከመሆኑ አንጻር፤ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ባልተገቡ ጉዳዮች ጊዜ ከመውሰድ መውጣት ፣ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት የሚያስችል ቁርጠኝነት ፈጥሮ ፈጥኖ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

በአጠቃላይ መንግሥት ”አንድም ዜጋ የሚበላው አጥቶ መሞት የለበትም ” በሚል ችግሩ ሰብአዊ ጥፋት ሳያስከትል ለመከላከል እያደረገ ያለውን ሁለንተናዊ ጥረት በሚጠበቀው ደረጃ በዓለም አቀፍ አጋሮች መደገፍ ይኖርበታል። ይህንን የማድረግ የሕግም የሞራልም ግዴታ አለበት!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከጩኸቶች በስተጀርባ …

ወጋሶ

መስማማት፣ መነጋገር፣ መወያየት፣ መመካከርና መሰል ቃላት፤ አንዳንድ አካላትን የሚያስቆጣቸው ለምን እንደሆነ አይገባኝም፡፡ በመስማማት ውስጥ እኩልነት፤ በመነጋገር ውስጥ መደማመጥ፤ በመወያየት ውስጥ መግባባት፣ በመመካከር ውስጥም መተዛዘን አለ፡፡ የእነዚህ ቃላት ተግባራዊ መሆን ሰላምን የማጽናት ያህል ነው፡፡ በተቃራኒው ሲሆን ግን ተደላድሎ መኖር ቀርቶ በሕይወት መቆየት በራሱ ያሳስባል፡፡

ከሰሞኑን ኢትዮጵያ ከራስ ገዟ ሶማሊላንድ ጋር የባሕር በር ማግኘት የሚያስችላትን የመግባቢያ ሠነድ ፈርማለች፡፡ ሰኞ ታኅሣሥ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ያከናወነችውን ስምምነት ተከትሎም በሚመለከታቸውም ሆነ በማይመለከታቸው አካላት በርካታ መግለጫዎች ወጥተዋል፡፡ እየወጡም ይገኛሉ፡፡ በተለይ ደግሞ በሱማሊያ በኩል ዛቻ አዘል መልዕክቶች ተደምጠዋል፡፡

እርግጥ ነው የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደኅንነት አማካሪ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን እንዳሉት፤ እነዚህ መግለጫዎች ተጠባቂዎች ናቸው፡፡ እጅግ ጎልተው ሲደመጡ የቆዩት እና አሁንም ድረስ እየተነገሩ ያሉ “የሱማሊያ ሉዓላዊነት ያሳስበኛል፤ የሱማሊያ ሉዓላዊነት መከበር አለበት፤ የሶማሊያ የግዛት አንድነት ሊጠበቅ ይገባል፤ ውጥረት እንዲረግብ ጥሪ አቀርባለሁ” የሚሉና የመሳሰሉ ናቸው፤ ከዚህ በተጨማሪ በቀጣናው ሀገራት መካከል ጠላትነትን ሊፈጥር እንደሚችል ብዙ እየተባለ ነው፡፡

የታሪክ መዛግብት እንደሚያመለክቱት፤ ኢትዮጵያ በዘመኗ የማንንም ሉዓላዊነት ተጋፍታ ሆነ ተዳፍራ አታውቅም፡፡ በዚህ በሰለጠነ ዘመን ደግሞ በጭራሽ አትሞክርም፡፡ እርግጥ ነው ሉዓላዊነቷን ለመዳፈር የቃጡትን በዓለም አቀፍ አደባባይ አሳፍራ መልሳለች ይህ የሚካድ አይደለም፡፡ ከዚህም ስጋት የተነሳ ብዙዎች እድገቷ ያስበረግጋቸዋል፡፡ ትልልቅ ውሳኔዎቿ ያቃዣቸዋል፡፡ ይበልጡኑ ደግሞ ለአህጉራችን አፍሪካ መልካም የሆነ አርዓያነቷ ሰላም ይነሳቸዋልና በሰበብ አስባቡ መተነኳኮሱን ተያይዘውታል፡፡

ወራሪም ሆነ ተወራሪም በሌለበት በስምምነት ለተከናወነ ሰነድ የዚያን ያህል ጩኸት ለምን አስፈለገ፤ የሶማሌ ላንድ ህዝብና መንግሥት ከማንም በላይ የሚጠቅመውን ያውቃል፤ ለዚህ አማክሩኝ፤ችግር አጋጠመኝ ድረሱልኝ ፤ ጩሁልኝ አላሉም።

ስምምነቱን ተከትሎ የሱማሊያ መንግሥት የተለያየ መግለጫዎችን አውጥቷል። መግባቢያ ሰነዱ ሕገ ወጥ ነው በሚልም ዓለም አቀፍ ድጋፍ ለማፈላለግ ሰፊ ጥረቶች እያደረገ ይገኛል፤ ይህ ቀጣናው ላይ ካለው የቆየ የፖለቲካ ባህል አንጻር ብዙ ሊያስብል የሚችል አይደለም፤ ተጠባቂ ነው።

ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነውና የሚያሳፍረው ግን፤ ከሀገራቸው ኢትዮጵያ በተቃራኒ የቆሙ አካላት መኖራቸው ነው፡፡ እነዚህ አካላት ስምምነቱን በአደባባይ ለመቃወም ሲወጡና ሲያብጠለጥሉ ከመስማት የበለጠ ምን አንገት የሚያስደፋ አሳፋሪ ነገር ሊኖር ይችላል? ይህ ክስተት በሀገሪቱ ታሪክ ፈጽሞ የሚታሰብ አይደም ።

የመግባቢያ ስምምነቱ መላውን ኢትዮጵያዊ ደስ ያሰኘ ለብዙ ጊዜ አንገት ካስደፋው እውነታ የሚወጣበት ነው። እንደ ሀገር አብዝቶ ሲመኙው የነበረው ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ነው ደስታውን መቆጣጠር አቅቷቸው አደባባይ ወጥተው ደስታውን ለመግለጽ የተገደዱት፡፡

ለነዚህ አካላት ከሀገር እና ከህዝብ ጥቅም ይልቅ የራሳቸው ጥቅም የሚቀድምባቸው ፤ከዚህ የተነሳም ከጠላቶቻችን ጋር አብሮ ለመስራት ሁለቴ ለማሰብ ያልታደሉ፤ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሀገርን አደጋ ውስጥ ለመክተት የማይመለሱ ናቸው። ይህ ባህሪያቸው ደግሞ በተጨባጭ ባለፉት ሶስት ዓመታት በአደባባይ ታይቷል።

ለጥቅማቸው ሲሉ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ጭምር ተባ‌ድነው በሀገር ጥቅም ላይ ሰልፍ የሚወጡ፤“ወደፊት!” ሲባሉ፤ “ወደኋላ!” ‹‹እንደግ›› ሲባሉ፤ እንፍረስ የሚሉ ናቸው፡፡ ከራስ ጥቅም ይልቅ የሀገርን ጥቅም ማስቀደም ፤ ሀገር ከሚኖራት ትሩፋት ከመቋደስ ባለፈ ለትውልድም መትረፍ መሆኑን ለመረዳት ፈቃደኛ ያልሆኑ ናቸው፡፡

ግራም ነፈሰ ቀኝ እድሜ ለሱማሊላንድ፤ አሁን መተንፈስ የሚያስችለን ባቡር ላይ ልንሳፈር ነው፡፡ ጉዳዩ በሰጥቶ መቀበል መርህ የተከተለ እንደመሆኑ መጠን ኢትዮጵያም በምትኩ ‹‹እንካችሁ!›› የምትላቸው የገዘፉ ስጦታዎች አሏት፡፡

> **ኢትዮጵያ** ግን ስውር ፍላጎት ያላቸው አካላት አይናቸው እያየ በሁለት እግሯ የምትቆምበት ጊዜ ቅርብ ነው፤ ይህም አይቀሬ ነው፡፡ ከየአቅጣጫው እየወጡ ያሉ መግለጫዎችም የአንድ ሰሞን ስለሆኑ መምከናቸው የግድ ነው

ታድያ ፈጣሪ የሰው ልጆች እንዲጠቀሙበት የተፈጥሮ ሀብት ዓለም አቀፉን ሕግን ተከትለን ለማደግ ስንደረደር ብዙዎቹን የሚዘገንናቸው ስለምንድን ነው? መቼስ በልተን ከማደር በዘለለ ጡንቻ ለማፈርጠም መንደርደራችን ከወዲሁ ገብቷቸው ስለሆነ በብርቱ እያሳሰባቸው መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ እንዲያ ካልሆነማ ‹‹ ከሱማሊላንድ ጋር ተስማማን›› ባልን ዕለት ልክ ‹‹ጦር ልንማዘዝ ነው›› ያልን ያህል ከወዲህ ወዲያ ጫጫታ የበዛ አይሆንም ነበር፡፡

ብዙዎች በዙሪያችን ያለውን የጋራ ሀብት ከምንጠቀምበት ይልቅ አይን አይኑን እያየን እንደ ቅርስ እንድናስተውለው ይፈልጋሉ፡፡ ቅርስ እንኳን ተጎብኝቶ ገንዘብ ያመጣል፤ የእኛ የባህር በር ማግኘት ማንንም የማይጎዳ ሆኖ ሳለ ስለምን እንደ ወራሪ ተመለከቱን ያስብላል፡፡ ኢትዮጵያ በእጅ አዙር እንጂ በራሷ መተንፈስ ካቆመች ሶስት አስርት ዓመት ተቆጥሯል፤ ይህን ልብ ልንል ይገባል፡፡

ቀደም ባሉ ጊዜያት በርካታ ስምምነቶችን ማድረጋችን ይታወሳል፡፡ እንዲያውም ከዚህቺው ሱማሊላንድ ጋር ከወደብ ጋር ተያይዞ ስምምነት ፈጽመናል፡፡ ምነዋ ያኔ ይህ ሁሉ መወናጨፍ አልተፈጠረ?! የአሁኑ የተለየው ለምን ይሆን? ስምምነቱን በአንክሮ፣ በጎሪጥ በጥብቅ፣ በጥንቃቄ በምናምን እየተከታተልነው ነው ማለታቸውስ የበዛው ስለምንድን ነው? ይህንን ለእናንተው ለአንባቢያን ትቼዋለሁ፡፡

ኢትዮጵያ ግን ስውር ፍላጎት ያላቸው አካላት አይናቸው እያየ በሁለት እግሯ የምትቆምበት ጊዜ ቅርብ ነው፤ ይህም አይቀሬ ነው፡፡ ከየአቅጣጫው እየወጡ ያሉ መግለጫዎችም የአንድ ሰሞን ስለሆኑ መምከናቸው የግድ ነው፡፡ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን በቂ ነው።

በስምምነቱ ላይ ያልተገቡ ድምጾችን የሚያሰሙ ኢትዮጵያውያንም የሀገራቸው እድገት የማይቀር መሆኑን በአይናቸው ማየታቸው ስለማይቀር የሚያፍሩበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ፡፡ ከዚህ በኋላ ሀገራችን የማደግ አማራጮቿ ብዙ ናቸው፤ ከእድገትና ልማቷ የሚገታት አይኖርም፡፡ ብትችሉ ኢትዮጵያ ከተያያዘችው የልማት ባቡር ላይ ተሳፈሩ፤ ‹‹ልማት ፣እድገት፣ ብልጽግና…ወዘተ አይመቸኝም›› የምትሉ ከሆነ ደግሞ ከመንገዷ ላይ ዘወር በሉ፡፡

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም
ጋር በመተባበር በየሣምንቱ የሚታተም

# ለ359 ቅሬታ አቅራቢዎች ፍትሕ የሰጠው የተቋሙ መፍትሔ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ ቁጥር 1142/2011 በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት ወደ ተቋሙ ቀርበው የአስተዳደራዊ በደል ተፈጾመብን የሚሉትን ዜጎች አቤቱታቸውን ተቀብሎ በመመርመር ተገቢውን የመፍትሔ ሃሳብ ይሰጣል። በዚሁ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረትም በየጊዜው ወደ ተቋሙ የሚመጡ በርካታ የአስተዳደር በደል ቅሬታዎችን ተቀብሎ በመመርመር የመፍትሔ ሃሳቦችን ሲሰጥ ቆይቷል:: በመስጠት ላይም ይገኛል::

በዛሬው እትማችን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም እነ አምረላ መሀመድ(3 ሰዎች) እና በእነ ዮናስ ጉተማ(356 ሰዎች) በቀረበ አቤቱታ ላይ ምርመራ በማድረግ እና ተጠሪ የሆነውን የኢፌዴሪ ጉምሩክ ኮሚሽን ምላሽ መሠረት በማድረግ የሰጠውን የመፍትሔ ሃሳብ እንደሚከተለው አዘጋጅተን አቅርበናል።

አቤት ባዮች ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ.ም ለተቋሙ ባቀረቡት አቤቱታ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ለንግድ የማይውሉ ወደ ሀገር የሚገቡ የግል መገልገያዎች ቀረጥና ታክስ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 51/2010 ባልተሻረበት ከ2010 ዓ.ም እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ለአራት ጊዜ ህግን በመጣስ በቃለ ጉባኤ በመወሰን ተጓዦች ከህግ ውጪ ቀረጥ እየተጣለብን ነው:: እቃዎችና አልባሳት እየተወረሱብን ነው:: ያለአግባብ ሪከርድ ውስጥ በማስገባት 200 በመቶ ቅጣት በመጣል እና ተጓዦችን ተመላላሽ ነጋዴ አድርጎ በመውሰድ በህግ የተሰጠንን የቀረጥ ነጻ መብት ያሳጣን እና አስተዳደራዊ በደል የተፈጸመብን በመሆኑ ጉዳዩ ተጣርቶ በመመሪያው እንድንስተናገድ መፍትሔ ይፈለግልን በማለት አመልክተዋል::

ተጠሪ የሆነው የኤፌዴሪ ጉምሩክ ኮሚሽን በቁጥር 7/0237/7 የካቲት 3 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ጥር 27 በቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር 07/07/291/14 በተጻፉ ደብዳቤዎች ለተቋሙ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ምላሹም፤

የእነ አምረላ መሀመድ አቤቱታን አስመልክቶ እንደ ኮሚሽን ተገልጋዮቻችን አቤቱታ የሚያቀርቡበትና የሚታይበት ግልጽ የሆነ አሰራር ማለትም በአንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ካስተላለፈው የስራ ክፍል አንስቶ በየደረጃው እስከ ዋናው መስሪያ ቤት ድረስ ባሉ የአቤቱታ አጣሪ ጽህፈት ቤቶች አቤቱታ ቀርቦ በየደረጃው መታየት እየቻለ ግለሰቦቹ ያደረባቸውን ቅሬታ ለሚመለከተው የሥራ ክፍልም ሆነ የሥራ ኃላፊ ያላቀረቡ በመሆኑ ጉዳዩ በዝርዝር ታይቶ ባለው አሰራርና መመሪያ መሰረት ተጣርቶ ውሳኔ መስጠት እንዲቻል ጉዳዩ ላይ ሂደቱን በተከተለ መልኩ አቤቱታ መቅረብ ቢችልና በየደረጃው ውሳኔ መስጠት የሚቻል መሆኑን ገልጿል::

እንደ አጠቃላይ መመሪያ ቁጥር 51/2010 ጋር በተያያዘ የመመሪያው መውጣት ያስፈለገበት ምክንያት ከመመሪያው መረዳት እንደሚቻለው መንገደኞች ይዘዋቸው ከሚመጡት “የግል መገልገያ” እቃዎች የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ላይ ወጥ አሰራር፣ ወጥ የታሪፍ ምጣኔ ተፈጻሚ ለማድረግ እንዲሁም ለመንገደኞች ፈጣን መስተንግዶ ለመስጠት ታስቦ እንደሆነና የመመሪያው ተፈጻሚነት ወደ ሀገር በሚገቡና በሚወጡ የግል መገልገያ እና ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያዎች ሆነው ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ መሆኑ ነው:: በአጠቃላይ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 2(24) እንደተገለጸው በመንገደኞች መግቢያና መውጫ በኩል የመንገደኛውና የቤተሰብ የግል መገልገያ ካልሆነ በቀር ለንግድ አላማ ሊውል በሚችል እቃ በህግ በተደነገገው አግባብ እየተሰራበት እንደሚገኝና በቀጣይም ያለ ሕጋዊ ንግድ ፍቃድ በመንገደኞች መተላለፊያ በተደጋጋሚ ምልልስ በማድረግ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩትን መቆጣጠር በሚቻልበት መንገድ ላይ የመመሪያ ማሻሻያ ማድረግ እንዲችሉ

> በመመሪያ ቁጥር 51/2010 አባሪ ሰንጠረዥ ተራ ቁጥር 19፤ በአልባሳትና ጫማ ላይ የተሰጠው የታክስ ነጻ መብትና ለንግድ አላማ የማይውሉ የግል መገልገያን አስመልክቶ በቀረጥ እንዲያስገቡ የተፈቀደውን መብት ጉምሩክ ኮሚሽን አክብሮ እንዲሰራና በቃለ ጉባኤ እየተወሰነ የሚሰራበት አሰራር ሕግን የጣሰ ተግባር ስለሆነ በአስቸኳይ እንዲቆም የሚል መፍትሔ ሃሳብ ተሰጥቷል

ግብዓት ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ የተላከ እና የህግ ማሻሻያም እየተደረገ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል::

የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምም የአቤት ባዮችን አቤቱታ እና የተጠሩ መስሪያ ቤትን ምላሽ መሰረት በማድረግ ለአቤት ባዮች በመመሪያ የተሰጠው የታክስ ነጻ መብት ተጥሷል ወይስ አልተጣሰም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምሯል::

ተቋሙ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ተገቢውን የመፍትሄ ሀሳብ ለመስጠት ያስችለው ዘንድ የአቤት ባዮችን አቤቱታ፣ ከተጠሪ መስሪያ ቤት ምላሽ እና ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያለውን ህግ ተመልክቷል:: ተቋሙ ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት ያለው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 24:52:54 የጉምሩክ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 10(2)፣ 32(1-6) የጉምሩክ 137/2011 አንቀጽ 5(15)፣ መመሪያ ቁጥር 51/2010፣ መመሪያ ቁጥር 59/2012 የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሰራተኞች መመሪያ እና የፌዴራል የአስተዳደር ስነ-ስርዓት ህግ አዋጅ ቁጥር 183/2012 አንቀጽ 16፣19 መሆኑን ግንዛቤ ወስዷል::

አቤት ባዮች የግል መገልገያ ነጻ የታክስ መብትና ለንግድ አላማ የማይውሉ የግል መገልገያ በቀረጥ ማስገባት መብት በሌላ መልኩ ወጥ የሆነ ታሪፍ ምጣኔ አወሳሰን የመመሪያው አንቀጽ 7(1) በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ “መ“ እና “ረ” መሰረት የሚገቡ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ እቃዎች ወጥ በሆነ የታሪፍ ምጣኔ መሰረት ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው ወደ ሀገር ውስጥ ይገባሉ:: (2) ለንግድ የማይውሉ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የግል መገልገያ እቃዎች የቀረጥ ምጣኔ በጉምሩክ ታሪፍ ምዕራፍ 98 መሰረት ይስተናገዳሉ:: (3) ባለስልጣኑ አጠቃላይ የዋጋ አተማመን መርህ ጋር በማጣጣም ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ እቃዎችን ዝርዝር የመነሻ ዋጋ ያዘጋጃል::

አንቀጽ 8 ወጥ በሆነ የታሪፍ ምጣኔ የማይስተናገዱት ባለመብቱ ለቤተሰቡና ለራሱ ጥቅም ሊያውለው ከሚችለው መጠን በላይ በተደጋጋሚ የሚያመጣቸው በስጋት ሥራ አመራር ከትትል የሚያዙ እቃዎች፣ ለንግድ ሊውሉ የሚችሉ እቃዎች እና ለንግድ የማይውሉ ተብሎ በሰንጠረዡ ከተዘረዘረው መጠን በላይ ያለፉ ዕቃዎች አስመልከቶ የተፈጠሩ ከፍተቶች በመመሪያው አንቀጽ 8(1-3) እንዲገዙ ማድረግ እየተቻለ አለመደረጉ በህግ ረገድ አግባብ አይደለም::

ሌላው የኤርፖርት ጉምሩክ በመመሪያው አንቀጽ 10 በሰንጠረዡ ያልተካተቱ ለግል መገልገያነት የሚውሉ ወይም ለንግድ የማይውሉ መገልገያ እቃዎች ሲመጡ ውሳኔ መስጠት እንደሚችል ያስቀምጣል:: ይህ ሲባል በመመሪያው በግልጽ የተመለከተውንና በሰንጠረዥ 19 የተገለጸውን ነጻ የታክስ መብት ለንግድ አላማ የማይውሉ የግል መገልገያዎችን ማለት አይደለም::

የፌዴራል የአስተዳደር ስነ-ስርአት ህግ አዋጅ ቁጥር 183/2012 አንቀጽ 16፣19 ማንኛውም መመሪያ በተገልጋዮችና በባለ ድርሻ አካላት ግብዓት ተሰጥቶበትና ግልጽ ውይይት ተደርጎበት እንደሚጸድቅና በፍትህ ሚኒስቴር ስር በሚገኘው ጠቅላይ አቃቤ ሕግ በህግ ማርቀቅና ማስረጽ ዳይሬክቶሬት በኩል መመዝገብ እንዳለበት የሚደነግግ ስለሆነ በኤርፖርት ጉምሩክ የተሰራበት ቃለ ጉባኤ የህግ አካል ሆኖ ሊወሰድ እንደማይገባና በዚህም አግባብ ሪከርድ ውስጥ የገባ ተጓዥም ካለ ተገቢነት የለውም::

ስለሆነም በመመሪያው በሰንጠረዥ “ሆ” የእቃው አይነት፣ ሰንጠረዥ “ለ” መለኪያ(በቁጥር፣ ሴት/ወንድ፣ በደርዘን፣ ኪሎ፣ በሜትር፣ ሊትር/ሚሊሊትር በካሬ..) ለመንገደኞች(ሰንጠረዥ “ሐ” ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያዎች ብዛት፣ ሠንጠረዥ “መ” ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት) ለተመላሽ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ለማገልገል በስምምነት ለሚመጡ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም የውጭ ሀገር ዜጎች(ሰንጠረዥ “ሠ” ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚፈቅድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት ሰንጠረዥ “ረ” ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት) በመመሪያው አባሪ በሰንጠረዥ የተመለከተ ሲሆን በመመሪያው አባሪ ሰንጠረዥ ቁጥር 19 ጨርቃ ጨርቅ አልባሳትና ጫማ መጠኑ ምንም ያህል ቢሆን መንገደኞች ሲወጡና ሲገቡ መያዝ እንደሚችሉ መመሪያው ነጻ መብትን እና ለንግድ አላማ የማይውሉ የግል መገልገያዎችን በሰኝጠረዡ በተገለጸው መጠን ልክ በቀረጥ የማስገባት መብትን የፈቀደ ሆኖ እያለ ተመላላሽ ነጋዴ ናቸው በሚል ይህ መብት መገደቡ አግባብነት የለውም::

በአቤት ባዮች ከቀረቡ ማስረጃዎች አንጻር ኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ታህሳስ 19 ቀን 2011 ዓ.ም የቃለ ጉባኤ ማሻሻያ በመመሪያ ቁጥር 51/2010 የተዘጋጀ አልባሳት መጠኑ ባለመጠቀሱ ሳይመዘገብ የሚለቀቅ፣ ለመጀመሪያ ተመዝግቦ የሚለቀቅ የንግድ መጠን ያላቸው ሆኖ በቅጣት የሚስተናገዱ በአይነትና በቁጥር ገደብ በማስቀመጥ፣ የንግድ መጠን ያልወጣባቸው እቃዎችን ይመለከታል በሚል ካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም ጫማና አልባሳት ለንግድ አላማ የማይውሉ ከማለት ውጪ መጠን ባለመገለጹ ንግድ ፍቃድ አውጥተው ከሚነግዱ ነጋዴዎች ቅሬታ የቀረበበት በመሆኑ በሚል፣ በጥር 20 ቀን 2012 ዓ.ም የጸደቀ ቃለ ጉባኤ ሙሉ ሱፍ ፣ቬሎና የሚዜ ልብስ ማንኛውም አልባሳትና ጫማ በጥቅል፣ በቁጥር፣ በሪከርድ የሚስተናገድ፣ በቅጣት የሚስተናገድ የውርስ ውሳኔ የሚተላለፍባቸውና አግባብ ባለው የወንጀል ህግ የሚታይ በማለት ከመመሪያው ውጪ አሰራር የዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም በቀን ህዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም ባወጣው ማስታወቂያ ምንም አይነት እቃ አልባሳትና ጫማን ጨምሮ ይዞ መምጣት የተከለከለ መሆኑንና ይዞ የሚመጣ ካለ በሕግ የሚጠየቅ መሆኑ በማስታወቂያ የተገለጸበት አግባብ በቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል::

በኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት በቀን የካቲት 2 ቀን 2014 ዓ.ም በውይይት ወቅት በተነሳው ፓስፖርት እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በመቀያየር በብሄራዊ ባንክ መምጣት ያለበትን የዶላር ምንዛሪ መንግሥትን በማሳጣት በሀዋላ እንዲላከላቸው በማድረግ በወር ውስጥ እስከ አራት ጊዜ ቱርክና ዱባይ ምልልስ በማድረግ በመንገደኛ መግቢያ መውጫ ተርሚናል ለንግድ አላማ የሚውል እቃ ይዘው መገኘታቸውና ሪከርድ ውስጥ በመግባታቸው ተመላላሽ ነጋዴ የሚያስብላቸው መሆኑ በውይይት የተገለጸ ሲሆን ነገር ግን በማስረጃ የተደገፈ ሆኖ አልተገኘም::

ሌላው በውይይት ወቅት የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት በመመሪያው አንቀጽ 11 መሰረት በመስራት ላይ እንዳለ የገለጸ ቢሆንም ይህ አንቀጽ የታክስ ነጻ መብትንና ለንግድ አላማ የማይውሉ የግል መገልገያዎችን የሚመለከት ሳይሆን በመመሪያው በታክስና በቀረጥ እንዲስተናገዱ ከተፈቀደው በላይ ወይም ለንግድ የሚውል እቃን በመንገደኛ መግቢያና መውጫ ወይም በሌላ ሁኔታ ያለአግባብ በተደጋጋሚ ለማሳለፍ ሲሞክር በክትትል የተያዘን ተጓዥ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል:: በአጠቃላይ የተጓዦች አቤቱታ ከህግና ከቀረቡ ማስረጃዎች አንጻር ሲመዘን በመመሪያው ለመንገደኞች የተሰጠን የታክስ ነጻ መብት ኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አክብሮ ያለመስራት ህግን የጣሰ ተግባር በመሆኑ አስተዳደራዊ በደል መፈጸሙ ተረጋግጧል::

የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምም በምርመራው ያገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ ተገቢ ነው ያለውን የመፍትሄ ሃሳብ በሚከተለው መልኩ አስቀምጧል::

በመመሪያ ቁጥር 51/2010 አባሪ ሰንጠረዥ ተራ ቁጥር 19፤ በአልባሳትና ጫማ ላይ የተሰጠው የታክስ ነጻ መብትና ለንግድ አላማ የማይውሉ የግል መገልገያን አስመልክቶ በቀረጥ እንዲያስገቡ የተፈቀደውን መብት ጉምሩክ ኮሚሽን አክብሮ እንዲሰራና በቃለ ጉባኤ እየተወሰነ የሚሰራበት አሰራር ሕግን የጣሰ ተግባር ስለሆነ በአስቸኳይ እንዲቆም የሚል መፍትሔ ሃሳብ ተሰጥቷል:: ተጠሪ መስሪያ ቤቱም በመፍትሔ ሃሳቡ መሰረት ክፍተቶችን አርሞ እርምጃ ወስዷል::

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ዛሬን በተስፋ - ነገን በስጋት



**መልካምሥራ አፈወርቅ**

በአካባቢው ያለገደብ የሚጮኸው ድምጽ አዲስ ለሆነ ጆሮ ይፈትናል:: ማሽኖች ያለአፍታ ይዘወራሉ፣ አፈር ዝቀው የሚወጡ ፣ጉድጓዱ ጠልቀው የሚምሱ መኪኖች ለአፍታ ሥራ አይፈቱም:: አቧራው ፣ሲሚንቶው፣ አሸዋና ድንጋዩ ከጠንካራ እጆች ገብተዋል:: ሁሉም በየፈርጁ ከተግባር ውሎ እየተጣደፈ ነው::

ባሬላ ይዘው ከላይ ታች የሚሮጡ፣ ፌሮ ቆርጠው የሚያስሩ፣ ድንጋይ በመዶሻ የሚቀጠቅጡ ብርቱዎች ብዙ ናቸው:: ሁሉም ስላደፉ ልብሶቻቸው፣ ስለቆሸሹ እጆቻቸው ደንታ የሰጣቸው አይመስልም:: አንዳቸው ሌላቸውን ሳያዩ የድርሻቸውን ይወጣሉ::

ስፍራው አመድ መስለው፣አመድ ልሰው ለእንጀራቸው የሚሮጡ የቀን ሰራተኞች መገኛ ነው:: ለእነሱ ፊታቸውን በጨርቅ፣ ራሳቸውን በሰሌን ባርኔጣ ከልለው መጣደፍ ብርቅ አይደለም:: በየቀኑ፣ በየሰአቱ ሲደክሙ፣ ሲባትሉ ይውላሉ:: በዚህ እውነታ ካሉቱ ባሻገር በጠዋቱ የግንባታውን አጥር ተደግፈው ሥራ ለመግባት በጉጉት የሚጠብቁ ሌሎች ትኩረት ይስባሉ:: አብዛኞቹ ከወዲያ ወዲህ ዓይናቸው ይንከራተታል:: ጆሯቸውን ጥለው ከአሁን አሁን ለመቀጠር መጠራታቸውን ይጠባበቃሉ:: በየጊዜው የውስጡና የውጪ ገጽታ በተቃርኖ ይተያያል::

አሁንም ከግንባታው መንደር ነኝ:: ጆሮዬን ዘልቆ የሚያልፈው ሀያል ድምጽ አእምሮዬን ያሸነፈ እስኪመስለኝ ደንዝዣለሁ:: አቧራው ይጨሳል፣ ሲሚንቶ ፣ ድንጋዩ ፣ አሸዋ ጠጠሩ ይራገፋል:: ሰራተኞቹ እረፍት የለሽ ናቸው:: ከወዲያ ወዲህ ይሮጣሉ፣ ይራወጣሉ::

ዙሪያቸው በህንጻዎች የተከበቡ ጅምር ፎቆች ከሚበልጧቸው ግዙፋን ጋር ፉክክር የያዙ ይመስላል:: በየቀኑ ቁመት እያከሉ ፣ያድጋሉ:: ወርዳቸው እየሰፋ፣ ቅርጻቸው ይለወጣል:: እንጨታቸው እየተነሳ ዲዛይናቸው ይታያል::

አላፊ አግዳሚው የሚደመምበትን ይህን ለውጥ በስጋት የሚያስተውለው ጎልማሳ ዛሬም ትካዜ ላይ ነው:: የዚህ ሰው እሳቤ ከሁሉም ይለያል:: ለእሱ የህንፃዎቹ ዕድገት የሚሰጠው ትርጉም ሌላ ነው:: አንዳንዴ ስራው ተቋርጦ ዝምታ ቢወርሰው ይመርጣል::

አንዳንዴ ደግሞ እንደቀድሞ አረፍ እያሉ የሚቀጥሉትን አይነት ሥራ ይመኛል:: ይህን ሲያስብ የጎን ጥቅሙ ይፈትነዋል:: ስራው ቢኖር በገንዘብ ይጠቀማል:: ባይኖር ደግሞ ገቢውን ያጣል:: ይህን ይተውና ልቡ ወደፊት ወደኋላ ይመላለሳል:: መልሱን ሲያገኘው አይዘገይም:: ሚዛኑ «መኖር» ከሚሉት እውነት ላይ ያሳርፈዋል:: ይህኔ ሀሳብ፣ ትካዜው ይጨምራል::

እነዚህ ግንባታዎች እስከዛሬ ለእሱና ለቤተሰቡ የጀርባ አጥንት ነበሩ:: በእነሱ እንጀራውን ቆርሷል፤ ልጆች አሳድጓል:: የህንጻዎቹ መቆም ለመኖሩ ምክንያት ሆኖም ዓመታትን ተሻግሯል:: ዛሬ ግን አባወራው ነገውን እያሰበ መጨነቅ ከያዘ ከራርሟል:: ጭንቀቱ ደግሞ አንዳንዴ እንደሚሆነው ልማድ አይደለም:: ጭንቀቱ ስር ሰዷል::

ከሚገነቡት ህንጻዎች የአንዱን ግድግዳ ተደግፎ ከሚተክዘው ዘውድነህ አጠገብ ደርሻለሁ:: በልዩ ትህትናው ተቀብሎኝ የልቡን እያወጋኝ ነው:: እሱ መነሻውን አይረሳም:: ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰ ያውቃል:: ዘውድነህ ዓመታትን በዚህ ስፍራ ሲቆይ በብዙ የህይወት ጎዳናዎች ተመላልሶ ነው::

### ትናንትን በትውስታ

ገና ጨቅላ ሳለ ወላጅ እናቱን በሞት ያጣው ህጻን ከፍ ሲል የሚሰማው ወሬ ይረብሸው ይዟል:: እናቱ እሱን ሲወልዱ ስለመሞታቸው የሚነግሩት ሰዎች ለስሜቱ መጠንቀቅ ልምዳቸው አይደለም:: እንዳመጣላቸው ታሪኩን እየነገሩ ያሳዝኑታል፤ያስለቅሱታል::

ዘውድነህ እውነቱን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ ፈገግታው ደምቆ አያውቅም:: በገዛ እጁ እናቱን የገደለ እስኪመስለው ራሱን ይወቅሳል:: ይህ ስሜት አብሮ ማደግ ቢጀምርም ውስጡን ያወቀለት ወዳጅ ዘመድ አልነበረም:: ከእኩዮቹ ተነጥሎ በብቸኝነት ሲቆዝም የሚያዩት ብዙ ናቸው::

አንድ ቀን የአባቱ ታላቅ እህት ከአዲስ አበባ ወደእነሱ መንደር ዘለቁ:: ከልጅነቱ ስለኑሮ ህይወታቸው የሚሰማው ታሪክ ጆሮውን ሲያነቃው፣ ልቡን ሲማርከው ቆይቷል:: አሁን ደግሞ በዕድሜው ከፍ ያለበት ጊዜ ነው:: አክስቱን ቀረብ ብሎ አወራቸው:: ጨዋታው ከቀድሞው የተለየ ነበር::

ከቀናት በኋላ አክስት ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ:: ዘውድነህ ከእሳቸው የሰማው የከተማ ኑሮ በህልም በእውኑ ሲመላለስበት ከረመ:: አብሮት ካደገው ብቸኝነት የሚገላገለው ቀዬውን ርቆ መውጣት መሆኑን ካመነበት ቆይቷል:: ይህ ፍላጎቱ የሚሞላው በአንድ መንገድ ብቻ ነው:: አክስቱን ተከትሎ በመሄድ ብቻ::

ከወራት በኋላ የዘውድነህ አክስት ተመልሰው መጡ:: ይህ ጊዜ ለዘውድነህ የውሳኔና የቁርጥ ቀን መጨረሻ ሆነ:: ቀድሞ ያሰበው የነበረውን ጉዳይ አሳውቆ ጓዙን ሸክፎ ተነሳ:: አክስቱ ሊከለክሉት አልወደዱም:: ታዳጊውን የወንድማቸውን ልጅ አስከትለው አዲስ አበባ ተመለሱ::

### አዲስ አበባ ...

አዲስ አበባና ዘውድነህ ለመላመድ ጊዜ አልፈጁም:: የከተማ ህይወት ለገጠሩ ልጅ አዲስ ቢሆንም እንግድነቱ ሳይከርምበት ሁሉን ፈጥኖ ተላመደ:: ውሎ አድሮ አክስቱ ትምህርት ቤት አስገቡት:: ደብተር ይዞ ቀለም መቁጠር ጀመረ:: ትምህርቱ ላይ ያሳየው ፍላጎት እምብዛም ነበር:: ውሎ ቢመጣም ለቁምነገር የሚበቃ ዕውቀት መያዝ አልቻለም::

ስሙን ከመጻፍ የዘለለ ለውጥ ያላገኙበት አክስት እንዳይማር ምክንያት እየፈጠሩ ሊያስቀሩት ሞከሩ:: ዘውድነህ አልተቃወመም:: ሰበብ ፈላጊው ልጅ ሃሳባቸውን በደስታ ተቀብሎ ቤት መዋል ጀመረ:: በአክስቱ ቤት የዘመድ ልጆች ብዙ ናቸው:: በየጊዜው ካገር ቤት እየመጡ የተማሩ፣ሥራ የያዙ፣ጎጆ የቀለሱ ጥቂት አይደሉም::

ዘውድነህ ቤት በዋለ ማግስት የሚሰራውን አላጣም:: በጊቢው ከሚረቡት ላሞች ጋር በፍቅር ወደቀ:: ሽታቸው፣ወተታቸው፣አዛባቸው ሁሉ አስተዳደጉን አስታወሰው:: ከትምህርቱ ይልቅ ለእነሱ ጊዜ ሰጥቶ አብሯቸው መዋል ያዘ:: በኪራይ የሚሸጠውን ወተት የሚያልበው፣የሚያዘጋጀው ታማኝ እሱ ብቻ ሆነ:: ዘውድነህ አልቦዘነም:: ጊዜውን፣ ጉልበቱን ያለስስት ሰጠ::

አሁን የገጠሩ ልጅ የከተማ ወጣት ሆኗል:: ይህ ዕድሜው ብዙ እያሳየው ነው:: እንደ እኩዮቹ መልበስ፣ መዝናናትን አይጠላም:: ሴት ጓደኛ ብትኖረው፣ አብሯት ቢወጣ ቢገባ ይወዳል:: ውሎው ግን ለዚህ ዕድል አይጋብዝም:: ከሰዎች ሲውል የልብሱ ጠረን ያሳቅቀዋል:: የሰዎቹን ፊት ሲያይ ዳግም ሊያገኛቸው ይፈራል:: ሁሌም የከብቶቹ ፣ የአዛባው ሽታ ከእሱ ጋር ነው:: ይህ እውነት ዘውድነህን ገለልተኛ ያደርገው ጀመር::

### ጦርነቱ...

ወቅቱ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት የታወጀበት ነው:: ይህ ጊዜ የሀገር መወረር፣ የዳርድንበር መደፈር ያስቆጫቸው ወገኖች ስለምን ሲሉ የጀገኑበት ነበር:: የዛኔ በሙዚቃው ፣ በግጥሙ፣ በፉከራና ቀረርቶው «እምቢ ባይነት» ደምቆ ይደመጣል:: ይህ ስሜት በርካቶችን ለጦርነት አነሳስቶ ወደ ጦር ግንባር እያዘመተ ነው::

ዘውድነህ ከበርካቶች መሀል አንዱ ለመሆን ጊዜ አልፈጀም:: ድንገት በወሰነው ሃሳብ «ማቄን ጨርቄን» ሳይል ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ተገኘ:: ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ወታደር ሆኖ ዘመቻ ተላከ:: ጦርነቱ ሲፋፋም፣ ጀግኖች ሲዋደቁ ለወራት የዘውድነህ ድምጽ አልተሰማም::

ዘመቻውን ከተቀላቀለ ጥቂት ጊዚያት በኋላ አክስቱ በማረፋቸው ስለእሱ የጠየቀ፣ ያስታወሰ አልተገኘም:: ጊዚያትን የቆጠረው ጦርነት እንዳበቃ ዘውድነህ አንድ እግሩን ተመቶ ሆስፒታል መተኛቱ ተሰማ:: በወቅቱ ስለእሱ ያወቁ ጥቂት ዘመዶቹ ስፍራው ተገኝተው ጠየቁት::

ዘውድነህ ከጦርነቱ ማግስት ከቁስሉ አገግሞ ከሆስፒታል ወጣ:: ወደአክስቱ ቤት ሲገባ የትናንቱን ታሪክ አላገኘም:: ቤቱ ተሸጧል፣ ቤተሰብ ዘመዱ ተበትኗል:: ጠረን ሽታቸው የሚናፍቀው ከብቶች፣በቅርብ የሚያውቃቸው ጎረቤቶች የሉም::

ዘውድነህ ስለሁሉም አዝኖ እርሙን አወጣ:: የደግ አክስቱን ትዝታ በልቡ ይዞም በውስጡ አነባ:: ያደገበትን ሰፈር ተሰናብቶ ወደ ሌላ አካባቢ አቀና፤ መንደርተኛው ወደደው:: ካለው እያጎረሰ፣ ከእጁ እያካፈለ ቀናትን አሻገረው:: ውሎ አድሮ የሰፈሩ አካል ሆነ:: ከደስታው እየተካፈለ፣ ከሀዘኑ ታደመ:: ሰፈርተኛው በኑሮው ከእሱ የሚበልጥ ፣የሚያንስ አይደለም:: ከማንነቱ ሊዋሀድ ፣ከኑሮው ሊመሳሰል ጊዜ አልቆጠረም:: በአጭር ጊዜ ከሁሉም ተግባብቶ ኑሮ መሰረተ::

### አዲስ ህይወት...

ዘውድነህ በብቸኝነት አልቀጠለም:: በዛው ሰፈር ትዳር መስርቶ ልጆች ወለደ:: ወግ ማዕረግ ባየበት አካባቢ ሀዘን ደስታውን የሚጋራው አላጣም::ትናንትን አስኪረሳ፣ ህይወቱ እንደ አዲስ ተጀመረ:: በደሳሳ ማረፊያው ቤተሰቡን ይዞ ዓመታትን ዘለቀ:: ጊዜያት አለፉ፣ እንደዋዛ ነጎዱ::

ከቀናት በአንዱ ለዓመታት ሲወራ የቆየው ጉዳይ ዕውን ሊሆን ግድ አለ:: ተዳፍኖ የኖረው ወሬም እንደ አዲስ ተቀጣጠለ:: አሁን ነዋሪዎቹ በልማት ምክንያት አካባቢውን ሊለቁ፣ከስፍራው ሊርቁ ነው:: ይህ ዜና ለአብዛኞቹ ደስታን አጎናጸፈ:: ዘመናዊ ኑሮን የተመኙ፣ ይህን ቀን ሲያልሙ የቆዩ ለመሄድ ተጣደፉ:: ጥቂቶች አቅማቸውን እያሰቡ በትካዜ ቆዘሙ:: አንዳንዶች ምትክ ቤት ለማግኘት በየቦታው ተሯሯጡ::

እነዘውድነህ በሙሉ አፍ «ቤት» ተብሎ የሚጠራ መጠለያ የላቸውም:: እንዲያም ሆኖ ህይወታቸው ከጎረቤቶቻቸው ያነሰ አልነበረም:: እንደሌሎች መስለው፣ ተመሳስለው ዓመታትን ገፍተዋል:: በዕቁብ በማህበር፣ በዕድር ተነጥለው አያውቁም:: እንደነባሮቹ ነዋሪዎች ግን ዕውቅና ኖሯቸው ቤት አልተመዘገቡም::

እነዘውድነህ ለቤት ዕጣው አልታደሉም:: እንደገሚሱ በምትክ ስለሚሰጠው መኖሪያም ያሰበ፣ ያስታወሳቸው የለም:: ይህ እውነት ካሉበት ተነስተው ወደየትም እንዳይሄዱ ምክንያት ሆነ:: ሌሎች ጓዛቸውን ሸክፈው ሰፈሩን ሲለቁ ዘውድነህና ቤተሰቦቹ በስፍራው ሊቆዩ ግድ ሆነ::

ሰፈርተኛው ከቦታው ሲርቅ የትናንቱን ደማቅ መንደር ዝምታ ዋጠው:: ጭርታው ለነ ዘውድነህ በእጅጉ ከበደ :: ቀናትን በብቸኝነት ቆጠሩ:: ውሎ አድሮ ተጠጋግተው የተሰሩት ዕድሜ ጠገብ ቤቶች ፈረሱ:: ትናንት ህይወትን የተጋሩበት፣ ድግስ የተጠሩበት፣ አውደ ዓመት ያሳለፉበት ፣ ድንቅ ጉርብትና እንደዋዛ ራቃቸው::

እነ ዘውድነህ ተስፋ አልቆረጡም:: ሁለት ህጻናት ልጆችን እንደያዙ የላስቲክ ጎጆ ቀልሰው ኑሮን ጀመሩ:: ማንም ምንም አላላቸውም፣ አልተቃወማቸውም:: ጉርብትና አብሮ መኖር፣ ደስታ ሀዘን ይሉት ትዝታቸው ሆነ:: የጨለማውን ግዝፈት ፣ የዝናብ ጸሀዩን ፈተና ፣ የውሀ ማጣቱን ችግር ተጋፈጡት :: ነገን በተስፋ እያለሙ ወራትን ተሻገሩ::

### የሰዎቹ ዓይን..

ጥቂት ቆይቶ ባለሀብቶች አካባቢውን ይዞሩት ያዙ:: በርካቶች ተመላልሰው ስፍራወን ያዩት፣ ይቃኙት ጀመር:: ይህኔ የእነ ዘውድነህ ልብ በስጋት ተያዘ:: የሰዎቹ እግር ማብዛት አንድ ቀን ከስፍራው እንደሚያርቃቸው ገምተው በሀሳብ ተዋጡ:: ያሰቡት አልቀረም :: ቦታውን ገዝቶታል የተባለ ባለሀብት በአጭር ጊዜ የህንጻ ግንባታውን ጀመረ::

እነ ዘውድነህ ከስፍራው አልራቁም:: ሰውዬውም ለምን እንዴት አላላቸውም:: የእነሱን መኖር ከበጎ ተርጉሞ ንብረት እየጠበቁ በቦታው እንዲኖሩ ይሁንታውን ሰጠ:: በሆነው ሁሉ የተደሰተው ቤተሰብ ከስጋቱ ተመለሰ:: ውሎ አድሮ የላስቲክ ጎጇቸው በቆርቆሮ ቤት ተተካ:: ቤቱን እንዳሻቸው ከፋፍለው መኖር ጀመሩ::

የህንጻው ግንባታ ተጀመረ :: ዘውድነህ የስራ ዕድል ለማግኘት አልዘገየም:: በዘበኝነት ዕቃ እየጠበቀ በቀን ስራው እንዲሳተፍ ተፈቀደለት:: ባለቤቱ ለቀን ሰራተኞች ምግብና ሻይ ቡና ማዘጋጀት ያዘች:: በአጭር ጊዜ ነገሮች መልካም ሆኑ:: ገቢያቸው ጨመረ፣ ኑሯቸው ተሻሻለ:: የልጆች ቁጥር ጨመረ:: ከፍ ያሉት ትምህርት ቤት መዋል ያዙ:: ባልና ሚስት ፈጣሪን አመሰገኑ::

አይቀሬው እውነት...

ዘውድነህ ዛሬ ላይ በፍጥነት ከሚገሰግሱት ህንጻዎች በአንደኛው ጥግ ጎጆ ቀልሶ ወግ ማዕረግ አይቷል:: ይህ ህንጻ ለዓመታት ታዛ ከለላው ነበር:: እንዲህ ሲሆን ግን በዚህ ፍጥነቱ ገስግሶ አልነበረም:: ዛሬ ይህ ሩጫው አልተመቸውም:: ስጋት ሆኖ እንቅልፍ ነስቶታል::

ዘውድነህ ከዓመታት በፊት ከዚህ ስፍራ ሲገኝ አካባቢው በደሳሳ የቀበሌ ቤቶች የተያዘ ነበር:: በነዚህ ቤቶች ውስጥ የነበረ ነዋሪ ህይወቱ ተመሳሳይ፣ ጓዳው አይደበቄ እንደነበር ያስታውሳል:: የዛኔ እሱና ባለቤቱ ከአንዳቸው በረንዳ ተጠግተው እንደወጉ ኑሮን ጀምረው ነበር::

ይህ ጊዜ ቢያልፍም ለዚህ ቤተሰብ የመነሻ ጥሪቱ ነው:: ምንም ባያገኙም ፍቅር አይተውበታል፣ ሀብት ባያፈሩም ደስታን ሸምተውበታል:: አብሮ መኖርን፣ መተባበር፣ መዋደድን አትርፈዋል ::ትናንት ይህ ታሪክ በ«ነበር» አልፏል:: ባላለፈው ዛሬ ያለው ህይወት ግን ይህ አልሆነም::

አሁን ህንጻው እየተጠናቀቀ ነው:: በዓመታት የግንባታ ቆይታው ባጋጠመው አንዳንድ ችግር ማለቅ ባለበት ጊዜ አልደረሰም:: እንዲህ መሆኑ የጎዳው ባለሀብቱን እንጂ ዘውድነህን አልነበረም:: ይህ አጋጣሚ ለእሱ ቱርፋቱ ነበር:: የቆይታው መርዘም የእሱን መኖር አዝልጎ የዓመታት ታዛ ሆኖታል:: ያለበትን እስኪዘነጋ፣ስለነገ ማሰብ እስኪረሳ ኑሮ ቀጥሎበታል::

ባለፉት ዓመታት ለዘውድነህ የተረፈው ተጠልሎ መኖር ብቻ አይደለም:: እንጨቶቹን ሸጦ እንዲጠቀም፣ የሚወገዱትን ለራሱ እንዲያደርግ ዕድል በእጁ ነበር:: በዚህ ብዙ ተጠቅሟል፣ ቤቱን ሞልቶ ልጆች አሳድጓል፣ ዶሮዎች አርብቶ እንቁላሎች ሸጧል::

ዛሬ ግን ይህ እውነት ከእሱ የለም:: የግንባታ እንጨቱ ሲነሳ ፣ልቡ ይደነግጣል፣ ህንጻው በቀለም ሲያምር ይከፋል፣ስፍራው ሲጠረግ ሲጸዳ ያዝናል፣ ይተክዛል:: ነገ በእሱ ውስጠት እንደትናንቱ አይደለም:: ቀናቶቹ ሲታዩት ልቡ ይናዳል፣ ስጋቱ ያይላል::«የት እደርሳለሁ ?ምን እሆናለሁ?» ይሉት ጭንቀት ከእሱ አልፎ ለቤተሰቡ ተጋብቷል::

ዘውድነህ ያለፈበትን የህይወት ጎዳና ሲቃኘው እምብዛም አይከፋውም:: አልፎበት ተራምዷልና ግስጋሴው ወደፊት ነው:: ዛሬ ግን ነገን ለመሻገር ያለበትን ጫና የሚያወርድለት ወገን መሻቱ አልቀረም:: ቀድሞ የሞከረው የቀበሌ ቤት ጥያቄ ባይሳካም ዛሬም ደጅ እየጠና መመላለስ ይዟል::

ይህ ህንጻ ሲያልቅ፣በስፍራው እንደማይቆ አሳምሮ ያውቃል ፤ልጆቹ ከጀመሩት ትምህርት እንዲደናቀፉ አይሻም:: ዛሬን አልፎ ከነገ ለመድረስ ሀሳብ የሆነበትን እውነት ሊደርስበት አይፈልግም::

ነገ ለእሱ ስጋቱ ነው:: ነገ ለእሱ ያልተመለሰ ጥያቄው ምላሽ ያላገኘበት ምስጢሩ ነው:: እናም መፍትሄን ይሻል::«አለንህ፣ከጎንህ ነን» የሚለውን ወገን ይናፍቃል:: ዛሬን በተስፋ አድሮ ነገን የሚሰጋው ብርቱ አባወራ::

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ፅናትና ታታሪነት ለስኬት ያበቁት ሁለገቡ ወጣት



አቶ ሰርፀሚካኤል ጉችማ

**አንተነህ ቸሬ**

አንዳንዶች ገንዘብን ገና በወጣትነታቸው ያገኙትና ልጅነት ይዟቸው፣ ማስተዋል አጥሯቸው ያገኙትን ገንዘብ ያለአግባብ አባክነውት የጉልምስና ዕድሜያቸውንም በችግርና በትካዜ ያሳልፉታል:: እነዚህ ሰዎች ገንዘባቸው ልባቸውን ቀድሞት በመሄዱ፣ ገንዘባቸውን በጥሩ ልብ መምራት ሳይሆንላቸው ቀርቶ ‹‹ምነው ያኔ ከገንዘቡ ጋር ልቡም ኖሮኝ ቢሆን?!›› እያሉ ለገንዘብ ቅርብ፣ ለልብ ግን ሩቅ ሆነው ያሳለፉትን ዘመናቸውን በቁጭት የሚያስታውሱ ናቸው::

ጥቂት ቢሆኑም ሀብትንም ብስለትንም በአንድ ጊዜ፣ ያውም በጠዋቱ፣ የሚጨብጡትና ይዘው የሚያቆዩት አስደናቂ ሰዎችም አሉ:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች ሕይወት ገና በጠዋቱ ብዙ ያስተማረቻቸው፣ የሕይወትን ትምህርትና ልምድ በማስተዋል የተገበሩ፣ ያላቸውን ለሌሎች በማካፈል በፅኑ የሚያምኑ እና ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች መሆን የሚችሉ አርዓያዎች ናቸው:: ገንዘባቸው ልባቸውን ሳይቀድም የሚመጣላቸውና ልባቸውን ለገንዘባቸው መምሪያና ማስተዳደሪያ በብቃት የመጠቀም ችሎታ ያላቸውም ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ለገንዘብ ቅርብ የሆኑትን ያህል ለልብም ቅርብ ናቸው::

የ‹‹ጣዝማ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር›› መስራችና ባለቤት አቶ ሰርፀሚካኤል ጉችማ ሀብታምነትንና ልባምነትን አስማምተው ከያዙ ወጣቶች መካከል የሚመደብ የስኬት ምሳሌ ነው:: ሰርፀሚካኤል የተወለደው በ1981 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ዞን፣ መርሐቤቴ ወረዳ፣ ዓለም ከተማ ነው::

ገና በልጅነቱ ወላጆቹን በሞት የተነጠቀው ሰርፀሚካኤል፣ አባቱ በወታደራዊው መንግሥት (ደርግ) ዘመን ሀገራቸውን በውትርድና ሲያገለግሉ ቆስለው ስለነበር በ1988 ዓ.ም አረፉ:: ሰርፀሚካኤልን ብቻቸውን የማሳደግ ኃላፊነትን የተረከቡት እናቱም ብዙም ሳይቆዩ በ1992 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ይህ አሳዛኝ አጋጣሚ የታዳጊውን የሰርፀሚካኤልን ሕይወት ገና በለጋነቱ መራራ ገፅታ እንዲጋፈጥ አስገደደው:: ሰፊ በሆነው የወላጆቹ ቤት ውስጥ ብቻውን መኖርን ጨምሮ፣ ለመኖር የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት ተቸገረ::

ሰርፀሚካኤል የሕይወትን ፈተናዎች ለማሸነፍ ትግሉን ጀመረ:: ለትምህርት ያለው የጋለ ፍላጎትና የትምህርት አቀባበሉም ጠንካራ ከሚባሉ ተማሪዎች ተርታ የሚያሰልፈው ስለነበር፣ አቅሙ የፈቀደውን ሥራ እየሠራ ትምህርቱን ለመቀጠል ወሰነ:: ፀጉር ቤት ከፍቶ ፀጉር እያስተካከለና ሌሎች ሥራዎችን እየሠራ በሚያገኘው ገቢ ሥራንና ትምህርትን ጎን ለጎን ማስኬድ ቻለ::

‹‹ለትምህርት የሚያስፈልገኝን ወጪ መሸፈኛ ገንዘብ አጣሁ ብዬ ትምህርቱን ማቋረጥ አልፈለግኩም›› የሚለው ሰርፀሚካኤል፣ የእናቱ ቃል ተጨማሪ ብርታት እንደሆነው ይናገራል::‹‹እናቴ ብቻዋንም ሆና በትምህርቴ እንድበረታ ታግዘኝ ነበር:: ስትሞትም ‹የልጄን ትምህርት አደራ› ብላ ተናግራ ነበር:: ቃሏን ለማክበርም ትምህርቴን መቀጠል ነበረብኝ›› በማለት ያስታውሳል:: ይህ ጥንካሬውም የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን (ከ1ኛ-8ኛ ክፍል) በዓለም ከተማ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በአርበኞች ሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት ተምሮ እንዲያጠናቅቅ አስችሎታል::

የ10ኛ ክፍል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በመርሐቤቴ ወረዳ ማስታወቂያ ጽሕፈት ቤት ፖስተኛ ሆኖ ተቀጠረ:: በወቅቱ የክልሉ መንግሥት ወጣት ለሆኑ፣ ፈጣን የትምህርት አቀባበል ለነበራቸው እና የተሻለ የሥራ አፈፃፀም ላሳዩ ሠራተኞች የትምህርት ዕድልና የሥራ ኃላፊነት ይሰጥ ስለነበር ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት የቻለው ሰርፀሚካኤል፣ የትምህርት ዕድሉ ተጠቃሚ ሆኖ ቀድሞ ከነበረባቸው የሥራ መደቦች ከፍ ባሉ ኃላፊነቶች ላይ ማገልገል ችሏል፤ ምስጉን የሥራ አፈፃፀሙ ቡድን መሪ እስከመሆን አደረሰው:: ቀን እየሠራ ማታ በ‹‹አልማዝ በም ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ›› በኮምፒዩተር ሳይንስ ተምሮ በደረጃ አራት (Level 4) በዲፕሎማ የተመረቀው በዚህ ወቅት ነበር::

ያልተቋረጠ ማደግና መሻሻል ከሕይወት መርሆቹ መካከል አንዱ ነውና ለተሻለ ሕይወት ወደሰፊዋ አዲስ አበባ መግባት እንዳለበት አምኖ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃዎቹን ይዞ በ2004 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጣ:: አዲስ አበባ ያደረገችለት አቀባበል ግን ሌላ የፈተና ምዕራፍ ሆነበት:: እርሱም ቢሆን ይህ ዓይነቱ ፈተና እንደሚገጥመው ቀድሞ ያውቅ ስለነበር ለዋና ከተማዋ የሕይወት ፈተና ራሱን አዘጋጅቶ እንደለመደው የለውጥ ትግሉን ተያያዘው:: በዚያ ጊዜ ለሥራ ፍለጋ ከአዲሱ ገበያ እስከ ቃሊቲ ድረስ በእግሩ ለመጓዝ ይገደድ ነበር::

የሰርፀሚካኤል የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ‹‹ምሥራቅ ድል ትምህርት ቤት ›› ላወጣው የሰው ኃይል አስተዳደር ባለሙያ የሥራ መደብ የሚመጥን ስለነበር፣ ውድድሩን አልፎ በዚሁ ሥራ መደብ የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ ለመሆን በቃ:: 1ሺ295 ብር ወርሃዊ ደመወዙ ለኑሮው በቂ ስላልነበር ተጨማሪ ሥራዎችን መሥራት እንዳለበት አመነ:: እናም ጠዋት ሥራ እስከሚገባ ድረስ እና ማታ ከሥራ ከወጣ በኋላ የሚኖረውን ጊዜ ተጨማሪ ሥራ ሊሠራበት ወሰነ::

‹‹መንጃ ፈቃድ ስለነበረኝ ከመደበኛው ሥራዬ በተጨማሪ ጠዋትና ማታ ታክሲ አሽከርካሪ ሆኜ እሠራ ነበር:: ጠዋት ቢሮ ከመግባቴ በፊት እስከ አውቶቡስ ተራ፣ ከሥራ ከወጣሁ በኋላ ከቀኑ 11 ሰዓት እስከ ምሽት ሦስት ሰዓት እስከአያት ድረስ እሠራ ነበር:: ከጓደኞቼ ጋር የሚኖረኝ የመዝናኛ ሰዓት ራሱን የቻለ ፕሮግራም አለው:: እንደዚያ ባላደርግ ኖሮ የኑሮ ጫናዎችን መቋቋም አልችልም ነበር›› በማለት የሚባክን ጊዜ እንዳልነበረው ያስታውሳል::

ሰርፀሚካኤል ቀደም ሲል ይታወቅበት የነበረው ትጋቱና የላቀ የሥራ አፈፃፀሙ በምሥራቅ ድል ትምህርት ቤት ከ2004 ዓ.ም መጨረሻ እስከ 2007ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ በነበረው ቆይታም አብሮት ዘልቋል:: ይህም ለተሻለ ኃላፊነት አበቃውና በተለያዩ ተቋማት ውስጥ በከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ተመድቦ እንዲሠራ አስችሎታል::

በእነዚህ የኃላፊነት ቦታዎችም ላይ ብቃት ያለው ባለሙያና መሪ መሆኑን በማስመስከሩ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ሆኖ በ2011 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በከተማ መሬት አስተዳደርና ኢንፎርሜሽን ሲስተም የትምህርት መስክ (Urban Land Use Management and Information System) የመጀመሪያ ዲግሪውን አገኘ:: በየትኛውም አጋጣሚ ከሥራ ውጪ መሆን የማይፈልገው ሰርፀሚካኤል፣ ትምህርቱን እየተማረም ሆቴል ከፍቶ ይሠራ ነበር:: በወቅቱ አዋጭ የነበረው ይህ ሥራው ለወደፊት እቅዱና ጉዞው ስኬት ጠቅሞታል::

በሀገሪቱ የግንባታ ሥራ ዘርፍ ላይ ለውጥ የሚፈጥርና ለዘርፉም እድገት የራሱን አስተዋፅዖ የሚያበረክት የግንባታ ተቋም የማቋቋም የረጅም ጊዜ እቅድ የነበረው ሰርፀሚካኤል፣ ይህ እቅዱ እውን የሚሆንበት ጊዜ መድረሱን በማመኑ፣ የትምህርት ዝግጅቱና የሥራ ልምዱ በሚፈቅድለት አግባብ መሠረት፣ በ2012 ዓ.ም በ150ሺ ብር መነሻ ካፒታል ‹‹ጣዝማ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር››ን አቋቋመ::

ድርጅቱን ‹‹ጣዝማ›› ብሎ የመሰየሙ ምክንያትም የድርጅቱ ሥራዎች ተመራጭ፣ ጥልቅና ጠንካራ ሆነው በግንባታው ዘርፍ ለሚታዩ ችግሮች እንደጣዝማ ማር ተፈላጊና ፍቱን መድኃኒት እንዲሆኑ ከመሻትና ከማቀድ የመነጨ እንደሆነ ሰርፀሚካኤል ይገልፃል:: ‹‹የጣዝማ ማር በቀላሉ የሚገኝ አይደለም:: ማሩን ለማግኘት ብዙ መልፋት ይጠይቃል:: ማሩ ለብዙ በሽታዎች ፍቱን መድኃኒትም ነው:: ‹ጣዝማ ኮንስትራክሽን›ም ሥራዎችን በጥረትና በልፋት በማከናወን በዘርፉ ለሚታዩ ችግሮች መፍትሔ ለመሆን ይተጋል:: ድርጅቱን ‹ጣዝማ› ብለን ስንሰይመው ተግባራችንን እንዲገልፅ ከመፈለግ በመነጨ ስሜት ነው:: ‹ጣዝማ› የሚለው ስም ጥረታችንን ሊያጎላ ይችላል ብለን እናምናለን›› በማለት ድርጅቱ ‹ጣዝማ› ተብሎ የተሰየመበትን ምክንያት ያስረዳል::

አቶ ሰርፀሚካኤል እንደሚገልፀው፣ ‹‹ጣዝማ ኮንስትራክሽን›› የግለሰብ ቤቶችን፣ አብያተ ክርስቲያናትን፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን፣ ኮብልስቶኖችን፣ ድልድዮችንና ሌሎች ግንባታዎችን በታቀደላቸው የግንባታ ጥራት፣ ዋጋና ጊዜ መሠረት ያከናውናል:: ከሥራዎቹ መካከል በቦሌ አራብሳ፣ አያት፣ የካ አባዶ፣ ፒያሳ (እሪ በከንቱ) አካባቢዎች የሚገኙ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የማጠናቀቂያ (ፊኒሽንግ) ሥራዎች ይጠቀሳሉ:: ድርጅቱ በርካታ የግለሰብ ቤቶችን፣ የግል ተቋማትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሕንፃዎችን ሠርቶ አስረክቧል:: ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪም የሚያከናውናቸው የግንባታ ሥራዎች አሉት:: ከግንባታ ሥራ በተጨማሪ የግንባታ ሥራ ለሚሠሩ አካላት ጠጠር፣ ብሎኬት፣ አሸዋና ሌሎች ግብዓቶችንም ያቀርባል::

አሁን በስፋት እየሠራበት ባይሆንም የሲልካሳንድ ማዕድንን (Silica Sand) ለብርጭቆና ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ያቀርባል:: በመርሐቤቴ ወረዳ፣ ዓለም ከተማ ላይ ባለአራት ኮከብ ሆቴል ለመገንባት የሚያስችለውን ፈቃድም አግኝቷል:: ቦታ ተረክቦ ግንባታውን ለመጀመር በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የሚስተዋለው የፀጥታ መደፍረስ እስከሚስተካከል ድረስ ብቻ እየጠበቀ ይገኛል:: ‹‹ጣዝማ ኮንስትራክሽን›› ከግንባታና የግንባታ ግብዓቶችን ከማቅረብ ሥራዎቹ በተጨማሪ የፈጣን መልዕክት አገልግሎት ይሰጣል:: የራሱ ንብረት በሆኑና በተከራያቸው ሞተሮች አማካኝነት መልዕክቶችን ለባለጉዳዮች ያደርሳል::

‹‹ግንባታዎችን የምንሠራው በተመጣጣኝ ዋጋ ነው፤ በሀገራችን ብዙ የሰው ኃይል አለ፤ብዙ ሥራዎችን በመሥራት በረጅም ጊዜ ትርፍ ለማግኘት (ከብዙ ሥራ ብዙ ትርፍ ማግኘት) እንጂ ከአንድ ሥራ ብዙ ትርፍ ለማግኘት አንሠራም:: ብዙ የግንባታ ባለቤቶችና የሥራ ተቋራጮች ግንባታዎች በጊዜያቸው ባለመጠናቀቃቸው ምክንያት አለመግባባት ውስጥ ሲገቡና ሲካሰሱ እናስተውላለን:: እኛ አቅማችንና ሕጉ በሚፈቅድልን አሠራር ብቻ ተወስነን ስለምንሠራ እስካሁን እንዲህ ዓይነት ቅሬታ ቀርቦብን አያውቅም:: ጥሩ የሥራ አፈፃፀም ታሪክ ስላለን ሥራዎችን ለማግኘት አንቸገርም:: ብዙ እውቅናዎችና ምስጋናዎችም ተችረውናል:: በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሻለ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችል መልክ እየሠራን እንገኛለን›› ይላል::

ይሁን እንጂ ሥራውን ሲጀምር በርካታ መሰናክሎች እንደነበሩ ያስታውሳል:: በቂ ልምድ አለመኖርና የግንባታ ባለቤቶችን ሙሉ እምነት ለማግኘት መቸገር እና የፋይናንስና የግንባታ ዕቃዎች እጥረት ዋናዎቹ ፈተናዎች እንደነበሩ ገልጾ፣ ድርጅቱ የመጀመሪያ ሥራዎቹን በታቀደው ጊዜና ጥራት አጠናቆ ማስረከብ ቢችልም ኪሳራ እንዳስመዘገበ ያስታውሳል:: ‹‹ጣዝማ ኮንስትራክሽን›› በመጀመሪያዎቹ ሥራዎች ኪሳራ ቢያስመዘግብም ሥራዎቹን በተሰጠው ጊዜና በተቀመጠላቸው የጥራት ደረጃ አጠናቅቆ ማስረከቡ በግንባታ ባለቤቶች ዘንድ እምነት አትርፎለት ለቀጣይ ሥራዎቹ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል:: በ150ሺ ብር ሥራውን የጀመረው ‹‹ጣዝማ ኮንስትራክሽን››፣ ዛሬ የበርካታ ሚሊዮን ብሮች ባለቤት መሆን ችሏል::

ሰርፀሚካኤል በወጣትነቱ የገንዘብ ሀብታም መሆን የቻለ ሰው ብቻ አይደለም፤ ገና በወጣትነቱ ልባምነትንም የታደለ ነው:: ልባም ለመባል ያበቃው ሀብት እንዲያፈራ ያስቻለው ትጉህ ሠራተኛነቱ ብቻ ሳይሆን ያለውን ሀብት ለሌሎች የማካፈል ባህርይው ነው::

ድርጅቱ ‹‹ጣዝማ ኮንስትራክሽን›› ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ በርካታ ተግባራትን ያከናውናል:: ‹‹ዞን ስድስት›› የሚባለው የአያት አካባቢ በክረምት ወራት የሰፈሩ መንገድ አስቸጋሪ ሲሆን አሸዋና ጠጠር በማቅረብ የመንገድ ጥርጊያ ሥራ ያከናውናል:: ለአብያተ ክርስቲያናትና ለመስጊዶች ድጋፍ ያደርጋል፤ ይህም ሰፈሩ ሰላማዊና የኅብረተሰቡም መስተጋብር ጠንካራ እንዲሆን አድርጓል::

በበዓላት ወቅት የማዕድ ማጋራት ሥራ ያከናውናል:: ለአብነት ያህል በዘንድሮው ገና በዓል ለክፍለ ከተማው ከ200 ሊትር በላይ ዘይት እንዲሁም ለወረዳው ደግሞ በርካታ በጎችና ዶሮ ገዝቶ አበርክቷል:: የድሃ ድሃ ተብለው ለተለዩ ዜጎች ቤታቸውን ያድሳል::

አቶ ሰርፀሚካኤልም በግለሰብ ደረጃ በሚኖርበት አካባቢ (አያት፣ ዞን ስድስት) ውሃና መብራት እንዲገባ የኮሚቴ አባል በመሆን እንዲሁም የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክቷል:: የአዲስ አበባ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በመሆንም በነፃ እያገለገለ ይገኛል::

‹‹አቅማችን በፈቀደ መጠን ማኅበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ጥረት ስናደርግ ቆይተናል፤እያደረግንም እንገኛለን፤ወደፊትም እንቀጥላለን:: በእኛ ሀገር ችግር የሆነው አቅም በፈቀደው ልክ አለመረዳዳት ነው:: ሰውንና ተቋማትን መርዳት በፈጣሪ ዘንድ ዋጋ ሊያሰጥና የመንፈስ እርካታ ሊያስገኝ የሚችል በጎ ተግባር ነው:: የጣዝማ አንዱ የስኬት ምክንያትም ማኅበራዊ ኃላፊነታችንን በመወጣታችን የምናገኘው በረከትና ምርቃት ነው›› በማለት ማኅበራዊ ኃላፊነትን የመወጣትን አስፈላጊነትና አስደሳችነት ያስረዳል::

ዛሬ በስኬት ጎዳና ላይ የሚገኘው አቶ ሰርፀሚካኤል ጉችማ፣ በአንድ ወቅት ወደ ቤቱ ለመድረስ ለትራንስፖርት የሚሆን ሁለት ብር አጥቶ እንደነበር እንዲህ ያስታውሳል:: ‹‹ከዓለም ከተማ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ፣ ከአዲሱ ገበያ እስከ ፒያሳ ድረስ በታክሲ ተጓዝኩ:: ከዚያ በኋላ ምንም ገንዘብ ስላልነበረኝ ከፒያሳ እስከ መገናኛ ድረስ በእግሬ ሄድኩ:: መኖሪያ ሰፈሬ አያት አካባቢ ስለነበር ሁለት ብር ከፍዬ በአውቶቡስ ለመጓዝ ተቸገርኩ:: በወቅቱ የነበረኝ አማራጭ ስልኬ ውስጥ ያለውን ካርድ ሸጬ በአውቶቡስ መጓዝ ስለነበር፣ የአየር ሰዓት (ካርድ) ወደ ሌላ ሰው አስተላልፌ ባገኘሁት ብር በአውቶቡስ ሰፈር ደረስኩ::

አቶ ሰርፀሚካኤል ችግሮችን የምሬትና መሰናክል ምንጭ አድርጎ ከማየት ይልቅ የጥንካሬ መመዘኛና የብቃት መፈተኛ አድርጎ ይመለከታቸዋል። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ‹‹ብዙ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ዋናው ቁም ነገር ለችግሮችና ለፈተናዎች አለመበገርና በፅናት ታግሎ ማሸነፍ ነው:: ችግር ባጋጠመን ጊዜ የበለጠ ጠንካራ በመሆን አሸናፊ መሆን ያስፈልጋል›› ብሎ የሚናገረው።

‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ሥራ ላይ ብቻ የመወሰንና ለስምንት ሰዓታት ብቻ የመሥራት ልምድ ሊቀየር ይገባል›› በማለት በአፅንዖት የሚናገረው አቶ ሰርፀሚካኤል፣ ሥራን ለነገ ብሎ አለማሳደሩ፣ ውሳኔ ለመወሰን አለመቸገሩ እና በአንድ ጊዜ ብዙ ሥራዎችን መሥራቱ ለስኬት እንዳበቁት ይገልፃል:: አቶ ሰርፀሚካኤል በርካታ ፈተናዎችን አልፎ ዛሬ ለሚገኝበት ትልቅ ደረጃ መብቃቱ ‹‹የስኬት ጫፍ ላይ ደርሻለሁና ይበቃኛል›› ብሎ እንዲቀመጥ አላደረገውም፤ድርጅቱን አሁን ካለበት ደረጃ የተሻለ የማድረግ ዓላማና ራዕይ አለው።

# ስፖርት





## የአፍሪካ ብሔራዊ ቡድኖችና የውጪ ተጫዋቾች ተፅእኖ

ቦጋለ አበበ

በዘንድሮው የ2023 አፍሪካ ዋንጫ ከ24 ሀገራት 630 ያህል ተጫዋቾች ብሔራዊ ቡድኖቻቸውን ወክለው እየተሳተፉ ይገኛሉ። ከእነዚህ ተጫዋቾች መካከል 200 ያህሉ ተጫዋቾች የተወለዱት ከአፍሪካ ውጪ ነው። ይህም በአፍሪካ ዋንጫ አዲስ ክብረወሰን ሆኖ ተመዝግቧል። ተጫዋቾቻቸው ሙሉ በሙሉ በአፍሪካ የተወለዱ ሀገራት ደቡብ አፍሪካ፣ ግብጽና ናሚቢያ ብቻ ናቸው።

በአፍሪካ ዋንጫው እየተሳተፉ ከሚገኙ ተጫዋቾች መካከል 104ቱ በፈረንሳይ የተወለዱ ናቸው። 24 ተጫዋቾች በስፔን፣ 15ቱ በእንግሊዝ፣ 13ቱ በኔዘርላንድስ፣ 10ሩ በፖርቹጋል የተወለዱ ናቸው። በዴንማርክ፣ አየርላንድ፣ ስዊድን፣ ስዊዘርላንድና በሌሎችም ከአፍሪካ ውጪ የተወለዱ ተጫዋቾች በአፍሪካ ዋንጫው ለተለያዩ ብሔራዊ ቡድኖች ተሰልፈዋል።

ዋንጫውን ለማንሳት ትልቅ ግምት የተሰጣት ሞሮኮ ከሀገሪቱ ውጪ የተወለዱ በርካታ ተጫዋቾችን በብሔራዊ ቡድኗ በማካተት ቀዳሚ ነች። የአትላስ አናብስት ባለፈው 2022 የዓለም ዋንጫ የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚ የሆነች የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት ሀገር ስትሆን መሠረታቸውን አውሮፓና ሌሎች ሀገራት ያደረጉ 18 ያህል ተጫዋቾች በብሔራዊ ቡድኑ መካተታቸው ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው።

የአፍሪካ ዋንጫ አዘጋጇ ኮትዲቯርን በሦስተኛው የምድብ ጨዋታ 4ለ0 በማሸነፍ አስደናቂ አቋም ያሳየችው ኢኳቶሪያል ጊኒ ከሞሮኮ በመቀጠል 17 ተጫዋቾቿ የተወለዱት ከሀገሪቱ ውጪ ነው። ዲሞክራቲክ ኮንጎ ደግሞ በ16 ተጫዋቾች ተከታዩን ደረጃ ትይዛለች። ጠንካራ ብሔራዊ ቡድን ያላቸው እንደ አልጄሪያ፣ ቻምፒዮኗ ሴኔጋል፣ ናይጄሪያ፣ ኮትዲቯርና ሌሎችም በርካታ ሀገራት ወሳኝ የሆኑ በርካታ ተጫዋቾቻቸው መሠረታቸው ከአፍሪካ ውጪ ነው።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአፍሪካ ዋንጫ ጠንካራ ብሔራዊ ቡድን ገንብተው እየታዩ የሚገኙ እንደ ኬፐቨርዴ ዓይነት ሀገራትም በውጭ ሀገራት የተወለዱ ተጫዋቾቻቸውን በመጠቀም ውጤታማ እየሆኑ ይገኛሉ።

እነዚህ ሀገራት በውጭ የተወለዱ ተጫዋቾቻቸውን በብሔራዊ ቡድናቸው መጠቀማቸው ጠንካራ ተፎካካሪ ሆነው ብቅ ለማለታቸው ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው በስፖርቱ ባለሙያዎች ተደጋግሞ የተነገረና የሚያስማማ ጉዳይ ነው። ዋናው ቁም ነገር ተጫዋቾቹ በውጭ ሀገራት መወለዳቸው አይደለም። ተጫዋቾቹ የዳበረ የእግር ኳስ ባህል፣ በዘመናዊ ሥልጠናና ሳይንሳዊ መንገድ መገራታቸው ለየቡድኖቻቸው የተሻለ ነገር እንዲያበረክቱ እንዳስቻላቸው የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም።

ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ተጠቃሚ መሆን ካልቻሉ ሀገራት አንዷ ነች። ባለፈው አፍሪካ ዋንጫ ከተሳተፉ 24 ሀገራት መካከል አንድም ከአፍሪካ ውጪ የተወለደ ተጫዋች ያላካተተችው ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች።

ለዚህም ጥምር ዜግነት አለመፍቀዷ ዋነኛው ምክንያት ሆኖ ሲያከራክርም ቆይቷል። ከሌሎች



የአፍሪካ ሀገራት ባልተናነሰ በአውሮፓና ሌሎች የተሻለ የእግር ኳስ ደረጃ ያላቸው ሀገራት ውስጥ ተወልደው በትልቅ ደረጃ የሚጫወቱ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በርካታ ናቸው። እነዚህ ተጫዋቾች በርካቶቹ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የመጫወት ፍላጎታቸውን ሲያሳዩ በተደጋጋሚ ታይቷል። ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያ ውጪ ያላቸውን ፓስፖርት ቀደው ለመምጣት ፍላጎት የላቸውም።

እነዚህ ተጫዋቾች ለኢትዮጵያ የመጫወት ፍላጎት የሚያሳዩት ሀገሪቱ እንደ አፍሪካ ዋንጫ ያሉ ታላላቅ መድረኮች ላይ ስትሳተፍ እንጂ በማጣሪያ ውድድሮች ላይ ፍላጎት የላቸውም ተብለው ይወቀሳሉ። በዚህ ሃሳብ የማይስማሙ አሰልጣኞች ተጫዋቾቹን ወደብሔራዊ ቡድኑ የመጥራትና የመመልከት ፍላጎት እንደሌላቸው ሲናገሩ ይደመጣሉ።

የኢትዮጵያ ሕግና የተጫዋቾቹ ፍላጎት ለየቅል መሆኑ ብሔራዊ ቡድኑ ይህን ዕድል መጠቀም እንዳልቻለ ፌዴሬሽኑ በተለያየ ጊዜ ሲገልጽ ይደመጣል። በውጭ የሚጫወቱ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ከያሉበት በመመልመል ለዋልያዎቹ እንዲጫወቱ ትልቅ ጥረት በማድረግ የሚታወቀውና ለኢትዮጵያ ቡና የተጫወተው ትውልደ ጀርመናዊው ዴቪድ በሻህ ግን ይህ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ ደጋግሞ ተናግሯል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ይህን ዕድል መጠቀም እንዲችል በሚዲያና በሌሎች የስፖርቱ ባለሙያዎች አማካኝነት ከብዙ ውትወታ በኋላ በቅርቡ በውጭ የተወለዱ ኢትዮጵያውያን ተጫዋቾችን መጠቀም የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ጥረት እንደጀመረ ይታወቃል።

እነዚህ ተጫዋቾች የውጭ ፓስፖርታቸውን ሳይቀዱ የኢትዮጵያን ጥምር ዜግነትም ሳያገኙ ለብሔራዊ ቡድኑ መጫወት የሚችሉበት ተስፋ ከወደ ፊፋ ተሰምቶ ነበር። ይህም ተጫዋቾች መጀመሪያ የያዙትን ፓስፖርት ሳይቀዱ በስፖርት ፓስፖርት (ስፖርት ቪዛ) የሚጫወቱበት መንገድ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ጉዳይ በራሱ ውስብስብና አሳሪ ሂደቶች ያሉት በመሆኑ ብዙ ርቀት ሳይጓዝ ተደፋፍኖ ቀርቷል።

ፊፋ እአአ 2014 ባወጣው አዲስ መመሪያ መሠረት አንድ ተጫዋች በእናቱና በአባቱ አሊያም በአያቶቹ ኢትዮጵያዊ ከሆነና ላደገበት ሀገር ዋና ብሔራዊ ቡድን ካልተጫወተ ለኢትዮጵያ የመጫወት መብት እንዳለው ያስቀምጣል። ይህም ቢሆን እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ጥምር ዜግነት ለማይፈቅዱ ሀገራትና የውጭ ፓስፖርታቸውን ለመቅደድ ፍቃደኛ ላልሆኑ ተጫዋቾች ጉዳይ መፍትሔ ሆኖ እየታየ አይደለም።

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

**ከኢፌዴሪ ግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም**

## አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ያደረገው ፕሮግራም

ሸምሱዲን ዩሱፍ

በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በተደጋጋሚ በሚከሰተው ድርቅና በሌሎችም ምክንያቶች ያጋጠመውን የምግብ ዋስትና ችግር ለመቅረፍና የችግሩ ተጠቂ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል በዘላቂነት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንዲችል የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ተቀርፀው ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይተዋል:: ከፕሮግራሞቹ ውስጥ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም አንዱ ነው::

በ1997 ዓ.ም የተጀመረው የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንጻር ሁለት ዋና ዓላማዎችን ያነገበ ነው። እነሱም የምግብ ክፍተትን በመሙላት የቤተሰብ ጥሪት መገንባትና የኅብረተሰብ ጥሪትን መገንባት ነው:: ፕሮግራሙ በእስካሁን እንቅስቃሴው አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል።

በዚህ ፕሮግራም የታቀፉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በገጠር የሚኖሩና ስር ለሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር የተጋለጡ ቤተሰቦች ናቸው። የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች በሁለት የተከፈሉ ሲሆኑ እነርሱም በማኅበረሰብ ሥራ የሚሳተፉ እና በነፃ ድጋፍ የሚያገኙ ናቸው::

ነፃ ድጋፍ የሚሰጣቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ በሕመም ምክንያት መሥራት የማይችሉ ሰዎች፣ እንዲሁም በጊዜያዊነት ነፃ ድጋፍ የሚሰጣቸው ተጠቃሚዎች ናቸው:: በማኅበረሰብ ሥራ በመሳተፍ የሚደገፉ ደግሞ የገጠማቸውን የምግብ ክፍተት ለመሙላት በተለያዩ የማኅበረሰብ ሥራዎች ላይ ተሳትፈው ክፍያ በማግኘት የሚጠቀሙ ናቸው:: ፕሮግራሙ አሁን በ5ኛ ምዕራፍ ላይ ደርሷል:: በማኅበረሰብ ሥራ የሚደገፉ 6,859,618፣ በነፃ የሚደገፉ ደግሞ 1,137,598 ናቸው::



አርሶ አደር መሐመድ አልይ



አርሶ አደር ከማል አብዱረሐማን

በአጠቃላይ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች 7,997,216 ናቸው::

ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በሀገራችን ተግባራዊ ከሆነ ወዲህ በተተገበረባቸው አካባቢዎች ድርብ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችሏል:: በተለይም ከቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ዘዴ ፕሮግራም ጋር በማስተሳሰር ከግንዛቤ ማዳበር ሥራ ጀምሮ በተከናወኑ ሥራዎች በርካታ የፕሮግራሙ ተጠቀሚዎች የምግብ ዋስትናቸውን በማረጋገጥ ሀብት ማፍራት ችለዋል:: በማኅበረሰብ ሥራ የተሳተፉት ተጠቃሚዎች የምግብ ክፍተታቸውን ከመሙላት ባሻገር በአንድ በኩል የቤተሰባቸውን ጥሪት ገንብተው በሌላ በኩል ደግሞ የማኅበረሰብ ጥሪት መገንባት ችለዋል:: እንዲሁም ማኅበረሰቡ ከጥገኝነት አመለካከት ተላቆ ሠርቶ የማግኘት አስተሳሰብን እንዲያዳብር ማድረግ ተችሏል:: ለማሳያነትም ሁለት አካባቢዎችን ማንሳት ይቻላል::

ገመቺስ ወረዳ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ውስጥ ነው የሚገኘው:: ከ1997 ዓ.ም በፊት ወረዳውን የሚያውቅ ሰው ነው ዛሬ የሴፍቲኔት ፕሮግራም ውጤትን በሚገባ የሚረዳው ነው ይላሉ ነዋሪዎቹ:: ወረዳው የመሬት አቀማመጡ ተዳፋታማ በመሆኑ ለም አፈር ታጥቦ ከጥቅም ውጪ የሆነበት፣ አካባቢው በመራቆቱ ለከፍተኛ የዝናብ እጥረት ተጋልጦ ለኑሮ ምቹ ባለመሆኑ ሕዝቡ ለቆ የሚሰደድበት ወረዳ ነበር:: ዛሬ ግን በፕሮግራሙ በተሠሩት በአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች አገግመው ተፋሰሶቹ ሁሉ ለምተዋል፤ በደን ተሸፍነዋል:: በቂ ዝናብ በማግኘት ለኑሮ ምቹ በመሆኑም ዛሬ ለኑሮ የሚመርጡት ወረዳ ሆኗል::

አርሶ አደር መሐመድ አልይ በገመቺስ ወረዳ የወሌንሱ ሂደዲማ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው:: ያላቸው ተዳፋታማ ሩብ ሄክታር እርሻ መሬታቸው የጎሮ ቢፍቱ ተፋሰስ አካል ነው:: በፕሮግራሙ የጠረጴዛ እርከን የተሠራበትን ምርሻ መሬታቸውን ፈጥነው ነው በተሻሻለ የእንስሳት መኖ ያለሙት::

አርሶ አደር መሐመድ እንደገለፁት ብድር ውስጥ ሳይገቡ ያለሙትን የእንስሳት መኖ ሸጠው የቆጠቡትን ገንዘብ በመጨመር በሬ ገዝተው ማደለብ ጀመሩ:: ያደለቡትን በሬ በ200 ሺህ ብር በመሸጥ ሁለት ጊደሮችና 3 ወይፈኖችን ገዙበት:: ጊደሮቹ ወልደው ዛሬ ወተት ያመርታሉ፤ ከቤተሰባቸው ፍጆታ የሚቀረውን ወተት ሸጠው ገቢ ያገኛሉ:: 3 በሬዎችን በጥሩ ሁኔታ እያደለቡ ይገኛሉ:: መኖሪያ ቤታቸውን ከሳር ቤት ወደ ቆርቆሮ ቤት መቀየር ችለዋል::

ድሬዳዋ ከተማ ዙሪያው ተራራማ በመሆኑ በጎርፍ መጥለቅለቅ በሰውና በንብረት ላይ የደረሰው ከፍተኛ ጉዳት የቅርብ ጊዜ ትውስታ ሲሆን ዛሬ ግን ያ ታሪክ ተቀይሯል:: በሁላሁሉል ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው ሀንደቃ ተፋሰስ በ38 የገጠር ቀበሌዎቹ ውስጥ ከሚገኙት ተፋሰሶች መካከል አንዱ ነው::

ተፋሰሱ ከ700 ሄክታር በላይ ይሆናል:: በፊት እጅግ ተጎድቶ በመራቆቱ የአካባቢው ማኅበረሰብም ለከፋ ችግር ተጋልጦ ነበር:: በተፋሰሱ ላይ በተሠሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ውጤት ተገኝቷል:: ተፋሰሱ በደንብ አገግሞ ለምቷል፤ በደን ተሸፍኗል:: ከጋራ ላይ በሚወርደው ጎርፍ የአፈር መሸርሸር ቆሟል፤ የዝናብ ሁኔታ ተሻሽሏል፤ የደረቁ ምንጮች ፈልቀው የነበሩም ጎልብተዋል::

ዛሬ ሌላውንም ቀበሌ ማልማት የሚችል የመስኖ ውሃ በቀበሌው ውስጥ ስላለ እርሻቸውን በመስኖ በማልማት የግብርና ምርትና ምርታማነት እንደጨመረላቸው የአካባቢው አርሶ አደሮች ገልፀዋል::

አርሶ አደር ከማል አብዱረሐማን በአሳልሶ ክላስተር የሁላሁሉል ቀበሌ ነዋሪ ናቸው:: የሀንደቃ ተፋሰስ ልማት ውጤሠት ተቋዳሽ ሆነዋል:: መስኖን በመጠቀም ከሁለት ጊዜ በላይ ማምረት ችለዋል:: ከፕሮግራሙ የቀረበላቸውን ምርጥ ዘር በመጠቀም ከቀይ ሽንኩርት ጀምረው የተለያዩ የአትክልት ዓይነቶችና ፍራፍሬዎችን በማልማት ለገበያ አቅርበው ገቢ ያገኛሉ:: በተለይ ከፍራፍሬዎች ጥሩ ገቢ የሚያገኙባቸው ብርቱካን፣ ፓፓያና ሙዝ ይጠቀሳሉ:: አርሶ አደር ከማል 7 ከብቶች፣ 20 ፍየሎችና ከባንክም 70 ሺህ ብር ጥሬ ገንዘብ እንዳላቸው ተናግረዋል:: ዘንድሮ ከልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በራሳቸው ፍቃድ ተመርቀዋል::